# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
## የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### ሦስተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ግንቦት
፳፻፯ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት**

__አድራሻ__፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

www.zeorthodox.org

**Email:- kesisolomon@gmail.com**
**Website፡- www.zeorthodox.org**

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ። በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም።

# መታሰቢያነቱ



በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ድርብ ኃላፊነትን ተሸክመው፣ በመንፈሳዊ አገልግሎት የቀና፣ ወለም ዘለም የማይል መንገድ መከተል የሚያስገኘውን በረከት አርአያ ሆነው ላስተማሩኝ በ2006 ዓ.ም. የ96 ዓመት አረጋዊ ለሆኑ አባቴ ለመምህሬ ከበደ መንገሻ ዘአምቦ መሠረተ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ቤ/ክ ይሁንልኝ።

www.zeorthodox.org

# ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል።

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | አረጋዊ ስምዖን | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | ቅዱስ ቁርባን | 4 | | ሁለተኛ | |
| 3. | ነገረ መላእክት | 7 | | ሦስተኛ | |
| 4. | ለጌዴዎን የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠ | 9 | | አራተኛ | |
| 5. | ለማኑሄ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠ | 11 | | አምስተኛ | |
| 6. | ምግባረ ሠናይ በጣቢታ ሕይወት | 13 | | ስድስተኛ | |
| 7. | ቅዱስ እስጢፋኖስ | 15 | | ሰባተኛ | |
| 8. | የመስቀል ኃይል | 17 | | ስምንተኛ | |
| 9. | እግዚአብሔር ሙሴን ለአገልግሎት ጠራ | 19 | | ዘጠነኛ | |
| 10 | የፈርዖን አለመታዘዝ | 21 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | ፋሲካ | 23 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | ቀይ ባሕርን መሻገር | 25 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | እግዚአብሔር ሕዝቡን በደመና እና በብርሃን መራ | 27 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | ሙሴ ዐሠርቱ ቃላትን ተቀበለ | 29 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | የእስራኤል ማጉረምረም | 31 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | የቃል ኪዳኑ ታቦት | 33 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | የአዳም ከገነት መባረር | 35 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | የክርስቶስ በበረት መወለድ | 37 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | የክርስቶስ ጥምቀት | 39 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መረጠ | 41 | | ሃያኛ | |
| 21. | የባቢሎን ግንብ | 43 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | ቅዱስ ቁርሎስ | 45 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | የመበለቷ ሁለት ሳንቲም | 47 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | አብርሃም ለይስሐቅ ሚስት አገኘለት | 49 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | እግርን ማጠብ | 51 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ኢየሱስ የቤተ ሳይዳውን እውር ፈወሰ | 53 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ምጽዋት | 55 | | ሃያ ሰባተኛ | |


www.zeorthodox.org

| ተ. ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ዕርገተ ክርስቶስ | 57 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠ | 59 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | ጰራቅሊጦስ | 61 | | ሠላሳኛ | |
| 31. | ካህናትን ማክበር | 63 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | የቅዱሳን ሐዋርያት በዓል | 65 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | ንስሐ | 67 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | የእመቤታችን በዓላት | 69 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ምልጃ | 71 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | ምስጋና | 73 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | አብርሃምና ሣራ | 75 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃልኪዳን አደረገ | 77 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | አብርሃም ተራብ | 79 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | አብርሃም ለጌራራ ንጉሥ ጸሎት አደረገ | 81 | | ዐርባኛ | |
| 41. | አጋርና እስማኤል | 83 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | ይስሐቅ ተወለደ | 85 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕትነት አቀረበ | 87 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | በሐረግ የታሰረው በግ | 89 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | የያዕቆብ ሕልም | 91 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | በትምህርት ውጤታማ መሆን | 93 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | የአገልግሎት ሕይወት | 95 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከ | 97 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | ያዕቆብ ለመባረክ ታገለ | 99 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | ይስሐቅ ርብቃን አባ | 101 | | ሃምሳኛ | |

www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

www.zoorthodox.org

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል። በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ።

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ።

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው። በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል።

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል። በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሚያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል። ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው።

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው። ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ። በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ። በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ።

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም። በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

www.zeorthodox.org

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጎብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጎብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# አረጋዊ ስምዖን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ የሚፈጽም በቃሉ የታመነ አምላክ እንደሆነ ለልጆች ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፡፡" ሉቃስ. ፪÷፳፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የኢሳይያስ. ፯÷፲፬ እንድምታ እና ሉቃስ ፪÷፳፪-፴፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ አረጋዊ ስምዖን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- ከእግዚአብሔር ተስፋ ተቀብለው የተፈጸመላቸውን ሰዎች ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- እመቤታችን ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ወደ መቅደስ ለምን አመጡት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አረጋዊ ስምዖን በኢየሩሳሌም ይኖሩ ከነበሩ ሊቃናት (መተርጉማን) መካከል አንዱ ነው፡፡ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ284 ዓ.ዓ. በጥሊሞስ የሚባል የግሪክ ንጉሥ ነበረ፡፡ ይህ ንጉሥ "ለወገኔ ያላደረኩት ምን አለ?" በማለት አማካሪዎቹን ሲጠይቅ "የኦሪትና የነቢያትን መጻሕፍት በቋንቋችን አላስተረጎምከም" አሉት፡፡ በጥሊሞስም መጻሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ግሪክኛ ቋንቋ የሚመልሱ (የሚተረጉሙ) ሰባ ሊቃውንትን ከኢየሩሳሌም አስመጣ፡፡ ከእነዚህ የተመረጡ መተርጉማን መካከል አረጋዊ ስምዖን አንዱ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል ለአረጋዊ ስምዖን ደረሰው፡፡ አረጋዊው ስምዖን ይህን የትንቢት መጽሐፍ ሲተረጉም "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች" የሚል የጸና የትንቢት ቃል አገኘ፡፡ "ይህን ቃል ብጽፈው ይህ ዓላዊ ንጉሥ ሐሰተኛ ብሎ ይቀጣኛል" በማለት ፈርቶ "እነሆ ሴት ትፀንሳለች" በሚል ቃል ተካው፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች" የሚለውን የጸና አምላካዊ ቃል እንደገና ጻፈ፡፡

አረጋዊ ስምዖንም እንደገና ይህን ቃል "እነሆ ሴት ትፀንሳለች" በሚል ተካው፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ በራእይ ተገልጦ "የዚህን የትንቢት ቃል ፍጻሜ ሳታይ አትሞትምና ቃሉን እንደተጻፈው ተርጉም" አለው፡፡ ስምዖን ይህን ራእይ ካየ በኋላ "እነሆ

ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙም አማኑኤል ይባላል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው" በማለት ተረጎመ፡፡ አረጋዊው ስምዖን ትንቢተ ኢሳይያስን ተርጉሞ ካስረከበ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ የእስራኤልን መጽናናት ለረጅም ዘመናት ይጠባበቅ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት መቀመጥና መነሣት ተስኖት ከአልጋ ተጣብቆ ይኖር ነበር፡፡ ልጆች ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ ስለ አረጋዊ ስምዖን "በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበር፤ ይህ ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፤ ጻድቅና ትጉህም ነበር፤ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ፡፡ በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር" በማለት ምስክርነት ሰጥቷል፡፡

እንደ ሙሴ ሕግ የመንጻት ሥርዓት በተፈጸመ ጊዜ እመቤታችን ማርያምና አረጋዊ ዮሴፍ ጌታችን ኢየሱስን ወደ መቅደስ አመጡት፡፡ ሕገ መጽሐፋዊን ማለትም ልማደ አይሁድን ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን ወደ መቅደስ ባስገቡት ጊዜ አረጋዊ ስምዖን ኢየሱስን ከማርያም ተቀብሎ አቀፈው፡፡ ከዚያም "ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና" በማለት ተናገረ፡፡ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ፈጽሞለታልና፡፡ አረጋዊ ስምዖን ዮሴፍና ማርያምን ባረካቸው፡፡ የጌታችን ኢየሱስን እናት እመቤታችን ማርያምን "እነሆ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ ይህ (ልጅሽ) በእስራኤል ላሉት ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፤ በአንቺም በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል" አላት፡፡

## ማጠቃለያ

አረጋዊ ስምዖን የመጻሕፍት ተርጓሚ ሊቅ፣ በሥራው ሁሉ ትጉህ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጻድቅና መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ነቢይ ነበር፡፡ ትንቢተ ኢሳይያስን ወደ ግሪክ (ፅርዕ) ቋንቋ ሲተረጉም የትንቢቱን ፍጻሜ ሳያይ ሞትን እንደማያይ ቃል ተገብቶለት ለረጅም ዘመናት የእስራኤልን መጽናናት እየተጠባበቀ ኖረ፡፡ እግዚአብሔርም በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀውን ማዳኑን አሳየው፤ ቃል የገባለትንም ፈጸመለት፡፡ አረጋዊ ስምዖንም እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ስለ ክርስቶስ ትንቢት ተናገረ፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ቃል የገባልንን በማድረግ፤ የሰጠንን ተስፋ በመፈጸም አይጠረጠርም፤ ስለ ተስፋ ቃሉ የታመነ ጌታ ነውና፡፡

www.zeorthodox.org

### ጥያቄዎች

1. የስምዖን ሥራ ምንድን ነበር?
2. "ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች" የሚል የትንቢት ቃል ያለው የትንቢት መጽሐፍ ማን ነው?
3. መጻሕፍተ ብሉያቱን ወደ ግሪከኛ ቋንቋ ለመተርጎም የተመረጡት ስንት ሊቃውንት ነበሩ?
4. አረጋዊው ስምዖን ኢየሱስን በእናቱ እቅፍ ባየው ጊዜ ምን አደረገ? ምንስ አለ?
5. አረጋዊ ስምዖን ስለ እመቤታችን ማርያም የተናገረው የትንቢት ቃል ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ የአረጋዊው ስምዖንን ጸሎት ልጆች በጋራ እንዲጸልዩት ያድርግ!!
- ከልጆች መካከል አንዱ የስምዖንን ታሪክ በአጭሩ እንዲተርክ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቁርባን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቅዱስ ቁርባን ትልቁ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ልጆች እንዲያውቁና ይህን ታላቅ ስጦታ በየጊዜው በደስታ እንዲቀበሉ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ” ዮሐ. ፮÷፶፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፮÷፶፩-፶፰፣ ምሳሌ ፱÷፩-፮ እና ማቴ. ፳፮÷፳፮-፳፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ልጆች ቅዱስ ቁርባን ተቀብላችሁ ታውቃላችሁ?
- ቅዱስ ቁርባን ማቀበል የሚችሉት እነማን ናቸው?
- ስለ ቅዱስ ቁርባን የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ቁርባን ከሰባቱ የቤተክርስቲያን ምስጢራት መካከል አንዱ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ለአማኞቿ ምስጢራትን ትፈጽማለች፡፡ በሚታየው የምስጢራት አፈጻጸም ሥርዓት የማይታየውን የእግዚአብሔር ጸጋ ታሰጣለች፡፡ ቅዱስ ቁርባን አምነው ለተጠመቁ ምእመናን የሚሰጥ የሚደገም ምስጢር ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን አምነን ከተጠመቅንበት ከሕፃንነታችን ጊዜ ጀምሮ በዘመናችን ሁሉ የምንቀበለው አምላካዊ ስጦታ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

በብሉይ ኪዳን ሰው ለእግዚአብሔር የሚያቀርባቸው መሥዋዕቶች ነበሩ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን ከእግዚአብሔር ለሰው ታላቅ ስጦታ ተሰጠ፤ ይህም ቅዱስ ቁርባን ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን ሰው ለኃጢአቱ ስርየት እንስሳትን መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አያቀርብም፡፡ በሥጋ የተገለጠው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ኃጢአት አንድ ጊዜ መሥዋዕት ሆኗል፤ ለዘላለምም ያድናል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱንና የተከተሉትን ሰዎች ሲያስተምር "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡፡ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው፡፡ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፡፡ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፡፡" አለ፡፡

ልጆች እስራኤል በምድረ በዳ መና ወርዶላቸው በልተዋል፤ ነገር ግን በበረሐ ሞተው ቀርተዋል፤ የበሉት የሥጋ ምግብ ነውና፡፡ ክርስቶስ ግን ሕያው እንጀራ ነው፤ ሕያውም ያደርጋል፡፡ እርሱን አምኖ በበረሐ መቅረት የለም፡፡ ከእርሱ በልቶ መሞት የለም፡፡ ስለዚህ ሕያው የሚያደርገን የሕይወት እንጀራ በቅዱስ ቁርባን ይሰጠናል፡፡

ጌታ ኢየሱስም "እውነት እላችኋለሁ ሥጋዬን ካልበላችሁ ደሜንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡ የሚበላኝ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል" በማለት አስረግጦ ነገራቸው፡፡ እነርሱ ግን ፈቀቅ አሉ፤ ንግግሩ አስጨንቋቸው ነበርና፡፡ ያመኑት ደቀመዛሙርቱ "ካንተ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ" በማለት ከእርሱ ጋር ኖሩ፡፡ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ይህን ቃሉን ለመፈጸም የጸሎተ ሐሙስ ሥርዓት ሠራ፡፡

ኅብስቱንም አንሥቶ ባረከ፤ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና "እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው" አለ፡፡ ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖም ባረከና ሰጣቸው፡፡ እንዲህም አለ "ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ማቴ. ፳፮÷፳፮፡፡ **የቁርባንን ሥርዓትን የሠራው፤ ደቀመዛሙርቱንም** ያስተማረው ራሱ የሥርዓቱ ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ አድኖናል፡፡ ሥርዓተ ቁርባንን ከሥጋ ወደሙ ጋር በካህኑ ጸሎት በምስጢር ኅብረት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ቅዱስ ሥጋውን እንድንበላ ክቡር ደሙንም እንድንጠጣ ያዘዘን እርሱ ነው፡፡ **፩ቆሮ ፲÷፲፮፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ቁርባንን በደስታ ስንቀበል ለኃጢአታችን ይቅርታ እናገኛለን፡፡** የዘላለም ሕይወት እናገኛለን፡፡ ከክርስቶስ ጋር በመንፈስ ኅብረት እናደርጋለን፡፡ ትእዛዙንም በመፈጸማችን አምላካችን ደስ ይለዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ቁርባን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባንን ስንቀበል የዘላለም ሕይወት ይኖረናል፡፡ ስለዚህ ትእዛዙን በመፈጸም ለዘላለም የማይጠፋ ሕይወት ለማግኘት፤ ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት፣ ቅዳሴ ማስቀደስና ቅዱስ ቁርባንን በዘመናችን ሁሉ በደስታ መቀበል አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

1. የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት የሠራው ማን ነው?
2. የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ማን ነው?
3. ቅዱስ ቁርባንን በመቀበላችን የምናገኛቸውን ጥቅሞች ተናገር?

## ተግባር

- መምህሩ ከቅዱስ ቁርባን በፊትና በኋላ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን ለልጆች ይንገራቸው፡፡
- በዕለተ ሰንበት ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ ያበረታታቸው! ልጆች በመርሐ ግብር እንዲቀርቡ ከወላጆቻቸው ጋር በመነጋገር ሁኔታዎችን ያመቻችላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ነገረ መላእክት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የመላእክትን ተፈጥሮና አገልግሎት ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት (ቅዱሳን መላእክት) ናቸው፡፡" ዕብ. ፩÷፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፴፫÷፯፤ ፺÷፲፩-፲፬፣ ማቴ. ፬÷፲፩ እና ማቴ. ፳፪÷፴

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የመላእክትን አገልግሎት ታውቃላችሁ?
- ልጆች ስለ መላእክት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- የምታውቋቸውን የመላእክት ስም ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
- ወርኃዊ የሆኑ የመላእክት በዓላትን ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መላእክት በዕለተ እሑድ የተፈጠሩ ፍጥረታት ሲሆኑ የእግዚአብሔር መልእክተኞችና የሰው ጠባቂዎች ናቸው፡፡ መላእክት ረቂቃን መናፍስት ናቸው፤ እንደ ሰው ሥጋና አጥንት የላቸውም፡፡ መላእክት መንፈሳዊ አካልና ማሰብ የሚችል ነጻ አእምሮ አላቸው፡፡ መላእክት የሥጋ ሥራን አይሠሩም፡፡

ልጆች ስለወደቁት መላእክት ታውቃላችሁ? ለእግዚአብሔር ባለመገዛታቸው ዲያብሎስና የጨለማው ሠራዊት ወደ ጥልቁ ተጥለዋል፡፡ እነዚህ መላእክተ ጽልመት ወይም ርኩሳን መላእክት ይባላሉ፡፡ አለቃቸው ዲያብሎስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ናቸው፡፡ ሰው ከአምላኩ ሕግ እንዲወጣና ክፉ በማድረግ እንዲጸና ተግተው ይሠራሉ፡፡ ዓላማቸው ሰውን ከእግዚአብሔር መንግሥት መለየት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ለዘላለም በእሳት ይጣላሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች እኛን የሚያገለግሉን ቅዱሳን መላእክት (ብርሃናውያን መላእክት) ናቸው፡፡ የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ማመስገንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያለመታከት መጠበቅ ነው፡፡ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ዙሪያ ይከባሉ ያድኗቸዋልም፡፡ መዝ. ፴፫÷፯

ቅዱሳን መላእክት ብዛታቸው የማይቆጠር ነው፡፡ እውቀታቸው ምጡቅ ኃይላቸው ታላቅ ነው፡፡ ቅዱሳን መላእክት በንስሐ በሚመላሱ ኃጥአን ደስ ይላቸዋል፡፡ ሉቃ ፲፭÷፲

ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን የማያምኑትን የሕዝብ ጠላቶች ይቀጣሉ፡፡ ሐዋ. ፲፪÷፳፫፡፡ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ያላቸውን አማኞች ያግዛሉ፡፡ ዕብ ፪÷፲፬፡፡

በብሉይ ኪዳን እስራኤል ዘሥጋን መላእክት ጠብቀዋል፡፡ እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ወደ ምድረ ርስት ከነዓን ባደረጉት ጉዞ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ በመንገዳቸው እያስቀደመ አስጠብቋቸዋል፡፡ በሐዲስ ኪዳንም ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ያላቸውን የሚያግዙ መላእክትን ይልክላቸዋል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ብርሃናውያን መላእክትን ፈጠረ፡፡ እነዚህ ቅዱሳን መላእክት በፊቱ ቆመው ቀንና ሌሊት ሳይደክሙና ሳያቋርጡ ያመሰግኑታል፤ በእግዚአብሔር የሚያምኑትን ሰዎች በፊታቸው እየቀደሙ ይጠብቃሉ፡፡ እርሱን የማያምኑትን ይቀጣሉ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት ምንድን ነው?
2. የወደቁት መላእክት አለቃ ማን ነው?
3. ቅዱሳን መላእክትን ወደ እኛ የሚልክልን ማን ነው?
4. ቅዱሳን መላእክት የተራዷቸውን ሰዎች ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱን ስለ መላእክት የተማሩትን እንዲናገር ያድርግ፡፡
- መዝሙር “**፯**”**ን** በጋራ እንዲያነቡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ስጌዴዎን የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር መላእክቱን በመላክ ጠላቶቻችንን እንደሚቋቋም ለልጆች ማስገንዘብ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና አትፍራ" ኢያሱ. ፩÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መሳፍንት ፮ እና ዕብ. ፲፩÷፴፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የእስራኤልን መሳፍንት ታውቃላችሁ?
- ስለ መስፍኑ ጌዴዎን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- መላእክት ወደ እግዚአብሔር አገልጋዮች የሚላኩት ለምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሠሩ፡፡ ክፋታቸውም እግዚአብሔርን አሳዘነው፡፡ ስለዚህ ለምድያም አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ ምድያማውያን ለሰባት ዓመታት አስጨንቀው ገዙአቸው፡፡ እስራኤላውያን በእርሻቸው ዘር በዘሩ ጊዜ ጠላቶቻቸው ይመጡባቸው ነበር፡፡ ቡቃያቸውንም ያጠፉባቸው ነበር፡፡ እንስሳቶቻቸውንም ይወስዱባቸው ነበር፡፡ እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡፡ እግዚአብሔርም መልአኩን ላከ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ በዖፍራ በወይን መጥመቂያ ውስጥ ስንዴ ሲወቃ ወደ ነበረው ወደ ጌዴዎን መጣ፡፡

www.zoorthodox.org

ጌዴዎን ከእስራኤል መሳፍንት አንዱ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠለት፡፡ መልአኩ "አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው" አለው፡፡ ጌዴዎንም "ጌታዬ ሆይ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን? አባቶቻችንን ከግብጽ ያወጣ ተአምራቱ ወዴት አለ? እግዚአብሔር ትቶናል" አለው፡፡ መልአኩም እግዚአብሔር የወገኑን ነጻነት በእጁ እንዳደረገለት ነገረው፡፡ የነገረውም እንደሚፈጸም ምልክት ሰጥቶት ተሰወረ፡፡ ጌዴዎን እስራኤልን ከምድያም እጅ ሊያድን ተጠራ፡፡ የበአልን መሠዊያ ካፈረሰ በኋላ ይሩበአል ተብሎ ተጠራ፡፡ ከሦስት መቶ ሰዎች ጋር ሆኖ ምድያምን ወጋ፤ አሸነፋቸውም፡፡ አርባ ዓመት ምድሪቱን ከጠላት አገዛዝ አሳርፎ ገዛ፡፡

እግዚአብሔር ሕዝቡን አስጨንቆ የሚገዛ ሥርዓትን ይቃወማል፡፡ የሕዝቡን እንቅስቃሴ ከአድማስ እስከ አድማስ በሁሉም ቦታ በሚመለከቱ ዓይኖቹ ስለሚቆጣጠር ሕዝቡን የሚጎዳ ነገር ሲመለከት መላእክቱን ይልካል፤ መላእክቱም የሕዝቡን ጠላት

ይቋቋማሉ፡፡ እግዚአብሔር በምንሄድበት ሁሉ ከእኛ ጋር ስለሆነ ክፉ ሊነካን አይችልም፡፡

## ማጠቃለያ

ጌዴዎን የእስራኤል መስፍን ነበር፡፡ በዖፍራ ተሸሽጎ ስንዴ ሲወቃ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠለት፡፡ ሕዝቡን ከምድያም ጽኑ አገዛዝ ነጻ አወጣ፡፡ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በማምለክ ጸንተው ሕግጋቱን አክብረው እንዲገዙ መከራቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር መውጣትና መግባታችንን የሚጠብቅ አምላክ ስለሆነ ክፉ አያገኘንም፤ መላእክቱ የሚጣሉንን ሊቋቋሙልን በዙሪያችን አሉና፡፡

### ጥያቄዎች

1. መልአኩ ሲገለጥለት ጌዴዎን ምን ይሠራ ነበር?
2. እስራኤልን ለሰባት ዓመት ያስጨነቋቸው ጠላቶች እነማን ናቸው?
3. የእግዚአብሔር መልአክ ጌዴዎንን ምን አለው?
4. ጌዴዎን ጣዖትን ካፈረሰ በኋላ የወጣለት ስም ማን ይባላል?
5. ጌዴዎን የእስራኤልን ምድር ለስንት ዓመታት በሰላም አሳርፎ ገዛ?
6. ልጆች ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- መምህሩ ከተማሪዎች መካከል አንዱ ታሪኩን ደግሞ እንዲተርክ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ለማኑሄ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቅዱሳን መላእክት ታሪክ የሚለውጥ የምሥራች ይዘው ወደ ሰው እንደሚመጡ ለልጆች ማሳወቅ/ማስገንዘብ/፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናል፡፡" መሳ. ፲፫÷፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መሳ. ፲፫÷፩-፳፭ እና ሉቃ. ፩÷፳፮-፴፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በብስራተ መልአክ የተወለዱ አባቶች እነማን ናቸው?
- ናዝራዊ ማለት ምን ማለት ነው?
- የሶምሶንን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? ማኑሄ የሶምሶን አባት መሆኑንስ ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ማኑሄ ማለት ዕረፍት ማለት ነው፡፡ ከዳን ወገን የነበረ ሰው ነው፡፡ ሚስቱ መካን ነበረች፡፡ በአንድ ወቅት መካን ለነበረችው ሚስቱ ማኑሄ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለጠላት፡፡ "ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ የሚያሰክር መጠጥ አትጠጪ፤ የሚያረክስም ነገር አትንኪ፤ የምትወልጅው ልጅ ዘመኑን ሙሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናል" አላት፡፡

ሴቲቱም የሰማችውን ለባሏ ለማኑሄ ነገረችው፡፡ ማኑሄም "ጌታ ሆይ የላክኸው እንደገና ወደ እኛ ይምጣ" በማለት ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም የማኑሄን ጸሎት ሰማ፤ መልአኩንም እንደገና ወደ እነርሱ ዘንድ ላከ፡፡

www.zeorthodox.org

የእግዚአብሔር መልአክ ለሴቲቱ በእርሻ ተቀምጣ ሳለ እንደገና ተገለጠላት፡፡ ፈጥና ባሏን ማኑሄን ጠራች፡፡ ማኑሄም የእግዚአብሔርን መልአክ አየው፡፡ መልአኩን "ከሚስቴ ጋር የተነጋገርህ አንተ ነህ?" አለው፡፡ የእግዚአብሔር መልአክም "አዎ እኔ ነኝ" አለ፡፡ ማኑሄም "ቃልህ በደረሰ ጊዜ የልጁ ሥርዓት ምንድን ነው?" አለው፡፡ መልአኩም "ለሚስትህ ከነገርኋት ሁሉ ተጠንቀቅ" አለው፡፡ ማኑሄም "የፍየል ጠቦት እስክናዘጋጅልህ እባክህን ቆይ" አለው፡፡ መልአኩ "የሚቃጠል መሥዋዕት ማዘጋጀት ብትወድ ለእግዚአብሔር አቅርበው" አለው፡፡ ማኑሄም "ነገርህ በደረሰ ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማን ነው?" አለው፡፡

የእግዚአብሔርም መልአክ "ስሜ ድንቅ ነው" አለው፡፡ ማኑሄም መሥዋዕት አቀረበ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ዐረገ፡፡ በመልአክ እንደተነገረው ወንድ ልጅ ወለዱ ስሙንም ሶምሶን አሉት፡፡

## ማጠቃለያ

ማኑሄ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ የምሥራችን ወደ ቤቱ አመጣለት፡፡ በመልአኩም እንደተነገረው ወንድ ልጅ ወለዱ፡፡ እርሱም ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ነበረ፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ማኑሄ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የእግዚአብሔር መልአክ ማኑሄን ምን አለው?
3. ናዝራዊ ራሱን ከምን ይጠብቃል?
4. ማኑሄ በብስራተ መልአክ ማንን ወለደ?
5. ልጆች ከታሪኩ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ታሪኩን እንደገና እንዲተርክ ያድርግ፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ምግባረ ሠናይ በጣቢታ ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ለድሆች ቸርነት ማድረግን እንዲለምዱ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ ስለምታገለግሉአቸውም ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር አይረሳም፡፡" ዕብ. ፮÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፱÷፴፮-፵፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ድሆችን በምትችሉት መጠን ረድታችሁ ታውቃላችሁ?
- የባለፈው ሳምንት በቃል የሚጠና ጥቅስ ምንድን ነበር?
- ጣቢታን ከሞት ያስነሣት ሐዋርያ ማን ነው?
- ልጆች ለካህናት ትታዘዛላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ከኢየሩሳሌም ስልሣ ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ በምትገኘው የይሁዳ ወደብ በሆነችው በኢዮጴ ጣቢታ የምትባል ደግ ሴት ትኖር ነበር፡፡ ይህች ስፍራ በአሁኑ ጊዜ የእስራኤል ሀገር ዋና ከተማ በሆነው ቴልአቪቭ ክፍለ ከተማ ስትሆን ጃፋ በሚባል ስም ትታወቃለች፡፡ በሐዋርያቱ የአገልግሎት ዘመን ጣቢታና ሌሎች ደጋግ ክርስቲያኖች ኖረውባታል፤ ቅዱስ ጴጥሮስም አገልግሎባታል፡፡

ጣቢታ ማለት ዶርቃ ማለት ነው፡፡ ድሆችን የምትመግብ፤ የታረዙትን የምታለብስ፤ ችግረኞችን በመመጽወት የምትታወቅ መልካም ሴት ነበረች፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስን በፍጹም ልቧ የምትወድ ሳታቋርጥ የምትጸልይና በሁሉ የምታመሰግን ክርስቲያን ነበረች፡፡ ስለዚህ ቅዱሳን ሐዋርያት ይወዱአት ነበር፤ በቤቷም ያርፉ ነበር፡፡ ጣቢታ ከእግዚአብሔር የተቀበለችውን በደስታ የምትሰጥ፤ ብድር መመለስ ለማይችሉ ድሆች የቸርነት ሥራ የምትሠራ ሴት በመሆንዋ የአካባቢዋ ሰዎች ያከብሯት ነበር፡፡ በአንድ ወቅት በጽኑ ታመመችና ሞተች፡፡ የአካባቢዋ ሰዎች እያለቀሱ ሥጋዋን አጥበው በሰገነት በክብር አስቀመጡ፡፡ ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ላኩ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጴጥሮስም ልዳ ከሚባል ቦታ መጣ፡፡ ወደ ሰገነት ወጣ፤ ተንበርክኮ ጸለየ፤ ወደ ሬሳዋም ዞወር ብሎ "ጣቢታ ተነሺ" አላት፡፡ ጣቢታ ዓይኖቿን ከፈተች ከሞትም ተነሣች፤ የሚያውቋት ሁሉ ደስ አላቸው፤ የኢዮጴ ሰዎችም በሆነው ተደነቁ፤ ኃይልን

በሚሰጠው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ፡፡ እግዚአብሔር ያገለገሉትን እንደማይጥል አወቁ፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች ዛሬ ብድራት ሳትጠብቁ የምታደርጉት መልካም ነገር በአንድ ወቅት ሕይወታችሁን ከሞት ያድናል፡፡ ለተቸገሩ ሰዎች ቸርነት ብታደርጉ ስትቸገሩ በጎ የሚያደርጉላችሁ ሰዎችን እግዚአብሔር ያዘጋጃል፡፡ ድሆችን መርዳት መልካም ተግባር ነው፡፡ መልካም የሚያደርጉ ደግሞ ከመልካም ነገር ሁሉ አይጎድሉም፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ጣቢታ ምን ትሠራ ነበር?
2. ቅዱስ ጴጥሮስ ጣቢታን ከሞት ለማስነሣት ምን አደረገ?
3. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- *መምህሩ ልጆች ትርፍ የሆኑና ያለቁ ልብሶቻቸውን አምጥተው ለተቸገሩ ነዳያን መስጠትን እንዲለማመዱ ያድርግ፡፡*

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ እስጢፋኖስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔር ያከበራቸውን ቅዱሳን እንዲያከብሩና በእምነት እንዲመስሏቸው ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው" ሐዋ. ፯÷፷

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፯÷፶፬-፷፣ የጥር አንድ ቀን ስንክሳር

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የምታውቋቸውን የሰማዕታት ስም ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ልጆች ቅዱሳን እነማን ናቸው?
- ልጆች ቅዱሳንን ለምን እናከብራቸዋለን?
- ልጆች ስለ ቅዱስ እስጢፋኖስ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በደሙ የመሠረታት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በጽርሐ-ጽዮን ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከተቀበለች በኋላ የትንሣኤውን ወንጌል ለትውልድ ማድረስ ጀመረች፡፡ ወንጌል እየተስፋፋ አማኞች እየበዙ መጡ፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት የሚያግዟቸው ሰባት ጠቢባን ወጣቶችን መርጠው የዲቁና ሥልጣን ሰጡአቸው፡፡ ከተሾሙት ዲያቆናት መካከል ቅዱስ እስጢፋኖስ አንዱ ነው፡፡ ሐዋ. ፮÷፭.

ቅዱስ እስጢፋኖስ የዲያቆናት አለቃ ነበር፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር፡፡ ከግሪክ አገር የመጡ አይሁድ በተከራከሩት ጊዜ በመንፈስና በጥበብ መለሰላቸው፡፡ አይሁድም ዳኞች በተሰየሙበት ሸንጎ ፊት አቅርበው በሐሰት ከሰሱት፤ ሸንጎውም በድንጋይ እንዲወገር ፈረደበት፡፡

www.zeorthodox.org

እስጢፋኖስ ግን በታላቅ ኃይልና በብዙ መረዳት ከአባቶቻቸው ታሪክ ተነሥቶ የዓለም መድኃኒት የሆነውን ክርስቶስን ሰበከላቸው፡፡ ጥላውን ከአካሉ ጋር እያጋጠመ ወደ ፍጹማን ጥበብ በጽድቅ ቃል መራቸው፡፡ አይሁድ በጣም ተቆጡ፤ ሁሉም በአንድነት ሆነው በድንጋይ ወገሩት፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰውነቱ ቆስሎና ዝሎ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ባነሣ ጊዜ የልዑልን ክብር ተመለከተ፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ ቀኝ ቆሞ አየ፡፡ ሐዋ. ፯÷፶፭፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ "እነሆ ሰማያት

**ተከፍተው** የሰው ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በአባቱ ቀኝ ቆሞ አያለሁ" አላቸው፡፡ አይሁድ ግን ልበ-ደንዳኖች (የማይራራ ጨካኝ ልብ ያላቸው) ስለሆኑ እስጢፋኖስን ከከተማ ወደ ውጭ አውጥተው ደበደቡት፡፡

ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰውነቱ ደከመ፤ ነፍሱ ከሥጋው ልትለይ በደረሰች ጊዜ በሞት ጣር ሆኖ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው፤ ነፍሴን ተቀበል" ብሎ ጸለየ፡፡ ነፍሱንም ለታመነው ፈጣሪ አደራ ሰጥቶ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡ የሰማዕትነት ሕይወትን በመጀመሩ ስለ ክርስቶስ ፍቅር መራራ ሞትን በመታገሡ ቀዳሜ ሰማዕት ተብሏል፤ የቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ሰማዕት ነውና፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች ቅዱስ እስጢፋኖስ በበረታች ጸጋ፣ በብዙ ጥበብና በማስተዋል እግዚአብሔርን ያገለገለ የመጀመሪያው ሰማዕት ነው፡፡ አይሁድ በድንጋይ ሲወግሩት ኃጢአታቸው እንዳይቆጠርባቸው ይቅርታን /ምሕረትን/ ያገኙ ዘንድ ጸለየላቸው፤ በዚህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አርአያነት መከተሉን አስመስክሯል፡፡ ልጆች ለሚበድሉን ይቅርታ ማድረግ አለብን፡፡ ክርስትና የፍቅር ሃይማኖት ነውና ስለ እግዚአብሔር ብለን ልንዋደድ ይገባል፡፡ ለሚያሳድዱን መጸለይ፣ የሚጠሉንን መውደድ፣ የሚረግሙንን መመረቅና ክፉውን በመልካም ማሸነፍ ይገባናል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ከቅዱስ እስጢፋኖስ ጋር ለዲቁና ሥልጣን የተሾሙት እነማን ናቸው?
2. የቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ሰማዕት ማን ነው?
3. ቅዱስ እስጢፋኖስ አይሁድ ሲወግሩት ምን ብሎ ጸለየላቸው?
4. ቅዱስ እስጢፋኖስ ዓይኖቹን ወደተከፈቱት ሰማያት ሲያነሣ ማንን አየ?
5. የሰው ልጅ የተባለው ማን ነው?

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ የዲያቆናት ሥራ ምን እንደሆነ ልጆቹን ይጠይቃቸው፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

# የመስቀል ኃይል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የመስቀሉን ቃልና ኃይል ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው" ፩ቆሮ. ፩፥፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፶፱፥፬፣ ኤፌ. ፪፥፲፮ እና ቆላ. ፪፥፲፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች መስቀል ማለት ምን ማለት ነው?
- መስቀል የምን ምልክት ነው?
- የመስቀል በዓል አከባበርን ለመምህራችሁ መንገር ትችላላችሁ?
- ግማደ መስቀሉ በየት ይገኛል?
- የመስቀል በዓል መቼ ይከበራል?
- በመስቀል ቅርጽ የምናማትብበት ምክንያት ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መስቀል የሰላም አርማ፤ የድል ምልክት ነው፡፡ መስቀል ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው "ዕፀ መስቀል" ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "መከራ መስቀል" ነው፡፡ ዕፀ መስቀሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደሙን ያፈሰሰበት ቅዱስ ሥጋውንም የቆረሰበት መሠዊያ ነው፡፡ ዕፀ መስቀሉ ከጠላት ቀስት ማምለጫ ነው፡፡ መከራ መስቀሉ የክርስቶስን መከራና የክርስቲያኖችን ነቀፌታ ያመለክታል፡፡ ክርስቶስ በፊቱ ስላለው ደስታ ነውርን ንቆ መከራን ታግሶ ከኃጢአተኞች የደረሰበትን ብርቱ ተቃውሞ ችሎ ከቅዱሳን ጉባኤ አስገብቶናል፡፡ ዕብ. ፲፪፥፫፡፡

www.zeorthodox.org

ክርስቲያኖች ደግሞ የክርስቶስን መከራ አብነትና መመኪያ በማድረግ መከራ መስቀሉን (ነቀፌታውን) ተሸክመው እረኛቸው ክርስቶስን ይከተላሉ፡፡ ማቴ. ፲፮፥፳፬፣ ፊልጵ. ፩፥፳፰፡፡ **መስቀል ክርስቶስ የዕዳችንን ጽሕፈት ደምስሶ ከመንገዳችን ያስወገደበት ኃይላችን** ነው፡፡ መስቀል የጥል ግድግዳ የፈረሰበትና ሰላም የተደረገበት የድል አርማ ነው፡፡ መስቀል የክርስቲያኖች መመኪያ ነው፡፡ ልጆች መስቀል የመዳን ቃል ነው፡፡ መስቀል የወንጌል ቃል ነው፡፡ መስቀል የማስታረቅ ቃል ነው፡፡ መስቀል የሕጉ ክስ የተሰረዘበትና እርግማን የተወገደበት ኃይል ነው፡፡

ስለዚህ የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፤ ለእኛ ለምንድን ግን ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ኃይላችን ነው፡፡ መስቀል ከቀስት ፊት ማምለጫ፤ የዲያብሎስ ድል መንሻ፤ በጠላትም ፊት ጋሻ ነው፡፡ ለዚህ ነው “መስቀል ኃይላችን ነው፡፡” እያልን የምንዘምረው፡፡

ቆስጠንጢኖስ የሚባል ንጉሥ በአንድ ሌሊት ሕልም አየ፡፡ ሕልሙም “የመስቀል ምልክት ይዘህ ብትዋጋ ጠላትህን ታሸንፋለህ” የሚል ነበር፡፡ ቆስጠንጢኖስም የመስቀል ምልክት በባንዲራውና በፈረሱ ኮርቻ ላይ አድርጎ ተዋጋ፤ ጠላቶቹንም አሸነፈ፡፡ መስቀል ኃይል እንደሆነ ተረዳ፡፡

## ማጠቃለያ

መስቀል የሰላም ምልክት፤ የድል አርማ፤ የአሸናፊዎች ሰንደቅ ነው፡፡ መስቀል ከቀስት ፊት የምናመልጥበትና ዲያብሎስን ድል የምንነሳበት ኃይላችን ነው፡፡ መስቀል ከጠላት የምንጋረድበት ጋሻችን ነው፡፡ መስቀል ጥል ተገድሎ ሰላም የተወጠነበት ትልቁ ኃይል ነው፡፡ ልጆች “ከጌታችን ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ” እያልን እንደ ቅዱስ ጳውሎስ በመስቀሉ ኃይል እንመካ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. መስቀል ስንት ዓይነት ነው?
2. መስቀል ምናችን ነው?
3. ክርስቶስ በመስቀሉ ምን አደረገ?
4. መስቀል የምን ምልክት ነው?
5. በመስቀል የተመካው ሐዋርያ ማን ነው?
6. የመስቀል ምልክት በሠራዊቱ ልብስና በባንዲራው አድርጎ ጠላቱን የረታ ንጉሥ ማን ይባላል?

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ የመስቀልን መዝሙር ልጆች እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡
- የተለያዩ የመስቀል ቅርጾችን ልጆች እንዲያዘጋጁ ያድርግ፡፡
- “መስቀል ኃይላችን ነው” የሚለውን የዘወትር ጸሎት እንዲጸልዩ ያድርግ፡፡

# እግዚአብሔር ሙሴን ለአገልግሎት ጠራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለከበረ ራእይ የተጠራንበትን ሰማያዊ ጥሪ ልጆች እንዲያውቁና ጠሪውን እንዲያከብሩ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነሆኝ እኔን ላከኝ" ኢሳ. ፮÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸአት. ፫፣፬፣ ፩ቆሮ. ፩÷፳፯ - ፳፱ እና ያዕ. ፪÷፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሙሴ እንዴት እንደተጠራ ታውቃላችሁ?
- እግዚአብሔር ሰዎችን ለምን ይጠራል?
- የሰማያዊው ጥሪ ዓላማ ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል የእነርሱ ባልሆነች ምድር ለአራት መቶ ሠላሳ ዘመናት ተቀመጡ፡፡ እስራኤላውያን ያለ ዕረፍት እየሠሩ፤ ያለ ደመወዝ እየኖሩ፤ የእነርሱ ለማትሆን ከተማ እየደከሙ፤ የመከራን ቀንበር ተሸክመው መራራ ለቅሶ አለቀሱ፡፡ እግዚአብሔርም የነጻነታቸውን ጎሕ በፊታቸው ሊያወጣ፤ በአረንጓዴ መስክ ያጌጡ ተራሮችና በወይን ዘለላ የተሞሉ ጓሮዎች ወዳሏት ከተማ ሊመራቸው ከመካከላቸው ሙሴን ጠራ፡፡

ሙሴ ከዕብራውያን የተወለደ የዕብራውያን (የእስራኤላውያን) ነጻ አውጭ ነው፡፡ ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን ንቆ፤ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መርጦ፤ የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ የግብጽን አገር በእምነት ተወ፡፡ በምድያምም የዮቶርን በጎች እየጠበቀ ሲፓራን አግብቶ ጌርሳምን ወልዶ መኖር ጀመረ፡፡

www.zeorthodox.org

በአንድ ወቅት በኮሬብ ወንዝ ዳርቻ በእግዚአብሔር ተራራ በሲና ከፍታ የለመለመው ቁጥቋጦ በእሳት ሲነድ፤ ነገር ግን ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው፤ የሐመልማሉም እርጥበት ነበልባለ እሳቱን ሳያጠፋው ተመለከተ፡፡ ሙሴ በተመለከተው ራእይ ተደነቀ፡፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን በስሙ ጠራው፡፡ "ሙሴ ሙሴ ሙሴ ሆይ" አለው፡፡ ሙሴም "እነሆኝ" አለ፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን "ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ሥፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ" አለው፡፡ ሙሴም የእግሩን ጫማ አወጣ፡፡ የልቡንም ቂም ተወ፡፡ የአእምሮውንም ከንቱ ትምህርት (የከላዳውያን ጥንቆላ) ናቀ፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን "እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃምም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ" አለው፡፡ ሙሴም ፈርቶ ስለነበረ

ፊቱን ሸፈነ፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን "በግብጽ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፤ ጩኸታቸውንም ሰማሁ፤ ከግብጻውያን እጅ አድናቸው ዘንድ ወተትና ማር ወደምታፈሰው አገር ወደ ከነዓን አወጣቸው ዘንድ ወደድሁ፤ አሁንም ና ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ" አለው፡፡

ሙሴ "ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማን ነኝ?" አለ፡፡ እግዚአብሔርም "እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" አለው፡፡ ሙሴ "የላከህ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ?" አለ፡፡ እግዚአብሔርም "ያለና የሚኖር የአባቶቻችሁ አምላክ ላከኝ" በላቸው አለው፡፡ እግዚአብሔር ኃይሉን በሙሴ ላይ አበዛ ተአምራት የማድረግ ሥልጣንንም ሰጠው፤ ሙሴም ሕዝቡን ነጻ ሊያወጣ ወደ ግብጽ ሄደ፡፡ ዐሥር ተአምራትን በግብጻውያን ፊት አደረገ፡፡ እግዚአብሔርም የግብጻውያንን የበኩር ልጆች በሞት ቀጣ፡፡ ፈርዖንም በባርነት ያስጨነቀውን ሕዝብ ለቀቀ፡፡ ሙሴ ወገኖቹን ነጻ አውጥቶ መራ፤ እግዚአብሔር የሰጠውን የከበረ ራእይ አከበረ፡፡ ጠሪውን እግዚአብሔርን በማወቅና ትእዛዙን በማክበር ዓላማውን ፈጸመለት፤ አምላኩንም አገልግሎ አንቀላፋ፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር ለታላላቅ ዓላማዎች እንደሚጠራ አወቃችሁ? እግዚአብሔር ሙሴን ወገኖቹን ከባርነት ነጻ እንዲያወጣቸው ጠራው፤ ሌሎች ሰዎችንም እንዲሁ ጠርቷል፡፡ እግዚአብሔር ለሰማያዊና ለዘላለማዊ ጥሪ ጠርቶናል፤ ማን እንደጠራን? እና ለምን እንደጠራን? በማወቅ ለጥሪው በጎ ምላሽ መስጠትና የተጠራንበትን ዓላማ መፈጸም ይጠበቅብናል፡፡

### ጥያቄዎች

1. ሙሴን የጠራው ማን ነው?
2. እግዚአብሔር ሙሴን ለምን ጠራው?
3. ሙሴ በግብጽ ስንት ተአምራትን አደረገ?
4. እግዚአብሔርን ሙሴ ስምህን ማን ልበላቸው ባለው ጊዜ ምን አለው?
5. ሙሴ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለምን መከራ መቀበልን ፈለገ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የለመለመ ቅጠል ያለው ዛፍ ሥዕል እንዲሠሩ ያድርግ፡፡
- ሙሴ ያየው ዛፍ ምንን እንደሚያመለክት ያስረዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የፈርዖን አለመታዘዝ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ማንም የማይቋቋመው ኃያል አምላክ እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እንዲያገለግሉኝ ሕዝቤን ልቀቅ" ዘጸአት. ፱÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸአት. ፯-፲ እና ሮሜ. ፱÷፲፬-፲፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሙሴን ወደ ግብጽ የላከው ማን ነው?
- እስራኤላውያን እንዴት በግብጻውያን አገዛዝ ሥር ሊወድቁ ቻሉ?
- እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት ነጻ አወጣ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ለሙሴ ፈርዖንን "ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" በለው አለው፡፡ ሙሴ ወደ ግብጽ መጣ፡፡ በፈርዖንም ፊት በግርማ ቆመ፡፡ ሙሴም "እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል" አለው፡ ፈርዖን ግን እምቢ አለ፡፡ "እግዚአብሔር ማን ነው? ሕዝቡንም አለቅም" በማለት ልቡ ደነደነ፡፡ ስለዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ዐሥር ተአምራትን አደረገ፡፡

1. የግብጽን ውኃ ሁሉ ወደ ደም ቀየረ፡፡
2. በጓጉንቸሮች (በዕንቁራሪቶች) መንጋ ግብጽን መታ፡፡
3. በሰውና በእንስሳቱ ላይ ቅማል ሆነ፡፡
4. በዝንቦች መንጋ ፈርዖን፣ ባሪያዎቹንና ግብጻውያንን አስጨነቀ፡፡
5. የግብጽን እንስሳት ሁሉ በረኃብ ገደለ፡፡
6. በሰውና በእንስሳቱ የሚያሰቃይ ቁስል አወጣ፡፡
7. የቁጣ ዝናብ የሚጎዳ በረዶ በግብጽ ላይ አዘነበ፡፡
8. በአንበጣ መንጋ የእርሻቸውን እህል ሁሉ አስበላ፡፡
9. ግብጽን የሚያስጨንቅ ጨለማ ለሦስት ቀናት ሆነ፡፡
10. የግብጻውያንና የእንስሳቶቻቸውን የበኩር ልጆች በሞት ቀጣ፡፡

www.zeorthodox.org

የፈርዖን አሽከሮች ወደ ሙሴ መጡ፤ እግዚአብሔር ቅጣቱን ካቆመ ፈርዖን እስራኤላውያንን እንደሚለቅ ነገሩት፡፡

እግዚአብሔር በብዙ ተአምራት ኃይሉን ገለጸ፡፡ ፈርዖንም የደነደነው ልቡ በሞት ፍርሃት ተይዞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለቀቀ፡፡ እስራኤላውያን በአምላካቸው የጸናች ክንድ እየተደገፉ ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጥተው ወደ ከነዓን ጉዞ ጀመሩ፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በኃይሉ የመከራን ቀንበር እየሰበረ ሕዝቡን ከክፉዎች በትር ያድናል፡፡ ልጆች እግዚአብሔርን በመተማመን መውጣትና መግባት እንችላለን፡፡ እርሱ እንደ ዓይኑ ብሌን ይጠነቀቅልናል፡፡ በቃል ኪዳኑ አጥር በምሕረቱ ጥላ በጥበቃው ክልል ያኖረናል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር በግብጽ ስንት ተአምራትን አደረገ?
2. ፈርዖን ሕዝቡን የለቀቀው በስንተኛው ተአምር ነው?
3. የፈርዖን ልብ ለምን ደነደነ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ተአምራቱን እንዲያስታውሱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ፋሲካ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ለሚያምኑት የሚያደርገውን ጥበቃና የፍቅር እንክብካቤ ለልጆች ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አጥፊው የበኩሮችን ልጆች እንዳይነካ ፋሲካንና ደም መርጨትን በእምነት አደረገ፡፡" ዕብ. ፲፩÷፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸአት. ፲፩÷፩-፲፪÷፴፮ እና ፩ቆሮ. ፭÷፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የፋሲካ በዓልን ስታከብሩ ምን ታደርጋላችሁ?
- እስራኤላውያን እንዴት ከግብጽ እንደወጡ ታስታውሳላችሁ?
- ፋሲካንና ደም መርጨትን በእምነት ያደረገው ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር በዐመፀኞች መንደር የቁጣ ጅራፉን ዘረጋ፡፡ በደነደነው የፈርዖን ልብ የመከራ ትኩሳት ጨመረበት፤ ከዕለት ወደ ዕለት የጸናች ክንዱ በግብጻውያን ላይ ኃይልን አደረገች፡፡ ዘጠኝ ተአምራትን እንኳ አድርጎ ፈርዖን ሕዝቡን ሊለቅ ስላልቻለ ዐሥረኛውን ተአምር ሞተ በኩርን ማድረግ ፈለገ፡፡

በፈርዖን አሽከሮችና በሕዝቡ ፊት እጅግ የከበረው ሙሴ እግዚአብሔር ሊያደረግ የፈለገውን ለሕዝቡ ነገረ፡፡ እንዲህም አላቸው፡- "በእኩለ ሌሊት እግዚአብሔር በግብጽ መካከል ያልፋል፤ በዙፋን ከተቀመጠው ከፈርዖን ልጅ ጀምሮ የበኩር ልጆችን ሁሉ በሞት ይቀጣል፤ የእንስሳት በኩርም ሳይቀር በሞት ይመታል" አላቸው፡፡

www.zoorthodox.org

እስራኤላውያን ፈሩ ግብጻውያን ተሸበሩ፡፡ እግዚአብሔር ግን የእስራኤላውያንን የበኩር ልጆች ከሞት የሚተርፉበትን ሥርዓት ሠራ፤ ለሙሴም ነገረው፡፡ ሙሴም ሕዝቡን (እስራኤላውያንን) "ነውር የሌለበት የበግ ጠቦት ለእያንዳንዳችሁ አዘጋጁ ሲመሽ እረዱት፤ በበጉም ደም የቤታችሁን ጉበንና መቃን ቀቡት፡፡ ሥጋውንም ከመራራ ቅጠል ጋር ብሉት፡፡ ወገባችሁን ታጥቃችሁ ጫማችሁን በእግራችሁ በትራችሁንም በእጃችሁ አድርጋችሁ የበጉን ሥጋ ብሉ፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው፡፡ እግዚአብሔር ግብጽን ሊመታ የበኩር ልጆቿንም በሞት ሊቀጣ ሲመጣ የፋሲካውን በግ ደም አይቶ ከእናንተ ያልፋል፡፡ ልጆቻችሁን ሞት

አይነካም፡፡ ይህ ለዘላለም ሥርዓት ይሁን" አላቸው፡፡ ሕዝቡም ሙሴ እንደነገራቸው አደረጉ፡፡ ፋሲካን በደስታ አከበሩ፡፡ ሞት የደሙን ምልክት አይቶ አለፋቸው፡፡ ይህ ለዘላለም እግዚአብሔርን በሚያምኑ ዘንድ ሥርዓት ሆነ፡፡

ፋሲካ ማለት "ፓሳህ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሲሆን "ማለፍ መሻገር" ማለት ነው፡፡ እስራኤላውያን ከሞት የዳኑበትን ሥርዓት ያስታውሰናል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን የአይሁድን ፋሲካ በክርስቶስ ፋሲካ ተክታ ታከብራለች፡፡ እስራኤላውያን ከሞት የዳኑበት በግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ንጹሑ የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሁላችን ታርዶ ከሞት ድነናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአል" በማለት እንደ ሙሴ ፋሲካን በእምነት እንድናደርግ መክሯል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ሕዝቡን በፋሲካው ደም ምልክት ከሞት አድኗል፡፡ እንደ ዓይኑ ብሌን ተጠንቅቆ ጠብቋል፡፡ ማንም በማያልፍበት ምድረ በዳ በረድኤቱ ጠል አሳልፏል፡፡ ፋሲካችን ክርስቶስም በደሙ ቀድሶ ሕይወትን ሰጥቶናል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን የበኩር ልጆች እንዴት ከሞት አዳናቸው?
2. ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ፋሲካችን ማን ነው?
4. ቤተ ክርስቲያን የፋሲካን በዓል እንዴት ታከብረዋለች?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የፋሲካውን በግ በሥዕል እንዲሠሩ ያድርግ፡፡
- ከልጆች መካከል አንዱ የተማረውን አስታውሶ ለጓደኞቹ እንዲነግር ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቀይ ባሕርን መሻገር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ ልጆች እንዲገነዘቡ ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አትፍሩ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ" ዘጸ. ፲፬÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸ. ፲፬፣ መዝ. ፻፮÷፯-፵፰፣ ሐዋ. ፯÷፴፮-፵ እና ዕብ. ፲፩÷፳፱

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ባሕር አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- ባሕርን እንዴት መሻገር ይቻላል?
- የኤርትራን ባሕር የከፈለው ለማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ኃይል በሙሴም መሪነት ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን ጉዞ ጀመሩ፡፡ የኤርትራ ባሕር ጉዟቸውን ስለገታው በባሕሩ ዳርቻ ሰፈሩ፡፡ ፈርዖን በሕዝቡ ነጻ መውጣት ተቆጥቶ በፈረስና በሠረገላ ሠራዊቱን ላከ፡፡ የፈርዖን ወታደሮች እስራኤላውያንን በማሳደድ ተከተሏቸው፡፡ በኤርትራ ባሕር አጠገብ ሰፍረው አዩዋቸው፡፡ የእስራኤል ልጆችም ግብጻውያንንና ስድስት መቶ ሰረገላዎቻቸውን ፈረሶቻቸውንም ባዩ ጊዜ ደነገጡ፤ ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ፡፡ ሙሴንም "በግብጽ መቃብር ስላልኖረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን? በምድረ በዳ ከምንሞት ብንገዛላቸው ይሻል ነበር" አሉት፡፡

ሙሴ ለሕዝቡ "አትፍሩ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብጻውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፤ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ፡፡ እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ፡፡" አላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር መልአኩን ላከ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ፡፡ የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ቆመ፡፡ በግብጻውያን ሰፈርና በእስራኤል ሰፈር መካከል ገባ፤ በዚያም ደመናና ጨለማ ነበረ፡፡ በእስራኤል በኩል ግን ሌሊቱን አበራ፡፡ የግብጽ ሠራዊት የእስራኤልን ልጆች አልነኩም፡፡ ሙሴ በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ፡፡

እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው፡፡ ባሕሩንም አደረቀው ውኃውም ለሁለት ተከፈለ፡፡ የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ፤ ውኃው በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው፡፡ የግብጽ ሠራዊት ከነሰረገላዎቻቸው ከፈረሶቻቸውም ጋር ወደ ባሕሩ ገቡ፡፡

ንጋትም በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በእሳትና በደመና ዓምድ ሆኖ የግብጽን ሠራዊት ተመለከተ፡፡ የሰረገሎቹንም መንኮራኩር ሰባበረ፡፡ ግብጻውያንም፡- "እግዚአብሔር ይዋጋላቸዋልና ከእስራኤል ፊት እንሽሽ" አሉ፡፡

እግዚአብሔር ሙሴን፡- "እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ ውኃውንም በግብጻውያን ሠራዊት ላይ ይመለስ" አለ፡፡ ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤ ባሕሩም ወደ መፍሰሱ ተመለሰ፤ የፈርዖንም ሠራዊት ሰጠሙ፡፡ እስራኤላውያን የግብጻውያንን ሬሳ በባሕሩ ዳር ሆነው አዩ፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በኃይሉ ሕዝቡን ባሕር ከፍሎ አሻገረ፡፡ የነጻነትን አክሊል አቀዳጅቶ ከጠላት በትር አድኖ ወደ ዕረፍት መራቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር የሚሳነው (የማይችለው) ነገር የለም፡፡ ባሕርን ያለመርከብ ያሻግራል፤ በረሐውን እንደ ገነት አድርጎ ይመራል፡፡ በእሳት ውስጥ ሳይቃጠሉ ያኖራል፡፡ በእሳትና በውኃ መካከል በሕይወት ያሳልፋል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ፈርዖን እስራኤላውያንን ከለቀቀ በኋላ እንደገና የተከተላቸው ለምንድን ነው?
2. እስራኤላውያን በፈሩ ጊዜ ሙሴ ምን አላቸው?
3. ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?
4. ሙሴ ባሕሩን እንዲከፍል እግዚአብሔር ምን አዘዘው?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ታሪኩን ደግሞ እንዲተርክ ያድርግ
- በቪዲዮ ምሥል ታግዞ ባሕሩ እንዴት እንደተከፈለ ያሳያቸው፡፡
- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነቱን የገለጸባቸው ተመሳሳይ ታሪኮችን ያስታውሳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# እግዚአብሔር ሕዝቡን በደመና እና በብርሃን መራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ልጆቹን እየጠበቀ በመልካም መንገድ እንደሚመራ ጉዞአቸውን የተቃና እንደሚያደረግላቸው ልጆች/ተማሪዎች/ እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ዮሐ. ፰፥፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸ. ፲፫፣ ዘኍ. ፱፥፲፭-፳፫ እና ኤር. ፪፥፮-፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እስራኤልን የሚጠብቅ የሚመራ ማን ነው?
- ያለፈውን ሳምንት ትምህርት በቃል የሚጠና ጥቅስ ታስታውሳላችሁ?
- እግዚአብሔር እስራኤልን ለመጠበቅ ለምን ፈለገ?
- ስለ እስራኤላውያን የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤላውያን በግብጽ ሃገር በባርነት ለአራት መቶ ሠላሳ ዘመናት ኖሩ፡፡ ጩኸታቸውን ለቅሶአቸውን የሰማው የአባቶቻቸው አምላክ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን በማሰብ በኃያል ክንዱ ነጻ አደረጋቸው፡፡ ባሕር ከፍሎ ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ በመንገዳቸው መልአኩን አስቀድሞ እየጠበቃቸው፤ ከፀሐይ ሐሩር በደመና ጋርዶ፤ የሌሊቱን ጨለማ በእሳት ዓምድ እየገፈፈ በብርሃን መራቸው፡፡ የደመናው ዓምድ በቀን፤ የእሳቱ ዓምድ በሌሊት ከሕዝቡ ፊት ከቶ ፈቀቅ አላለም፡፡ በእስራኤላውያን ፊት ደመናው ቀድሞ ሲቆም ደመናው በቆመበት ቦታ እስራኤላውያን ይሰፍሩ ነበር፡፡ የደመናውን መነሣት እየጠበቁ ይጓዙ ነበር፡፡ በደመናው ክልል ውስጥ መቀመጣቸው ከዲያብሎስ አገዛዝ ነጻ ወጥተው በእግዚአብሔር የምሕረት ጥላ ማረፋቸውን ያሳያል፡፡ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጓዛሉ፤ ይሰፍራሉ፤ ሕጉንም ይጠብቃሉ፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር የሕዝቡ ዕድል ፈንታ ነበር፤ እንደ ዓይኑ ብሌን ተጠንቅቆ ሕዝበ እስራኤልን በሚገባ እየጠበቀ፤ በረሐውን ገነት አድርጎ፤ ከሰማይ መና እያወረደ ከጭንጫ ውኃ እያፈለቀ መራቸው፡፡ እስራኤላውያን ስንቅ አልያዙም፤ እግዚአብሔር ግን በየቀኑ ማለዳ ስድስት መቶ ሺሕ ሕዝብ የሚያጠግብ ትኩስ መና ከሰማይ ያወርድላቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ልጆቹን በረድኤቱ ጠል አረሰረሳቸው፤ ከግብጽ ባርነት አውጥቶ በሐሩር በረሐ ጠብቆ እየመራ ወስዶ አዲሲቱን የርስት ሃገር አወረሳቸው፡፡ ዘዳግም. ፴፪፥፱-፲፪፡፡

## ማጠቃለያ

እስራኤልን የመራ ሌላ አምላክ የለም፡፡ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሞት ጥላ ምድር ማንም በማያልፍበት በር አሳልፎ፤ ኮረብቶቿ በአረንጓዴ መስክ ያጌጡትን፤ ዳሮዎቿም በወይን ዘለላ የተሞሉትን ከነዓንን አወረሳቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ያመነችውን ነፍስ በመንገዱ ቀድሞ ያሳካላታል፡፡ በብርሃኑ የመንገዷን ጨለማ ያርቃል፡ በኃይሉ የጠላቷን ወጥመድ ይሰብራል፡፡ በግዛቱ አሳርፎ ክፉ ሳያስነካ ወዳሰበላት ስፍራ ይመራታል፡፡

### ጥያቄዎች

1. እስራኤላውያን በግብጽ ስንት ዓመታት ኖሩ?
2. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዴት መራቸው?
3. ከታሪኩ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- መምህሩ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ልጆች በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሙሴ ዐሠርቱ ቃላትን ተቀበለ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የእግዚአብሔርን የቃልኪዳን ሕጎች በጸጋው ተደግፈው እንዲጠብቁ ማስተማር

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ዮሐ. ፲፬÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸ. ፲፱÷፳፤፳÷፲፯፤ ዘዳግም. ፭÷፮-፴፫ እና ማቴ. ፭÷፲፯-፵፰

## መግቢያ

- *መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡*
- *ልጆች እግዚአብሔር ሕግጋትን ለምን እንደሰጠን ታውቃላችሁ?*
- *ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕግ የተቀበለው የት ነው?*
- *ሙሴ የማን ነፃ አውጭ መሪ ነው?*
- *ልጆች እናትና አባታችሁን ታከብራላችሁ? እናትና አባትን ማክበር ከዐሥሩ ሕግጋት አንዱ መሆኑንስ ታውቃላችሁ?*

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጥተው የበረሓውን ጉዞ ጀመሩ፡፡ በእግዚአብሔር ተራራ በሲና ግርጌ በሰፈሩ ጊዜ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ወደ ሲና ተራራ ወጣ፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ መናገር ጀመረ "ለያዕቆብ ቤት እንዲህ በል፤ በግብጻውያን ያደረግሁትን በንስርም ክንፍ እንደተሸከምኋችሁ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አስተውላችኋል? አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የመረጠ ርስት ትሆናላችሁ?" አለው፡፡ ሙሴም ወደሕዝቡ መጣ፡፡ የሕዝቡን ሽማግሌዎች ጠርቶ እግዚአብሔር ያዘዘውን ይህን ቃል ሁሉ በፊታቸው ተናገረ፡፡ ሕዝቡ ሁሉ አንድ ላይ ሆነው "እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፡፡" ብለው መለሱ፡፡ ሙሴም የሕዝቡን ቃል ወደ እግዚአብሔር አደረሰ፡፡ ሕዝቡም ልብሳቸውን አጠቡ ራሳቸውን አዘጋጁ፡፡

www.zeorthodox.org

***እግዚአብሔር ሕግጋቱን (ዐሥርቱን ቃላተ ኦሪት) ለሙሴ መንገር ጀመረ፡-***

1. "ግብጽ ምድር ከባርነትም ቤት ያወጣውህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፡፡
2. የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፡፡
3. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡
4. አባትና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፡፡

5. አትግደል፡፡
6. አታመንዝር፡፡
7. አትስረቅ፡፡
8. በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፡፡
9. የባልንጀራህ የሆነውን ሁሉ አትመኝ፡፡
10. ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ፡፡” አለው፡፡

ሙሴም ዐሥሩን ቃላት ተቀብሎ ወደ ሕዝቡ ተመለሰ፡፡ ሕዝቡም ሁሉ ነጎድጓዱንና መብረቁን የቀንደ መለከቱን ድምፅ ተራራውም ሲጨስ አዩ፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ሕገ ኦሪትን (ዐሥሩን ቃላት) ለሙሴ ሰጠ፡፡ ሙሴም ተቀብሎ ለሕዝቡ ነገረ፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የመለየት ሥርዓትን የሚያጸና ሕግ ሰጥቷል፡፡ ልጆች እርሱን መውደዳችንን በሥራ ለመግለጽ በጸጋው እየተደገፍን ትእዛዛቱን ልንፈጽም ይገባል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ሙሴ የተቀበላቸው ሕገ ኦሪት /ቃላት/ ስንት ናቸው?
2. ሙሴ ሕገ ኦሪትን የተቀበለው የት ነው?
3. እግዚአብሔር ዐሥሩን ቃላት ለሙሴ ከመስጠቱ በፊት ምን አደረገ?
4. እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለሚፈጽሙ ምን ያደርግላቸዋል?
5. ከዐሥሩ ቃላት ለልጆች የተላለፈው ትእዛዝ ምንድን ነው?
6. ልጆች አባትና እናታቸውን በማክበር ምን ያገኛሉ?

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ ልጆች ዐሥሩን ቃላት ጽፈው ሁል ጊዜ በሚያስታውሱበት ቦታ ላይ እንዲያስቀምጡና እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡

# የእስራኤል ማጉረምረም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የኃጢአት ፍጻሜው መራራ ሞት እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል፡፡"
ዘጸ. ፳፩÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘኁልቁ. ፳፩፣ መዝ. ፸፰÷፯-፳፯ እና ዕብ. ፫ እና ፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እባብ ትፈራላችሁ?
- እግዚአብሔር ሕዝቡን ለምን ይቀጣል?
- ስለ ኃጢአት ያላችሁን እውቀት ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ?
- ኃጢአት ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እስራኤላውያን እግዚአብሔር መንገዳቸውን እያቀናላቸው በግብጽ በረሐ ሲጓዙ በሙሴ ላይ ተቆጡ፤ በእግዚአብሔርም ላይ አጉረመረሙ፡፡ "በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብጽ ለምን አወጣኸን? እንጀራ የለም፤ ውኃ የለም፡፡ ሰውነታችን ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ" አሉ፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ፤ ሕዝቡንም ነደፉ፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ስጦታውን ሲያቃልሉበት ይቆጣል፡፡ የቁጣውን ጅራፍ በአመፀኞች ላይ ይዘረጋል፡፡ ውለታውን ለሚረሳ የልብ ስቃይ ይልክበታል፡፡

እስራኤላውያን ያዳናቸውን ፈጥነው ረሱ፡፡ በምድረ በዳ ክፉ ምኞትን ተመኙ፡፡ ከሰማይ የሚወርድላቸውን መና ሰለቹ፡፡ በእግዚአብሔር እጅ መመገብን ጠሉ፡፡ የግብጽን ሽንኩርት ናፈቁ፡፡ በማጉረምረማቸው እግዚአብሔርን አስመረሩት፡፡ ባለማመናቸው ጠንቅ እባብ ነድፎ ገደላቸው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ከማንም ጋር መዛመድ አይችሉም፤ ሰውም እንስሳቱም ጠላት ሆነው ይነሡባቸዋል፡፡

www.zeorthodox.org

እስራኤላውያን ወደ ሙሴ መጥተው "በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ስለ ተናገርን በድለናል፡፡ እባክህ እባቦችን ከእኛ ያርቅልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን" አሉት፡፡ ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም መመለሳቸውን ወደደ፤ ሙሴንም "እባቡን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል" አለው፡፡

ሙሴ የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ፤ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ፡፡

ልጆች የናሱ እባብ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ነው፡፡ "ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ

የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል” በማለት ራሱ ክርስቶስ ተናግሯል፡፡ ዮሐ. ፫÷፲፬፡፡ **እስራኤላውያን የናሱን እባብ አይተው ከሞት** እንደዳኑ ሁሉ እኛም በመስቀሉ የተሰቀለውን ክርስቶስን አይተን ከሞት ድነናል፡፡

## ማጠቃለያ

እስራኤላውያን ፈጥነው የአምላካቸውን ሥራ ረሱ፤ ክፉ በመመኘት በደሉ፡፡ ኃጢአታቸው መራራ ሞትን አመጣባቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል፡፡ ከኃጢአት ጋር ተስማምተው የሚኖሩቱንም ይቀጣል፡፡ ስለዚህ በፊቱ በቅድስና ሥርዓት እንመላለስ፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የቀጣቸው ለምንድን ነው?
2. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምን ቀጣቸው?
3. ሕዝቡ ከሞት እንዲድኑ ሙሴ ምን አደረገ?
4. የናሱ እባብ የማን ምሳሌ ነው?
5. የእስራኤል ኃጢአት ምንድን ነበር?

## ተግባር

- *መምህሩ ልጆች ስለ እባብ የሚያወሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዲያጠኑ መረጃ ይስጣቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

# የቃል ኪዳኑ ታቦት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የቃልኪዳኑን ታቦት ታሪክና ጥቅም እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ባለው በሁለቱ ኪሩቤል መካከል አነጋግርሃለሁ" ዘጸ. ፳፭÷፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፬-፯፣ ኢያሱ. ፫÷፬ እና ራዕ. ፲፩÷፲፱

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡
- ልጆች የቃል ኪዳኑ ታቦት ለምን ለእስራኤላውያን ተሰጠ?
- በጥምቀት ዋዜማ ታቦታቱ ከመንበራቸው ተነሥተው ከተማውን ሊባርኩ ወደ አፍላጋት ሲወርዱ ተከትላችሁ አክብራችሁ ታውቃላችሁ?
- ስለ ቃልኪዳኑ ታቦት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ቃልኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የቃልኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር ለእስራኤል ለሰጠው ቃልኪዳን የሚታይ ምልክት ነው፡፡ ታቦቱ በወርቅ የተለበጠ፤ መክደኛው ከወርቅ የተሠራ ነበር፡፡ በላዩም ሁለት ኪሩቤል ተቀርፀዋል፡፡ እግዚአብሔር ለማይለወጠው ኪዳኑ የቃል ኪዳኑን ታቦት ምልክት አድርጎ ሰጥቷል፤ ይህም የቃልኪዳኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

የቃልኪዳኑ ታቦት ዐሥርቱ ቃላት የተጻፈባቸው የሁለቱ ጽላት ማደሪያ በመሆን ያገለግል ነበር፡፡ ከእስራኤል መሪዎች ጋር የእግዚአብሔር መገናኛም ነበረ፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ነበር፡፡ ዘጸ. ፳፭÷፩-፳፪፡፡

www.zeorthodox.org

የቃልኪዳኑን ታቦት እስራኤላውያን በሄዱበት ቦታ ሁሉ ይዘውት ይጓዙ ነበር፡፡ ዮርዳኖስን ሲሻገሩና ኢያሪኮን ሲዞሩ ካህናት ተሸክመውት ፊት ፊት ይሄዱ ነበር፡፡ እስራኤላውያን ታቦቱን ይዘው በተዋጉባቸው ጦርነቶች አሸናፊዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከኃጢአታቸው ሳይመለሱ ከተዋጉ ይሸነፉ ነበር፡፡ በመሳፍንቱ ዘመን በጦርነት እንደ መከላከያ ሲጠቀሙት በፍልስጥኤማውያን ታቦቱ ተማርኳል፡፡ የቃልኪዳኑ ታቦት ዳጎንን ሰብሮ የጠላቶችን መንደር አስጨንቆ በድል ተመልሷል፡፡

በዚህ በኩል ታቦት የእመቤታችን የማርያም፤ ጽላት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት የጽላት ማደሪያ እንደሆነ ሁሉ ድንግል ማርያምም የጌታ ማደሪያ ሆናለችና፡፡

## ማጠቃለያ

የቃል ኪዳኑ ታቦት ለማይታየው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚታይ ምልክትና የቃል ኪዳኑ ማኅተም ነው፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር ከእስራኤል መሪዎች ጋር የሚገናኝበት የግንኙነት ማዕከል ነበር፡፡ እስራኤላውያን በሄዱበት ቦታ ሁሉ ይዘውት ይጓዙ ነበር፤ ስመ አምላክ አለበትና በመንገዳቸውም ድል ያመጣላቸው ነበር፡፡ ይህም ታቦት በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. የቃል ኪዳኑ ታቦት ጥቅም ምንድን ነበር?
2. እስራኤላውያን በሄዱበት ሁሉ የቃልኪዳኑን ታቦት ይዘው የሚጓዙት ለምንድን ነው?
3. የቃልኪዳኑ ታቦት በፍልስጥኤማውያን የተማረከው በማን ዘመን ነበረ?
4. የቃልኪዳኑ ታቦት የማን ምሳሌ ነው?
5. ጽላት በማን ይመሰላል?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆቹ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡
- ልጆች የሚያውቁትን የታቦት መዝሙር ያዘምራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የአዳም ከገነት መባረር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ሰውን የሚወድ አምላክ እንደሆነና ንጹሕ ባሕሪው ኃጢአትን እንደሚጸየፍ ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው" ዘፍ. ፫፥፳፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፫፥፳፪-፳፬፣ ሮሜ. ፭፥፲፪-፲፬ እና ማቴ. ፬፥፩-፲

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች አዳም መቼ እንደተፈጠረ ታስታውሳላችሁ?
- አዳም ከገነት ለምን ተባረረ?
- እግዚአብሔር እንዴት ሰውን ወደደ?
- እግዚአብሔር ለምን ኃጢአትን ይጠላል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በአርአያውና በአምሳሉ ፈጥሮ በኤደን ገነት አስቀመጣቸው፡፡ ለማየት ደስ የሚለውንና ለመብላት መልካም የሆነውን ዛፍ እንዲበሉ ፈቀደላቸው፡፡ "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" በማለት ዕፀ በለስን እንዳይበሉ ከለከላቸው፡፡

አዳምና ሔዋን የተፈጠሩበትን ዓላማ አክብረው በንጽሕና በመመላለስ መኖር ጀመሩ፡፡ እግዚአብሔርም ለቃሉ በመታመናቸው ደስ አለው፤ መላእክቱንም ወደ እነርሱ ይልክ ነበር፡፡ ቅዱሳን መላእክትም አዳምና ሔዋንን ያጫውቷቸው ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የወንድሞች ከሳሽ የሆነው ዲያብሎስ በእባብ ላይ አድሮ ሔዋንን ክፉ ምክር መከራት፡፡ "ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ፡፡ መልካምንና ክፉውን እንደ እግዚአብሔር ታውቃላችሁ፡፡ የሰማይና የምድር አምላክ ትሆናላችሁ" አላት፡፡ ሔዋንም ዛፉን አይታ ጎመጀች፤ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አይታ ከፍሬው ቆርጣ በላች አዳምም ከእርስዋ ጋር በላ፡፡

www.zeorthodox.org

የአዳምና የሔዋን ዓይኖች ተከፈቱ፡፡ ራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ፡፡ ከበለስ ቅጠል ሰፍተው ግልድም አደረጉ፡፡ ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምፅ በገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰምተው በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ፡፡ እግዚአብሔር አዳምን "ወዴት ነህ?"

እያለ ጠራው፡፡ አዳምም "በገነት ድምፅህን ሰማሁ ራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ ተሸሸግሁም" አለው፡፡ አዳም በመንፈሱ በመሞቱና ከሕያዋን መንደር በመለየቱ እግዚአብሔር አዘነለት፡፡ በዘመን ፍጻሜ ሞቱን በሞት በመሻር እንደሚያድነው ተስፋ ሰጠው፡፡ ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው አለበሳቸውም፡፡ ከገነት አባረራቸው፡፡ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ በኪሩቤል አስጠበቀው፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ሰውን ሁሉ ይወዳል፡፡ ነገር ግን እውነተኛ ፈራጅ ስለሆነ የሚጠላውን ኃጢአት የሚያደርጉትን በመጠን ይቀጣል፡፡ አዳምና ሔዋን የፍቅሩን ሕግ ችላ ብለው የጠላትን ምክር በመስማታቸው ኃጢአት ሠሩ፤ በኃጢአታቸው ምክንያት ሞት በሰው ታሪክ ተቆራኘ፡፡ አዳምና ሔዋን በኃጢአታቸው ኃፍረታቸው ሲገለጥ ጊዜያዊ ልብስ ቅጠል ሲለብሱ እግዚአብሔር ግን የሚሞቅ ዘላቂ የቆዳ ልብስ አለበሳቸው፡፡ ረጅሙን መንገዳቸውን እርሱን በሚጠብቅ ተስፋ እንዲጓዙት አደረገ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በየት አስቀመጣቸው?
2. ልጆች የማንን ቃል ትሰማላችሁ? የእግዚአብሔርን ወይስ የሰይጣንን?
3. እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ያለበሳቸው ምንድን ነው?
4. ሔዋን የተከለከለችውን የዛፍ ፍሬ ለምን በላች?
5. ሰውን እጅግ አድርጎ የሚወደው እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለምን ፈረደባቸው?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ታሪኩን ደግሞ እንዲናገርና ከታሪኩ የተማረውን እንዲያካፍል ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የክርስቶስ በበረት መወለድ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረን አምላክ ሥጋችንን ተዋሕዶ ለመልካም ሥራ ዳግም ሊፈጥረንና ሊያከብረን እንደተገለጠ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ክርስቶስ ተወልዶላችኋል" ሉቃ.፪÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፩÷፲፰-፳፬፣ ሉቃ.፪÷፩-፳ እና ኢሳ.፱÷፮-፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ተወለደ?
- ልጆች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደታት ስንት ናቸው?
- ፈጣሪዋን የወለደችው ድንግል ማን ናት?
- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ተወለደ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አዳም ከገነት ሲባረር ተስፋ በልቡ ተጽፎለት ነው፡፡ "ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ" የሚለውን አምላካዊ የተስፋ ኪዳን ወደ ሲኦል የወረዱ አባቶች ሁሉ ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ የመከራውና የኩነኔው ዘመን ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ዓለምን የሚያረጋጋ የምሥራች ድምፅ ይዞ ወደ ድንግል ማርያም መጣ፡፡ ድንግል ማርያምም የምሥራቹን ቃል "እንደቃልህ ይሁንልኝ" በማለት በእምነት ተቀበለች፡፡ አካላዊ ቃል በእርሷ ማኅፀን ተቀረፀ፡፡

ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሳር ትእዛዝ በወጣ ጊዜ ዮሴፍ አረጋዊ እመቤታችን ማርያምን ይዞ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ቤተልሔም ሊቆጠር ወጣ፡፡ በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ የበኩር ልጇን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ወለደች፡፡ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ ለእንግዶች ማደሪያ ስፍራ ስላልነበረ በግርግም አስተኛችው፡፡ ልጆች ዓለምን ፈጥሮ ለሰው መኖሪያ የሰጠው አምላክ በዓለም ራሱን የሚያስጠጋበት ማደሪያ አጣ፡፡ ለዓይን በማያምር ለሰው ማደሪያ በማይሆን በከብቶች በረት ተወለደ፡፡ ክርስትና የተጀመረው በቤተልሔም ዋሻ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ክርስቶስ ሁሉን የፈጠረ፤ ሁሉን የሚገዛ፤ ሁሉን ያደረገ አምላክ ሲሆን የፈጠረውን ሥጋ ሊያከብረው ተዋሐደው፡፡ የማይሞተው አምላክ የሚሞተውን ሥጋ ለብሶ የሞትን ቁራኝነት አላቆ የማይሞት አደረገው፡፡ ዓለምን በመሐል እጅ የያዘው ጌታ

በበረት ሲወለድ ሰማያውያን መላእክት ከምድራውያን እረኞች ጋር በምስጋና ተባበሩ፡፡ እረኞችም እስከቤተልሔም በመሄድ የሆነውን አይተው እግዚአብሔርን አከበሩ፡፡

## ማጠቃለያ

በመከራው ዘመን ፍጻሜ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ማርያም ተገለጠ፡፡ ዓለምን የፈጠረውና የሚገዛት ወደዓለም ሲመጣ በእንግዶች ማደሪያ ስፍራ አጣ፡፡ የምስኪኖች መጠጊያ የሆነው አባት መጠጊያ አጣ፡፡ ሰማይና ምድርን የፈጠረው በከብቶች በረት ተወለደ፡፡ በመወለዱ ሰማያውያን መላእክትና ምድራውያን እረኞች በአንድነት አመሰገኑ፡፡ የክርስቶስ መወለድ ለሁሉ የሚሆን ደስታ አስገኝቷል፡፡ ዘመንን ለሁለት ከፍሎ የኩነኔውን ዘመን አሳልፎ የምሕረት ዓመት መቁጠር አስጀምሮናል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ክርስቶስ በየት ተወለደ?
2. ቤተልሔም የማን ከተማ ናት?
3. ሕዝቡ ሁሉ እንዲጻፍ ትእዛዝ ያወጣው ቄሳር ማን ነው?
4. በክርስቶስ ልደት በምስጋና የተባበሩት እነማን ናቸው?
5. በክርስቶስ ልደት ያገኘናቸውን ገጸ በረከቶች ተናገሩ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የልደት በዓልን እንዲያከብሩ፣ ክርስቶስ ሲወለድ የነበረውን ሁኔታ በቅርጻ ቅርጽና በሥዕል በማዘጋጀት እንዲለማመዱ ያድርግ፡፡
- የልደት መዝሙሮችን እንዲያጠኑና እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የክርስቶስ ጥምቀት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ክርስቶስ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም እንደ እኛ እንደተጠመቀ ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ማቴ.፫÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ.፫÷፲፫-፲፯፣ ሉቃ.፫÷፳፪ እና መዝ.፻፳÷፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ጥምቀት ምንድን ነው?
- ለምን እንጠመቃለን?
- በማን ስም እንጠመቃለን?
- ካህናት ልጆችን እንዴት ያጠምቃሉ?
- ጌታ ኢየሱስ ለምን ተጠመቀ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ የንስሐ ጥምቀት ያጠምቅ ነበር፡፡ ሕዝቡም ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ይጠመቁ ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ "እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤ እርሱ ከእኔ በኋላ ቢመጣም ከእኔ በፊት ነበረ" እያለ ስለ ክርስቶስ መሰከረ፡፡ ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡ ዮሐንስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያየው "እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጂ አንተ ወደ እኔ እንዴት ትመጣለህ?" አለው፡፡ ጌታ ኢየሱስ መጥቶ "አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና" አለው፡፡ ፈቃጁ ጌታ በፈቃዱ ዮሐንስን አስፈቅዶት ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ተጠመቀ፡፡ እኛ ደግሞ የእርሱን አርአያነት በመከተል እርሱ የፈጸመውን ጽድቅ በእምነት ለመቀበል እንጠመቃለን፡፡

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ መጥምቅ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ሰማያት ተከፈቱ፡፡ የባሕርይ አባቱ አብ በደመና ተገልጦ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" አለ፡፡ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በእርሱ ላይ መጣ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በሠላሳ ዘመኑ ተጠመቀ፡፡ በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎ በልዕልናው ያመኑትን ከፍ አደረገ፡፡ ልጆች እኛ በእርሱ የተፈጸመውን ጽድቅ በእምነት ለመቀበል በአርባ እና በሰማንያ ቀናችን እንጠመቃለን፡፡ በመጠመቃችንም የምስጢራት ሁሉ ተካፋይ እንሆናለን፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. መጥምቁ ዮሐንስ ያጠምቅ የነበረው የት ነው?
2. የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ለምን ልጅነትን አላሰጠችም?
3. ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ የመጣው ከየት ተነሥቶ ነው?
4. መጥምቁ ዮሐንስ ክርስቶስን በእኔ አትጠመቅም ብሎ ለምን ከለከለው?
5. ጌታችን ኢየሱስ በስንት ዓመቱ ተጠመቀ? ለምን?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር እንዲወያዩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መረጠ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔር ጥሪ ዘላለማዊ ክብር እንደሚያሰጥ ለልጆች በማስረዳት በሰማያዊ ጥሪ መጠራታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉን ትተው ተከተሉት" ሉቃስ. ፭÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኤር. ፩÷፭፣ ማቴ. ፬÷፲፰-፳፪፣ ሉቃስ ፭÷፩-፲፩፣ ዮሐ. ፩÷፴፱-፶ እና ፩ቆሮ. ፩÷፳፮-፳፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ስንት ናቸው?
- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እንዴት ጠራቸው?
- የደቀመዛሙርቱ የቀድሞ ሥራቸው ምንድን ነበር?
- ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት (ደቀመዛሙርት) ቀራጭ የነበረው ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በአንድ ወቅት ኢየሱስ በጌንሴሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ ነበር፡፡ በጴጥሮስ ታንኳ ተቀምጦ የመንግሥቱን ወንጌል ሰበከ፡፡ ነገሩንም ከጨረሰ በኋላ ስምዖን ጴጥሮስን "ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ" አለው፡፡ ጴጥሮስም "አቤቱ ሌሊቱን ሁሉ ስንደክም አደርን ምንም አልያዝንም ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ" አለው፡፡ ጌታም እንዳላቸው ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ከዓሣው ብዛት የተነሣ ተቀደዱ፡፡ በጓደኞቻቸውም ታንኳዎች ሞሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ስምዖን ጴጥሮስ የኢየሱስን ሁሉን ቻይነት አይቶ በጉልበቱ ሰገደ በግንባሩ ምተደፋ፡፡ "ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ" አለው፡፡ ከእርሱ ጋር የነበሩ ሁሉ የዘብዴዎስ ልጆች ዮሐንስና ያዕቆብም ተደነቁ፡፡

ኢየሱስም "ከእንግዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህና አትፍራ" አለው፡፡ ታንኳዎቻቸውንም ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት፡፡ መኖሪያውን አዩ፤ የአንደበቱን የሕይወት ቃል ሰሙ፤ የእጆቹን ተአምራት ተመለከቱ፤ የሕይወቱን ፍጹምነት ወደው ከእርሱ ጋር ኖሩ፤ የመዓዛው ሽታዎች፤ የሥራው ምስክሮች፤ የመንግሥቱ ወንጌል ሰባኪዎች ሆኑ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም በጸጋ ሾማቸው፤ ዘላለማዊ ክብርንና ዘመን ተሻጋሪ ዝናን ሰጣቸው፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች የሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች እንድትሆኑ በክርስቶስ ተጠርታችኋል፡፡ እግዚአብሔር ጠቢባንን የሚያስደንቅ ሥራ በሕፃናት ይሠራል፤ በታናናሾች ትልልቅ ራእዮቹን ይፈጽማል፡፡ እግዚአብሔር እስከተጠቀመበት ድረስ ትንሽ የሚባል ነገር የለም፡፡ ነቢዩ ኤርምያስ ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ ነበር ለነቢይነት ጸጋ የታጨው፡፡ ሕፃንነቱን ተመልክቶ “ብላቴና ነኝ እናገር ዘንድ አልችልም” ሲል ጠሪው እግዚአብሔር “ብላቴና ነኝ አትበል” አለው፡፡ ልጆች ሆይ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ክብር ለሚያጎናጽፍ ራእይ አጭቷችኋልና መጠራታችሁን ተመልከቱ፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ጌታ ኢየሱስ እነ ጴጥሮስን ያገኛቸው ማን በሚባለው የባሕር ዳር ነው?
2. ጴጥሮስ መረቡ በዓሣ ሲሞላ ምን አደረገ?
3. እግዚአብሔር ሰዎችን ለምን ዓላማ ይጠራል?
4. የኢየሱስ የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት እነ ማን ናቸው?
5. ሰውን ማጥመድ ማለት ምን ማለት ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ታሪኩን እንደገና እንዲተርክ ያድርግ፡፡
- ከጥሪው ታሪክ ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የባቢሎን ግንብ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በጽድቅ የሚፈርድ አምላክ እንደሆነ ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ" ማቴ. ፲፩÷፳፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፲፩÷፩-፱ እና ሮሜ.፩÷፲፰-፴፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ባቢሎን ማለት ምን ማለት ነው?
- ልጆች ስለ ኖህና ቤተሰቡ የምታስታውሱትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ሰው እግዚአብሔርን መቋቋም ይችላልን?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር በኖህ ዘመን የነበሩ ክፉ ሰዎችን ከምድር ካጸዳ በኋላ ምድር ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች፡፡ ሰዎች በሰናዖር ምድር አንድ ሰፊ ሜዳ አገኙ፤ በዚያም ተቀመጡ፡፡ እርስ በርሳቸው "ኑ ጡብ እንሥራ በእሳትም እንተኩሰው" ተባባሉ፡፡ ጡቡም እንደ ድንጋይ ጠንካራ ሆነላቸው፡፡ ለሕንፃ መሥሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን አሟሉ፡፡ "ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ በምድር ላይ ስማችንን እናስጠራው" አሉ፡፡ ለዝና ሲሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ሰማይ ጠቀስ ሕንፃ ገነቡ፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ፡፡ ለክብሩ የማይሆን እርሱን ለመቃወም የተሠራ እንደሆነም ባየ ጊዜ "እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፤ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህንም ለማድረግ ጀመሩ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም፡፡ ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን እንደባልቀው" አለ፡፡

እግዚአብሔር የሰውን ክፉ ምክር ያፈርሳልና በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው፡፡ እነርሱም የዐመጽ ከተማቸውን ለመሥራት አልቻሉም፡፡ የከተማዋ ስም "ባቢሎን" ተባለ፡፡ ባቢሎን ማለት "ድብልቅልቅ" ማለት ነው፤ እግዚአብሔር ቋንቋቸውን ደባልቋልና፤ ክፉ ምክራቸውን አፍርሶ በምድር ሁሉ በትኗቸዋልና፡፡

ባቢሎን የእግዚአብሔር ስሙ የማይጠራባት፤ ክብሩ የማይገለጥባት፤ አላውያን ነገሥታት የበቀሉባት፤ ለእግዚአብሔር ሕዝብ

ጠላት ሆነው የተነሡ ሰዎች የተገኙባት ከተማ ሆናለች፡፡ ባቢሎን የቅዱሳን ደም ተገኝቶበታል፤ ብዙ ደጋግ ሰዎችን ገድላለች፤ የንጹሐንን እንባ አፍስሳለች፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ደግሞ በፍርዱ ሊበቀላት ይፈልጋል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በጽድቅ የሚፈርድ በየዋህነት በትሕትና የሚመላለሱትን የሚወድ አምላክ ነው፡፡ የባቢሎን ሰዎች እግዚአብሔርን ለመቋቋም ክፉ መከሩ እርሱ ግን ምክራቸውን አፍርሶ፤ ቋንቋቸውን ደባልቆ በክፉ መስማማታቸውን ጠልቶ በምድር ሁሉ በተናቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔርን የሚታገሉ ይወድቃሉ፡፡ እርሱን በማመን በልባቸው የዋሃን በኑሯቸው ትሑታን የሆኑትን ይወዳልና እንደ ፈቃዱ በመታዘዝ እንኑር፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. በክፉ ምክር የተጓዙት ሰዎች ሕንፃ የገነቡበት ሜዳ የት ነው?
2. ባቢሎን ማለት ምን ማለት ነው?
3. እግዚአብሔር የአዳም ልጆችን ሕንፃ አይቶ ምን አለ?
4. ከታሪኩ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- መምህሩ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ልጆች በጋራ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ቄርሎስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በእምነትና በትዕግሥት የተሰፋውን ቃል የሚወርሱትን ቅዱሳንን እንዲመስሏቸው ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው" ዕብ. ፲፫÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፩÷፩-፵ እና "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ"

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- የጉባኤ ኤፌሶንን አጀንዳና ውሳኔ ታውቃላችሁ?
- ቅዱሳንን በእምነት የምንመስላቸውና የምንዘክራቸው ለምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ቄርሎስ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ግብጻዊ ሊቀጳጳስ ነው፡፡ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ (ፓትርያርክ) በመሆን አገልግሏል፡፡ ቤተክርስቲያንን ከውስጥ ጠላቶች ሴራ የታደገ የቤተክርስቲያን ጠበቃ (አፖሎጅስት) ነው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በቤተክርስቲያናችን "ማኅተመ አበው" በመባል ይታወቃል፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ የሦስተኛው ዓለም ዓቀፋዊ ጉባኤ መሪ ነበር፡፡ ንስጥሮስ የሚባል መናፍቅ የሐሰት ትምህርት አስተማረ፤ ተመክሮ ሊመለስ ፈቃደኛ ስላልነበረ ጉባኤ ኤፌሶን በ**፬፻፴፩ዓ.ም** በኤፌሶን ከተማ ተደረገ፡፡ ብዙ ሊቃውንት፤ ሊቃነ ጳጳሳትና መምህራን ከተለያዩ የክርስትናው ዓለማት ተሰበሰቡ፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስብሰባውን መራ፡፡ ንስጥሮስን ተከራክሮ ረታ፡፡ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ ከብሮ ያከበረን እውነተኛ አምላክና የዘላለም አባት ነው፡፡ እናቱም ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት (ወላዲተ አምላክ) ናት" በማለት መሰከረ፤ ጉባኤውም በዚህ ከዐለት ይልቅ በጸና እውነት ተዘጋ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ቄርሎስ በነገረ ሥጋዌ ትምህርቱ የታወቀ ሊቅ ነው፡፡ "ድንግል ፈጣሪዋን ወለደች እርሱም የፈጠረውን ሥጋ ተዋሐደ" በሚለው የምስጢረ ተዋሕዶ ትምህርቱ ይታወቃል፡፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ በእምነት የምንመስለው፤ በመልካምነቱ የምናስበው፤ የኑሮ ፍሬው የጣፈጠለት ደግ አባት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ቄርሎስ የኑሮ ፍሬው ያማረለት፤ ሥራው ዛሬም የሚናገር፤ በእምነት የምንመስለው ታላቅ አባት ነው፡፡ ልጆች በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን ቅዱሳን በእምነት እንመስላቸው፡፡

## ጥያቄዎች

1. ቅዱስ ቄርሎስ የመራው ጉባኤ የትኛውን ዓለማቀፋዊ ጉባኤ ነው?
2. ቅዱስ ቄርሎስ የሚታወስበት የምስጢረ ተዋሕዶ ትምህርት ምንድን ነው?
3. ቅዱስ ቄርሎስ ተከራክሮ የረታው መናፍቅ ማን ይባላል?
4. ቅዱስ ቄርሎስ በቤተክርስቲያናችን ማን በመባል ይታወቃል?
5. ቅዱሳንን በምን እንመስላቸዋለን?

## ተግባር

- መምህሩ ስለ ሌሎች የቤተክርስቲያን ጠበቆች እንዲያውቁ መረጃ ይስጣቸው፡፡
- ከታሪኩ ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የመበለቷ ሁለት ሳንቲም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔር ከሰጠን በመስጠት የበለጠ መቀበልን እንዲማሩ ማድረግ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳል" ፪ቆሮ. ፱÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፳፩÷፩-፬ እና ማቴ. ፯÷፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ለድሆች ሳንቲም ሰጥታችሁ ታውቃላችሁ?
- ለድሆች ቸርነትን በማድረግ የሚታወቁ ሰዎችን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ለቤተክርስቲያን ዐሥራት እንደሚሰጥ ታውቃላችሁ?
- ስለ መበለቷ መብዓ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- መብዓ ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሥጋ የተገለጠው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት በቤተ መቅደስ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለጠጎችን ዓይኑን አንሥቶ አየ፡፡ አንዲት ድሃ መበለት ግን ሁለት ዲናር ሳንቲም ከዐሥራ ሦስት የመብዓ ሳጥኖች በአንዱ ስትጨምር አየ፡፡ በደስታ እንደሰጠች ልቧን ስላየ ደስ አለው፡፡ "እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህች ድሃ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች" አላቸው፡፡ ሕዝቡ እንዴት አሉ? "እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና ይህች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች" በማለት በሕዝብ ሁሉ ፊት ተናገረላት፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች ከባዕለጠጎች ብዙ መብዓ ይልቅ በትንሹ ስጦታዋ ተባረከች፤ ባላት ነገር ሳትሰስት በደስታ ሰጥታለችና፡፡ እግዚአብሔር ከስጦታችን በፊት የሰጠንበትን ምክንያት ያያል፡፡ በምንችለው በአቅማችን መብዓ መስጠት ለድሆች መመጽወት ይገባናል፡፡ መበለቷ ባዕለጸጋ አልነበረችም ነገር ግን ያላትን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መዝገብ አስገባች፡፡ ጌታም ከባዕለጸጎቹ ብዙ ብር ይልቅ የእርሷን በደስታ የቀረበ መብዓ አየ፡፡ ለእግዚአብሔር ካለን ብቻ ሳይሆን ከጉድለታችንም ልንሰጥ ይገባል፡፡

“ስጡ ይሰጣችኋል” በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት በመስጠታችን እንቀበላለን፡፡ ለእግዚአብሔር ብለን ባደረግነው ነገር ኪሳራ አይገጥመንም፡፡ የመበለቷ ሁለት ሳንቲም ከሚሊየነሮች ብዙ ገንዘብ ይልቅ በፊቱ ሚዛን ደፍቷል፡፡ በደስታ ለክብሩ የተደረገ ነበርና፡፡

## ማጠቃለያ

መብዓ ለእግዚአብሔር ካለን እውነተኛ ፍቅር ይመነጫል፡፡ እግዚአብሔርን የመብዓችንን መብዛት ሳይሆን በደስታ ማድረጋችን ያስደስተዋል፡፡ በልባችን እንዳሰብን በደስታ ያለንን እንስጥ፡፡ ሕይወቱን ለሰጠን መባችንን አንከልክለው፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. መበለቷ ስንት ሳንቲም ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጣለች?
2. ጌታ ኢየሱስ በመበለቷ መብዓ ለምን ተደሰተ?
3. መብዓችን እግዚአብሔርን የሚያስደስት እንዲሆን እንዴት እንስጥ?
4. ከመበለቷ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ሳንቲም፣ ምግብና የጠበባቸውን ልብስ ለድሆች እንዲሰጡ፤ የወላጆቻቸውን መብዓ በሙዳየ ምጽዋት በመጨመር በደስታ መስጠትን እንዲለማመዱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# አብርሃም ለይስሐቅ ሚስት አገኘለት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር መልካም ወደሆነው እኛንም ወደሚጠቅመው ሁሉ እንደሚመራን ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር መልአኩን በፊትህ ይሰዳል ለልጄም ሚስት ታገኛለህ" ዘፍ. ፳፬÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፬÷፩-፷ እና ዕብ. ፲፩÷፳

## መግቢያ

- ➔ መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ➔ ልጆች ስለ ይስሐቅ ምን ታስታውሳላችሁ?
- ➔ አብርሃም ለልጁ ሚስት እንዲፈልግለት የላከው ማንን ነው?
- ➔ ስለ አብርሃም የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- ➔ ከዛሬው ትምህርት ምን ትጠብቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም የይስሐቅ አባት ነው፡፡ ይስሐቅ ደግሞ አብርሃም በስተርጅና ያገኘው የተስፋው ዘር መጠሪያ ነው፡፡ አብርሃም ለልጁ ቆንጆ ሚስት ሊያጋባው ፈለገ፡፡ አገልጋዩን ኢያውብርን "ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እጭለት" አለው፡፡ አገልጋዩም "ሴቲቱ ምናልባት ወደዚህ አገር መምጣት ካልፈለገች ልጅህን ልውሰደውን?" አለው፡፡ አብርሃም " ልጄን እንዳትወስድ የተስፋው ዘር መጠሪያ ነውና ምድሪቱን እሰጥሃለሁ ብሎ የማለልኝ ሕያው እግዚአብሔር መልአኩን በፊትህ ይሰድዳል ለልጄም ሚስት ታገኛለህ" አለው፡፡ ኢያውብርም በጌታው ሐሳብ ተስማምቶ ከጌታው ግመሎች መካከል ዐሥር ግመሎችን ወስዶ እቃውን ጭኖ ሄደ፡፡ ወደ ናኮር ከተማ በደረሰ ጊዜ "የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ እለምንሃለሁ መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ፡፡ በዚህ የውኃ ምንጭ አጠገብ እኔ ቆሜአለሁ የዚህችም ከተማ ሴቶች ልጆች ውኃውን ሊቀዱ ይመጣሉ፤ ውኃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብይ የምላት እርስዋን ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን" እያለ ጸሎቱን ሳይጨርስ የባቱኤል ልጅ ርብቃ እንስራዋን በጀርባዋ ተሸክማ ወጣች፡፡ ርብቃ መልከዋ እጅግ ያማረ ወንድ የማያውቃት ድንግል ነበረች፡፡ ወደ ምንጭ ወረደች፤ እንሰራዋንም ሞላች የአብርሃም አገልጋይ "ከእንስራሽ ጥቂት ውኃ ታጠጪኝ ዘንድ እለምንሻለሁ" አላት፡፡ እርሷም "ጌታዬ ሆይ ጠጣ" አለችው፤ ግመሎቹንም አጠጣችለት፡፡የአብርሃም አገልጋይ ትኩር ብሎ እያያት እግዚአብሔር መንገዱን አቅንቶለት እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማወቅ ዝም አለ፡፡ "አንቺ የማን ልጅ ነሽ?" አላት፡፡ ርብቃም "የባቱኤል" አለችው፡፡ እርሱም "በአባትሽ ቤት የምናድርበት ስፍራ ይገኛልን?" አላት፡፡ እርስዋም "አዎ" አለችው፡፡ ወደ አባቷም ቤት ወሰደችው፡፡ ቤተሰቧም በመልካም ተቀበሉት፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

የአብርሃም አገልጋይ የሆነውን ሁሉ አጫወታቸው፡፡ የርብቃ ቤተሰቦችም "ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቶአል፡፡ ክፉም በጎም ልንመልስልህ አንችልም" አሉት፡፡ ርብቃንም ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆነው ሰጡት፡፡ ቤተሰቦቿ ርብቃን "አንቺ እኅታችን እልፍ አእላፋት ሁኚ ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረስ" ብለው መርቀው ሸኙአት፡፡ የአብርሃም አገልጋይ ርብቃን ለይስሐቅ ሰጠው፤ ይስሐቅም ወደ እናቱ ድንኳን አገባት፤ ከእናቱም ሞት ተጽናና፡፡

### ጥያቄዎች

1. ርብቃ የማን ልጅ ናት?
2. የአብርሃም አገልጋይ ርብቃን እንዴት አገኛት?
3. የርብቃ ቤተሰቦች ለመልእክተኛው የነገሩት ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆቹ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲያጠኑት ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# እግርን ማጠብ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በትሕትና ሌሎችን ማገልገል እንደሚገባ ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም" ዮሐ. ፲፫÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፲፫÷፩-፳፤ ማቴ. ፲፩÷፳፱ እና ፩ቆሮ. ፲፪÷፬-፲፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በቤተክርስቲያን ኅፅበተ እግር የሚከናወነው መቼ ነው?
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር ለምን አጠበ?
- ወላጆቻችሁ እግራችሁን ሲያጥቧችሁ ምን ይሰማችኋል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሥጋ ማርያም ተገልጦ እንደ እግዚአብሔር እየሠራ እንደሰው የተመላለሰው አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ከምንገምተው በላይ፤ ሰሚውን የሚማርኩ፤ አስተማሪ የሆኑ ነገሮችን ፈጽሟል፡፡ አምላክ ሆኖ ሳለ የፈጠረውን ሥጋ መልበሱ፣ ባዕለ ጠጋ ሆኖ ሳለ በከብት በረት መወለዱ፣ የዓለም ባለቤት ሆኖ ሳለ ራሱን የሚያስጠጋበት ማደሪያ ማጣቱ፣ ውቅያኖስን የፈጠረ ሲሆን ከሳምራዊቷ ውኃ መለመኑ፣ መምህር ሆኖ ሳለ የተማሪዎቹን እግር ማጠቡና ሁሉ የሚቻለው ሲሆን እንደምስኪን መቆጠሩ የብዙዎችን አእምሮ ማርኳል፤ አርአያነቱን የተከተሉ መልካሞችን ፈጥሯል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ወደ አባቱ የሚሄድበት ሰዓት እንደደረሰ አውቆ በመከራው ዋዜማ የመጨረሻውን እራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር በላ፡፡ ከእራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ፤ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፤ በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፡፡ የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠብ ጀመረ፡፡ ወደ ስምዖን ጴጥሮስ መጣ፡- ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን?" አለው፡፡ ኢየሱስም "ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም" ብሎ መለሰለት፡፡ ጴጥሮስ "ጌታ ሆይ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አትጠብ" አለው፡፡ ጌታ ኢየሱስ "የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፡፡ ሁለንተናው ንጹሕ ነውና፡፡ እናንተም ንጹሐን ናችሁ" አለው፡፡ ጌታ ኢየሱስ እግራቸውን አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ ደቀመዛሙርቱንም "ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ተጣጠቡ፡፡ እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም" አላቸው፡፡

www.zoorthodox.org

በቤተ ክርስቲያናችን በዓመት አንድ ጊዜ የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ይህ ሥርዓት ይከናወናል፡፡ ታላላቆች የታናናሾችን እግር ያጥባሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን አርአያነት ትውልዱ እንዲከተል በተግባር በተገለጠ አገልግሎት ታስተምራለች፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ጌታና መምህር ሆኖ ሳለ ራሱን ዝቅ አድርጎ በትሕትና የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ፡፡ የሰው ልጅ ሊያገለግል እንደመጣ በተግባር አሳየ፡፡ ልጆች ሌሎችን በትሕትና እናገልግል፡፡ ዝቅ ብለን እናገልግል ከፍ አድርጎ ይሾመናልና፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ጌታ ከሐዋርያቱ በመጀመሪያ የማንን እግር አጠበ?
2. ጌታ የመጨረሻውን የፋሲካ እራት መቼ በላ?
3. በቤተ ክርስቲያን የእግር አጠባ ሥርዓት የሚከናወነው ለምንድን ነው? መቼ ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በሰሙነ ሕማማት የጸሎተ ሐሙስን የኅፅበተ እግር ሥርዓት እንዲመለከቱ ይጋብዝ፡፡
- ሌሎችን እንዴት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ያስረዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢየሱስ የቤተ ሳይዳውን እውር ፈወሰ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማንኛውም ደዌ እንደሚፈውስ ለልጆች ማሳወቅ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ዮሐ. ፰÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማር. ፰÷፳፪-፳፮፣ ማቴ. ፲፩÷፳፰ እና ኢሳ. ፶፱÷፩-፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ጌታ ኢየሱስ ወደ ቤታቸው ሄዶ የፈወሳቸው እነማን ናቸው?
- ጌታ ኢየሱስ ከሞት ያስነሣው እነማንን ነው?
- ጌታ ኢየሱስ ካደረጋቸው የፈውስ ተአምራት መካከል የትኛው ይደንቃችኋል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ አራት ሺሕ ሰዎችን በእጁ ተአምራት ካጠገበ በኋላ ወደ ቤተሳይዳ መጣ፡፡ ዓይነ ስውር አመጡለት፡፡ የታወረውን ዓይኑን ዳስሶ እንዲፈውሰው ለመኑት፡፡ ጌታ ኢየሱስም እውሩን እጁን ይዞ እየመራ ከመንደር አወጣው፡፡ በዓይኑም ላይ ምራቁን እንትፍ ብሎ እጁንም ጭኖበት "አንዳች ታያለህ?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ማየት የተሳነው የቤተ ሳይዳ ሰው "ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ" አለው፡፡

ጌታ ኢየሱስ አጥርቶ ባላየው ሰው ዓይን ላይ እጁን ጫነበት አጥርቶም አየ፤ዳነም ከሩቅ ሳይቀር ሁሉን ተመለከተ፡፡ ጌታ ኢየሱስ "ወደ መንደሩ አትግባ በመንደሩም ለማንም አንዳች አትናገር" ብሎ በሰላም አሰናበተው፡፡

ልጆች ሕሙማን፣ ሸክም የከበዳቸውንና ቀን የከፋባቸውን ምንዱባን ወደ ክርስቶስ ዕረፍት መጥራት ይጠበቅብናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከመፈወሱ በፊት መንደር ከተባለው ከዘረኝነት፣ ከነጠኝነት፣ ከጠባብነት፣ ከጨለምተኛነትና ከከንቱ አመለካከት ለይቶ እጃችንን ይዞ ያወጣናል፤ ወደ ልበ ሰፊነት፣ ወደ ዕረፍት ሰገነትና ወደ ፍጹማን ክብር ይመራናል፡፡ ነገሮችን አጥርተንና አርቀን ማየት እስከንችል ድረስ ቀኝ እጁን ይጭንብናል፡፡ ወደ ቀደመ ክፉ ሥራችን እንዳንመለስ አስጠንቅቆና ከችግር አላቆ ወደ ቤታችን ይመልሰናል፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች ወደ ክርስቶስ መጥተው ወይም ክርስቶስ ወደ እነርሱ ሄዶ የፈወሳቸው ሰዎች ለሕይወታቸው ዘላቂ መፍትሔና የማያዳግም ፈውስ አግኝተዋል፡፡ ወደ እርሱ መጥቶ በባዶ እጅ አፍሮ የሚመለስ የለም፡፡ የዳሰሱት ሁሉ ተፈውሰዋል፡፡ የማንኛውም

ችግር መፍትሔ፣ የትኛውም ጥያቄ መልስና ማንኛውም ደዌ ፈውስ ያለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ሳይዳ ያገኘውን ዐይነ ስውር ፈወሰው፤ እውሩም አጥርቶ አየ፡፡ በጌታ ኢየሱስ ዘንድ ጥያቄ ሁሉ መልስ፤ ችግር ሁሉ መፍትሔ ዕንቆቅልሽ ሁሉ ፍቺ አለው፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ጌታ ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ እውሩን ሲያመጡለት ምን አደረገ?
2. ጌታ ኢየሱስ ዓይነ ስውሩን ከፈወሰው ለኋላ ምን አዘዘው?
3. መንደር የተባለ ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በመንገድ የሚያጋጥሟቸውን ማየት የተሳናቸውን ሰዎች እንዲረዱ መንገድ ሲያቋርጡ እጃቸውን ይዘው እንዲያሻግሯቸው ይምከራቸው፡፡
- በእምነታቸው ጽናት ስለተፈወሱ ሰዎች ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ምጽዋት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ያላቸውን በማካፈል ለድሆች ቸርነት ማድረግን እየተለማመዱ እንዲያድጉ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል" ምሳ. ፲፱÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ. ፲፯÷፲፱-፴፩፣ ሉቃስ. ፲፬÷፲፫ እና ማቴ. ፳፭÷፴፭-፵፯

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ምጽዋት ምንድን ነው?
- ለድሆች ቸርነት አድርጋችሁ ታውቃላችሁ?
- ድሆችን በመርዳታችን ምን እንጠቀማለን?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ምጽዋት ማለት ካለን ነገር ለሌሎች ማካፈል ማለት ነው፡፡ ምጽዋት ችግረኞችን በማሰብና በመርዳት በእግዚአብሔር የምንታሰብበት እና በረከት የምናገኝበት የትሩፋት ሥራ ነው፡፡ እኛ ከእግዚአብሔር ተቀበልን፤ እግዚአብሔር ደግሞ በድሆች በኩል ይቀበለናል፡፡ ጠቢቡ ሰለሞን "ለድሃ ቸርነት የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል" በማለት እንዳስተማረን ለድሆች ማድረግ ለእግዚአብሔር ማድረግ ነው፡፡ ብድራት ሳንጠብቅ የተቸገሩትን እንርዳ፤ የድሆች ዕዳ ከፋይ እግዚአብሔር በምድር በረከትን በሰማይ ገነትን ያወርሰናል፤ በትንሣኤ ጉባኤ ዋጋችንን ይከፍለናል፡፡

ምጽዋት መመጽወት ከተቀባዩ በላይ ለሰጪው ይጠቅማል፡፡ ለተቀባዩ እንደዕዳ ሲሆን ለሰጭው ግን የደስታ ምንጭ ነው፡፡ መስጠት ደስታን ያስገኛል፤ መቀበል ደግሞ ዕዳ አለው፡፡ ሌሎችን ስንረዳ እኛን የሚረዳንን እናገኛለን፡፡ በሰው መከራ ሳንጨክን ለድሃው ተቆርቋሪ ከሆን መልካም ብድራት ይጠብቀናል፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ሰጪ ካደረገን በደስታ እንስጥ፡፡ እግዚአብሔር ሰጪውን ተቀባይ፤ ተለማኙን ለማኝ፤ ባዕለ ጠጋውን ድሃ፤ ንጉሡን ተራ ሰው ማድረግ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር የምንሰጠው አያሳጣን እንጂ ከሰጠን በደስታ መስጠት አለብን፡፡ ምጽዋት ሌሎች የሚታሰቡበትና የሚጎበኙበት የትሩፋት መንገድ ነው፡፡ አብርሃም እንግዶችን በመቀበል፤ ኢዮብ ድሆችን በመንከባከብ፤ ክርስቶስ ሰው የራቃቸውን በመርዳት ምሳሌ ሆነውልናል፡፡ ጠያቂና ደጋፊ ሰው ለሌላቸው ረዳት ሰው ሆኖ መገኘት ትልቅነት ነው፡፡ ልጆች በጎ ማድረግ ጥቅሙ ለራስ ነው፡፡ ዛሬ በጎ የሚያደርጉ በጎውን ዘመን ዓይኖቻቸው ያያሉ የእግዚአብሔር ጥበቃ ከክፉ ይጋርዳቸዋል፡፡

የድሃውን ጩኸት ያልሰማ ሰው እግዚአብሔር ልመናውን አይሰማለትም፡፡

## ማጠቃለያ

ምጽዋት ካለን ነገር ለድሆች ማካፈል ማለት ነው፡፡ የድሃውን ጩኸት ቸል ሳይል የሚሰማው አምላክ ድሆችን በኑሮ እንድናግዛቸው ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ምጽዋት በመመጽወት እግዚአብሔርን እናስደስት፡፡

## ጥያቄዎች

1. ምጽዋት ምንድን ነው?
2. ለድሆች ምንድን መመጽወት እንችላለን?
3. እንግዶችን በመቀበል የሚታወቀው አባት ማን ነው?
4. ለድሃ የሚሰጥ ለማን ያበድራል?
5. ምጽዋት ከተቀባዩና ከሰጪው ለማን ይጠቅማል?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ካላቸው ነገር በጋራ ለድሆች እንዲመጸውቱ ያድርግ፡፡
- መምህሩ ለድሆች ምን ሊሰጡ እንደሚችሉ ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዕርገተ ክርስቶስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ስለ ክርስቶስ ዕርገት እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው" ሐዋ. ፩÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሐዋ. ፩÷፪-፲፩ እና ሉቃስ. ፳፬÷፶-፶፫

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ክርስቶስ በተነሣ በስንተኛው ቀን ዐረገ?
- ዕርገት ማለት ምን ማለት ነው?
- ክርስቶስ በየት ተራራ አጠገብ ዐረገ?
- ክርስቶስ ሲያርግ እነማን አዩት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀናት ከደቀመዛሙርቱ ጋር በፍቅር ቆየ፡፡ ቃሉን እንዲያስተውሉ መጻሕፍትን እንዲረዱ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፡፡ ለሥራው ሕያዋን ምስክሮች እንደሆኑ ነገራቸው፡፡ ኃይልን ከአርያም እስኪልክላቸው ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አስጠነቀቃቸው፡፡

እስከ ቢታንያም አወጣቸው፤ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው፡፡ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፡፡ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው፡፡ ደቀመዛሙርቱ ጌታችንን ወደሰማይ እያረገ ሲሄድ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት በአጠገባቸው ቆሙ፡፡ "እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችሁ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል" አሏቸው፡፡ ደቀመዛሙርቱም በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ፡፡

www.zoorthodox.org

ክርስቶስ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ" ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት በመንፈስ ከእነርሱ ጋር ነበር፤ ተገልጦም ያነጋግራቸው ነበር፡፡ ደቀመዛሙርቱ ወደ ክብሩ ዓለም የተመለሰውን በድል ያረገውን ጌታ እየባረኩ በደስታ ኖሩ፡፡ ዕርገት ማለት ወደላይ ከፍ ከፍ ማለት ሲሆን የመሬትን የስበት ኃይል የሚያሸንፍ ከፍታ ነው፡፡ ክርስቶስ ወደሰማይ ያረገው የመሬት የስበት ኃይል ሳይገድበው ነው፡፡ የክርስቶስ ዕርገት ቀድሞ በትንቢት የተነገረ፤ በሚያምኑት ዘንድ በናፍቆት ሲጠበቅ የቆየ እና በራሱ በጌታችን የተሰበከ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ በተነሣ በአርባኛው ቀኑ በድል ዐረገ፡፡ ወደ ሰማይ እያረገ ሲሄድ እንዳዩት ደግሞ ባልዳነው ዓለም ላይ ሊፈርድ ይመጣል፡፡ ማረጉን አምነን ዳግም መምጣቱን እንናፍቅ፡፡

## ጥያቄዎች

1. ወደ ሰማይ ያረገው ማን ነው?
2. ዕርገት ማለት ምን ማለት ነው?
3. ጌታ ከማረጉ በፊት ደቀመዛሙርቱን ምን ነገራቸው?
4. ዕርገቱን የሰበኩት መላእክት ስንት ናቸው?
5. መላእክቱ የገሊላ ሰዎችን ምን አሏቸው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ዕርገተ ክርስቶስን በሥዕል ሠርተው እንዲያሳዩ ያድርግ፡፡
- ስለ ዕርገት መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እንግዶችን መቀበል በረከት እንደሚያስገኝ ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" ዘፍ. ፲፰÷፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፲፰÷፩-፲፮፤ ፳፩÷፯ እና ዕብ. ፲፫÷፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የአብርሃም ሥራ ምን ነበር?
- ስለ አብርሃም የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡
- ልጆች የእንግዳ መቀበል ጥቅም ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም እግዚአብሔርን ባለማወቅ ለብዙ ዘመናት የኖረ ከብዙ ዘመናት በኋላ ፈጣሪውን እግዚአብሔር አምላኩን አውቆ ሲመሽ የተሰበሰበ አባት ነው፡፡ አብርሃም እውነተኛውን አምላክ ፍለጋ ብዙ ደክሟል፡፡ የፀሐይ አምላክ እግዚአብሔር ሲገለጥለት የሰላምና የዕረፍት ሃገር ተሰጠው፡፡ አብርሃም እግዚአብሔርን ቃል በቃል ብዙ ጊዜ አናግሮአል፡፡ ወራሽ ልጅ እንዲሰጠው ለምኖአል፡፡

ከዕለታት በአንድ ቀን አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ አድባር ተገጠለት፡፡ አብርሃም ዐይኑን አነሣና ሲመለከት ሦስት/ሥላሴ/ ሰዎች አየ፤ ሊቀበላቸው ሮጠ፤ ወደ ምድርም ሰግዶ "አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምንሃለሁ" በማለት ወደቤቱ ጋበዛቸው፡፡ እቤቱ አስገብቶ እግራቸውን አጠበ፡፡ የሰባውን ፍሪዳ አርዶ ቤት ያፈራውን አቅርቦ አስተናገዳቸው፡፡

www.zeorthodox.org

እነርሱም "ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት?" አሉት፡፡ አብርሃምም "በድንኳኑ ውስጥ ናት" አላቸው እነርሱም "የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ ሚስትህ ሣራ ልጅን ታገኛለች" አሉት፡፡ ሣራ በድንኳኑ ደጃፍ በስተኋላው ሳለች ይህንን ሰማች፡፡ አብርሃምና ሣራ በዕድሜአቸው ሸምግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር፤ በሴቶች የሚሆነው ልማድ ከሣራ ተቋርጦ ነበር፡፡ ሣራም በልብዋ "ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ሸምግሎአል፤ ብላ አሰበች፡፡ እነርሱም "ሣራ በልብዋ ስለምን ሳቀች በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" አሉት፡፡ ጊዜው ሲደርስ ሣራ እንደ ቃሉ ወለደች፡፡ ስቃ ስለነበር የልጁ ስም

ይስሐቅ ተባለ፡፡ ይስሐቅ ማለት እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎልኛል ይህንንም የሚሰማ ሁሉ በእኔ ምክንያት ይስቃል” ማለት ነው፡፡ አብርሃም እንግዳ ሰው ለመቀበል በከፈተው ደጅ እግዚአብሔር ጎበኘው፡፡ በቃል የጠየቀውን የልመናውን መልስ በአካል መጥቶ መለሰለት፡፡ እግዚአብሔርን በፍጹም መለኮታዊ ግርማውና ልዕልናው ማየት አይቻልም፡፡ ለአብርሃም የተገለጠው አብርሃም ሊያየው በሚችለው መጠን በሰው አምሳል ነው፡፡ ፍጻሜው ግን ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ የአብርሃምን ዘር ይዞ በሥጋ መገለጡ ነው፡፡ እግዚአብሔር በአብርሃም ድንኳን መገኘቱ የአብርሃምን ዘር ይዞ ከሥጋና ከደም ጋር ተካፍሎ በሞት ፍርሃት የተያዙትን ነጻ እንደሚያወጣ ለማጠየቅ ነበር፡፡ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ይህን አድርጎታል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት፡፡ አብርሃም ጌታውን በድንኳኑ አስተናገደ፡፡ እግዚአብሔር ወደ አብርሃም ቤት ሲገባ የአብርሃምን ጥያቄ መለሰ፤ ዕንቆቅልሹን ፈታ፤ የጎደለውን ሞላ፡፡ ቤታችን በእግዚአብሔር ሲጎበኝ እንዲህ ይሆንልናል፡፡ ስለዚህ እንግዶችን በደስታ እንቀበል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. አብርሃም ማን ነው?
2. እግዚአብሔር ለአብርሃም በየት ተገለጠለት?
3. ሣራ ለምን ሣቀች?
4.. ይስሐቅ ማለት ምን ማለት ነው?
5. ይስሐቅ በስንት ቀኑ ተገረዘ?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል አንዱ ታሪኩን ደግሞ እንዲናገር ያድርግ፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጰራቅሊጦስ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሰጪ፣ ምስጢርና ቋንቋ ገላጭ የአማኞችም አጽናኝ እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" ሐዋ. ፩÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፳፬÷፵፱-፶፫፣ ሐዋ. ፳፩÷፩-፵፯ እና ዮሐ. ፲፮÷፯-፲፭

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ጰራቅሊጦስ ማለት ምን ማለት ነው?
- መንፈስ ቅዱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ የወረደው ክርስቶስ ወደ ሰማይ ባረገ በስንተኛው ቀን ነው?
- ስለ መንፈስ ቅዱስ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ከዕርገተ ክርስቶስ በኋላ ደቀመዛሙርቱ በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ተሰብስበው በጸሎት ይተጉ ነበር፡፡ በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፡፡ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው፡፡ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ አደረባቸው ፡፡መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር፡፡

በዓሉን ለማክበር የተሰበሰቡ አይሁድ ተደነቁ፡፡ በየቋንቋቸው ሲናገሩ ሰሙ፡፡ "እነዚህ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? የገዛ ቋንቋችንን እንዴት ሊያውቁና ሊናገሩ ቻሉ?" በማለት ተጠያየቁ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ያስገኘውን ጥቅም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ማደሩን፤ የትንሣኤውን ወንጌል፤ የማዳኑን ዜና፤ የምሥራቹን ድምፅ ሰበከላቸው፡፡ እነርሱም "ምን እናድርግ?" በማለት ከልባቸው ተመለሱ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም "ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ" አላቸው፡፡ ሦስት ሺሕ ሰዎች በአንድ ስብከት ተመለሱ ተጠመቁም፡፡ ያም ዕለት የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ይባላል፡፡

www.zoorthodox.org

ጰራቅሊጦስ ማለት አጽናኝ፤ በመንገድ ደጋፊ፤ ረዳት ማለት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ለማጽናናት ወደ ዓለም ስለመጣ ጰራቅሊጦስ ተብሏል፡፡ የአገልጋዮች ሩጫ፣ የምእመናን ጉዞ የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት አፈጻጸም ያለ መንፈስ ቅዱስ አይከናወንም፡፡ መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መንፈስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የቤተክርስቲያን መሪ እና የመምህራን መምህር ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ

ሕይወት ሰጪና ምስጢር ገላጭ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ጰራቅሊጦስ ማለት አጽናኝ (ረዳት) ማለት ነው፡፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ለማጽናናት ወደ ዓለም መጣ፡፡ መንፈስ ቅዱስ የቤተክርስቲያንን የልደት በዓል በእሳት ላንቃና በዓለም ቋንቋ አከበረ፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሊቃውንት ምስጢር ገላጭ የፍጥረታት ሕይወት ሰጭ ነው፡፡

## ጥያቄዎች

1. ጰራቅሊጦስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ስም ተናገሩ?
3. በበዓለ ሃምሳ ምን ተደረገ?
4. ለደቀመዛሙርቱ ስንት ቋንቋ ተገለጠ?
5. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ስለ ጰራቅሊጦስ መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡
- በዓሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚከበር ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ካህናትን ማክበር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በጸጋ የሾማቸውን በፍቅር ተቀብሎ ማክበር እንደሚገባ ልጆች አውቀው በተግባር እንዲገልጹ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር እንደ ላከኝ ታውቀላችሁ" ዘኁ. ፲፮÷፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘኁ. ፲፮÷፲፫-፴፫፣ ፩ጴጥ. ፫÷፱-፫ እና ሉቃ. ፲፯÷፲፬

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ካህን ማለት ምን ማለት ነው?
- በቤተክርስቲያን ቅዱስ ቁርባን የሚያቀብሉአችሁ እነማን ናቸው?
- ካህናትን የሚሾም ማን ነው?
- የካህናት ሐላፊነት ምንድን ነው?
- ካህናት ለምን አስፈለጉ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ካህናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተላኩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡ ካህናት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ይተጋሉ፡፡ ካህናት የአማናዊው እረኛ የኢየሱስ ክርስቶስ እንደራሴዎች ናቸው፡፡ ኢየሱስ በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ ነው፡፡ መንጋውን አንድ አድርጎ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ያሳድራል፤ በለምለም መስክ ያሰማራል፡፡ የእረኞች እረኛ ስለሆነ በሚገለጥበት ጊዜ ለታመኑለት አገልጋዮቹ ዋጋ ይከፍላል፡፡

www.zeorthodox.org

ካህናት እግዚአብሔር ሓላፊነት ያለበት ሥልጣን ስለሰጣቸው ስለ በጎች መጥፋት፣ መከሳት፣ መጎዳት ይጠየቃሉ፡፡ ለመንጋው ተጠንቅቀው በሚገባ እየጠበቁ በመልካም ቦታ በሰማይም በምድርም ዋጋ አላቸው፡፡ ካህናት ከእግዚአብሔር የተላኩ፤ ከሰዎች መካከል ተመርጠው ሰውን የሚያገለግሉ አገልጋዮች በመሆናቸው በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አላቸው፡፡ ልጆች ካህናትን ማክበር መስቀላቸውንም መሳለም ይጠበቅብናል፡፡ ካህናትን ማክበር የሾማቸውን እግዚአብሔርን ማክበር ነው፡፡ ካህናትን ማቃለል ያከበራቸውን አምላክ ማቃለል ነው፡፡ ካህናቱን የሚያቃልሉበትን እግዚአብሔር ይቀጣል፤ በብሉይ ኪዳን ሊቀ ነቢያት ሙሴን

የናቁትን አቤሮን፣ ዳታንና ቆሬን እግዚአብሔር ቀጥቷልና፡፡

ዳታንና አቤሮን በሙሴ ላይ ተነሡ፡፡ ባልተሾሙበት ድንኳን የካህናትን ልብስ ለብሰው ቆሙ፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ በዓመፀኞቹ ላይ ነደደ፡፡ ምድርም አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው፡፡ በሕይወታቸው ወደ ሲኦል ወረዱ፡፡ የቀሩትንም ተባባሪዎች እሳት በላቻቸው፡፡

ልጆች ከክፉዎች ድንኳን ፈቀቅ ማለት አለብን፡፡ ክፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከክፉ አድራጊዎች ዓመፃ መተባበር የኃጢአተኞችንም ሥራ መመኘት ያስቀጣል፡፡ ሳይሾሙ ሊያገለግሉ ሳይቀቡ ሊነግሡ ሳይላኩ ሊሄዱ የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው፡፡ አባቶችን የሚያቃልሉ ካህናትን የሚያዋርዱም ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ያከበረውን አለማክበር መናቅ ያስቀጣል፡፡

## ማጠቃለያ

ካህናት የሰውና የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡ ካህናት ከሕዝብ መካከል የሚመረጡ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ናቸው፡፡ ካህናትን ማክበር መንፈሳዊ ግዴታችን ነው፡፡ ካህናትን ማክበር ያስከብራል፤ አለማክበር መናቅ፣ማቃለል ግን እንደ ዳታንና አቤሮን ያስቀጣል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1.ካህናትን ባለማክበራቸው የተቀጡት እነማን ናቸው?

2.በብሉይ ኪዳን ለክህነት የተጠሩት የማን ዘሮች ነበሩ?

3.ካህናትን በማክበራችን የምናገኘውን ጥቅም ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

4. ካህናትን ስታገኙ ምን ማድረግ አለባችሁ?

## ተግባር

❖ *መምህሩ ካህናት የሚፈጽሟቸውን ተልዕኮዎች በማስረዳት የልጆች ድርሻ ምን መሆን እንዳለበት ይንገራቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

# የቅዱሳን ሐዋርያት በዓል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ክርስቶስ ጻድቃንን እንደሚባርክ ኃጥአንን እንደሚወድ ወደ ቅድስናም እንደሚመራቸው ልጆች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “የኑሯቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው” ዕብ. ፲፫÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፱÷፱ እና ሐዋ. ፪÷፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሐዋርያ ማለት ምን ማለት ነው?
- የክርስቶስ ሐዋርያት ስንት ናቸው?
- ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያቱን ወደ ዓለም የላካቸው ለምንድን ነው?
- ሐዋርያት በዘመናቸው ምን ምን ሠሩ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሐዋርያ ማለት ተጓዥ፤ መልእክት የያዘ መንገደኛ፤ የላኪውን ቃል ወደ ተላከው ሕዝብ ታምኖ የሚያደርስ ማለት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ በሥጋ ተገልጦ ባስተማረበት ዘመን ዐሥራ ሁለት ሰዎች ለሐዋርያነት ጠራ፡፡ መልእክት ሰጥቶ ወደ ጠፉት በጎች ላካቸው፡፡ ክርስቶስ ሐዋርያትን ጠርቶ አከበራቸው ወዶ አጸደቃቸው፡፡ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከውርደት ወደ ክብር አመጣቸው፡፡ እነርሱም ከልባቸው አጥብቀው ወደዱት፤ ምስክሮቹም ሆኑ፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት የምሥራቹን ድምፅ ለሰሚዎች ያደረሱ፤ የትንሣኤውን ወንጌል የሰበኩ፤ የማዳኑን ዜና ያወጁ፤ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሰማዕትነት የተቀበሉ፤ በእሳትና በውኃ ውስጥ በእምነት ያለፉ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት ድውያንን የመፈወስ፣ ሙታንን የማስነሣትና አጋንንትን የመግዛት ጸጋ ነበራቸው፡፡ ይህን ሁሉ በስሙ ሥልጣን አድርገውታል፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱሳን ሐዋርያት በዓለ ሃምሳን (ጰራቅሊጦስን) በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ሆነው አክብረዋል፡፡ በየዓመቱ የጌታን ልደትና ትንሣኤ በደስታ ያከብሩ ነበር፡፡ በዓል የእግዚአብሔርን ዕረፍት በማሰብ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ሥርዓት ነው፡፡ የሐዋርያትም ትልቅ በዓል እግዚአብሔር የሠራውን በማሰብ ማመስገን ነበር፡፡ በየሳምንቱ በሰንበተ ክርስቲያን ቅዳሴ በመቀደስና ወንጌል በመስበክ ዕረፍት በማድግ ያስቡ ነበር፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት በቤተክርስቲያናችን የሚዘከሩበት በዓላት አሏቸው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

| መስከረም 1 | ጥቅምት 12 | ኅዳር 18 | ታኅሳስ 4 | ጥር 4 | የካቲት 10 | መጋቢት 8 | ሚያዚያ 17 | ግንቦት 26 | ሐምሌ 2 | ሐምሌ 5 | ሐምሌ1 0 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በርተሎሜዎስ | ማቴዎስ | ፊልጶስ | እንድርያስ | ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎ ስ | ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ | ማትያስ | ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ | ቶማስ | ታዴዎስ | ጴጥሮስ | ናትናኤል |

## ማጠቃለያ

ሐዋርያት ጥሪውን ሰምተው ክርስቶስን የተከተሉ፤ ስለፍቅሩ ሞትን የደፈሩ አገልጋዮቹ ናቸው፡፡ የክርስቶስ የሥራው ምስክሮች ናቸው፡፡ ክርስቶስ ስላከበራቸው እናከብራቸዋለን፡፡ ቤተክርስቲያናችንም ቀን ሰጥታ ትዘክራቸዋለች፡፡

## ጥያቄዎች

1. ቅዱስ ጴጥሮስ መቼ ይዘከራል?
2. ሐዋርያት በጋራ ያከበሩት በዓል ማን ነው?
3. የክርስቶስ ሥራ የዓይን ምስክሮች እነማን ናቸው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ሐዋርያት የሚከበሩባቸውን በዓላት በጋራ እንዲያጠኑና እንዲያስታውሱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ንስሐ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ፊት የምሕረት እጅን የዘረጋበትን የንስሐ ምስጢር ለልጆች ማስተማር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡" ፩ዮሐ. ፩÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሕዝ. ፲፰÷፴-፴፪፣ ኢሳ. ፩÷፲፰-፳፣ ኢዩ. ፪÷፲፪-፲፬ እና ፩ዮሐ. ፩÷፰-፲

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ንስሐ ማለት ምን ማለት ነው?
- ስለ ሰባቱ ምስጢራት የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- የንስሐ ዓላማ ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው፡፡ እግዚአብሔር በማይመለሱ ልበ ደንዳኖች ላይ ግን የቁጣ ጅራፉን ይዘረጋል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ወዳጅ ነው፡፡ ኃጢአትን ግን ይጠላል፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ስለሚወድ ከኃጢአት የሚመለሱበትን የሕይወት መንገድ ዘረጋ፡፡ ይህ መንገድ ንስሐ ይባላል፡፡

ንስሐ ማለት ከልብ መፀፀት፣ ወደኃጢአት ላለመመለስ መወሰን እና ወደ እግዚአብሔር በፍፁም ልብ መመለስ ማለት ነው፡፡ ንስሐ የልቡና ትንሣኤ ነው፡፡ ንስሐ እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ፊት የዘረጋው የምሕረት እጅ የምንይዝበት፣ ከክፉዎች ጉባኤና ከኃጢአት የምንለይበት ሥርዓት ነው፡፡ ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ታርቀን ለመኖር የተሰጠን ዕድል ነው፡፡ ንስሐ ከኃጥአን መንደር ወደ ቅዱሳን ሰፈር የምንሸጋገርበት ድልድይ ነው፡፡

ልጆች እግዚአብሔር ይወደናል፡፡ ኃጢአት እንዳንሠራ አዝዞናል፡፡ በአጋጣሚ ብንሳሳት ደግሞ የምንመለስበትን መንገድ የምንነጻበትን ሥርዓት አዘጋጅቶልናል፣ ይህም ንስሐ ነው፡፡

በንስሐ በሚመለሱት ኃጥአን ሰማያውያን መላእክትና ምድራውያን አገልጋዮች ሐሴት ያደርጋሉ፡፡ እግዚአብሔር በንስሐ

www.zeorthodox.org

የሚመለሱትን በደስታ እጁን ዘርግቶ ይቀበላቸዋል፡፡ ከሞት ወደ ሕይወት ያሻግራቸዋል፤ ኃጢአታቸውን በልጁ ደም ደምስሶ፤ በምሕረቱ ይቀበላቸዋል፡፡

እግዚአብሔር ይቅርታን የሚሰጥ መተላለፍን የሚደመስስ አምላክ ነው፡፡ ንስሐ ለመግባት ከልባችን ወደ እግዚብሔር መመለሳችንን ማረጋገጥና ወደ ኃጢአት ላለመመለስ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ንስሐ ስንገባ በእግዚአብሔር ፊት በደልን አምኖ ይቅርታውን መለመን፤ በካህናት ፊት ቆሞ በደልን ሳንሰውር መናዘዝ፤ የበደልናቸውን ይቅርታ መጠየቅ አለብን፡፡ ልጆች መመለሳችንን የሚናፍቅና ከኃጢአት የሚያነጻ መሐሪ አባት እንዳለን ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን፡፡ ንስሐ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተዘረጋ የምሕረት ድልድይ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ይጠነቀቅልናል፡፡ ሁል ጊዜ በፊቱ በንጽሕና እንድንመላለስ ይፈልጋል፡፡ በኃጢአት ስንተዳደፍ በንስሐ እንድንመለስ ፈቅዷል፡፡ ንስሐ ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ ነው፡፡ ንስሐ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት የምንጓዝበት የሕይወት መንገድ ነው፡፡ ልጆች ኃጢአት የለብንም ማለት አንችልም፤ ሁሉም የእግዚአብሔር ክብር ጎድሎታልና ንስሐ ያስፈልገዋል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ንስሐ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በንስሐ በሚመለስ ኃጥእ ደስ የሚላቸው እነማን ናቸው?
3. ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ማነው?
4. ንስሐ እንዴት እንገባለን?
5. ንስሐ ለምን እንገባለን?

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ ልጆች ጥፋታቸውን ለካህናት እንዲናዘዙ ያድርግ፡፡

# የእመቤታችን በዓላት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር፣ ትሕትና እና በዓላት ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነሆ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ሉቃስ. ፩÷፵፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉ.ቃ. ፩÷፳፮-፶ እና ተአምረ ማርያምና ነገረ ማርያም

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እመቤታችን ማርያም የማን እናት ናት?
- የምታውቁትን የእመቤታችን ማርያምን በዓላት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
- ስለ እመቤታችን ቅድስት ማርያም የምታስታውሱትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሕጋዊ ጋብቻ ጸንተው ከኖሩት ከሐናና ከኢያቄም ተወለደች፡፡ በሦስት ዓመቷ ወደ ቤተመቅደስ አመጡአት፡፡ መልአኩ ፋኑኤል ኅብስተ ሰማይ መገባት፡፡ በቤተመቅደስ ሐርና ወርቅ እያስማማች መላእክት እያረጋጓት አደገች፡፡ ንጉሥ ውበቷን ስለወደደላት የአባቷን ቤት ረሳች፡፡ እግዚአብሔር ለአንድያ ልጁ ማደሪያነት መረጣት፣ እግዚአብሔር ወልድ ዙፋኑ አደረጋት (እናቱ አደረጋት)፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አነጻት፤ አጸናት፤ ከልሎ ከክፉ ሁሉ ጠበቃት፡፡ አምላክን በድንግልና ፀንሳ፤ በድንግልና የወለደች የአምላክ እናት ናት፡፡ እግዚአብሔር በእርሷ ያደረገውን ያስተዋለ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይላታል፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቀድማ ከአምላክ ለመታረቅ ምክንያት የሆነች የሰው ሁሉ የእርቅ ሰነድ አማላጅ ናት፡፡

www.zeorthodox.org

እመቤታችን ማርያም ያመነች ብፅዕት፤ ጌታዋን ያከበረች ትሑት፤ ጌታ ያከበራት ክብርት፤ ከክፉ የራቀች ንጽሕት፤ መልአኩ ያመሰገናት ፍስሕት ናት፡፡ እመቤታችን ማርያም የሚበላውን የሕይወት ፍሬ፤ የሚጠጣውንም የሕይወት ውኃ ስለወለደች እንወዳታለን፡፡ ቤተክርስቲያናችን እመቤታችን ማርያምን በዓመታዊና በወርኃዊ በዓላት ትዘክራታለች፡፡ ግንቦት አንድ ቀን የተወለደችበትን፤ ታህሳስ ሦስት ቤተ መቅደስ የገባችበትን፣ የካቲት ፀሥራ ስድስት ቀን ቃልኪዳን የተቀበለችበትን፤ ጥር ሃያ አንድ ቀን ያረፈችበትን፤ ኅዳር ስድስት ከስደት የተመለሰችበትን፤ ሰኔ ሃያ አንድ ቀን መቅደሷ የታነፀበትን በዓላት ታከብራለች፡፡ በአጠቃላይ

ሠላሳ ሦስት በዓላት አሏት፡፡ እመቤታችን ማርያም ከመስቀሉ ሥር ያየናት እናታችን ናት፡፡ እመቤታችን ማርያም በትሕትናዋ፣ በቅድስናዋ፣ በዝምታዋ፣ በንጽሕናዋ፣ በእምነትዋና በምስጋናዋ የሕይወት ሰባኪ ናት፡፡ በቃና ዘገሊላ "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" በሚለው የቃል ስብከትዋም ከአማላጅነት ድርሻዋ ጋር አስተምራለች፡፡

እመቤታችን ማርያምን እመአምላክ፣ እመብርሃን፣ የጌታችን እናት፣ የፍቅር እናት፣ የሰላም እናት፣ አማላጃችን እመቤቴና እናቴ ብለን እንጠራታለን፡፡

## ማጠቃለያ

እመቤታችን ማርያም ያመነች ብፅዕት፣ ጌታዋን ያከበረች ትሑት፣ ጌታ ያከበራት ክብርት፣ ትውልድ የሚወዳት ልዕልት፣ ከክፉ መንፈስ ቅዱስ የጠበቃት ንጽሕት፣ መልአኩ ተፈስሒ ያላት ፍስሕት ናት፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ከእመቤታችን በዓላት መካከል ልደቷ የሚዘከረው መቼ ነው?
2. የእመቤታችን የዕረፍት በዓል መቼ ይከበራል?
3. የእመቤታችን እናትና አባት እነማን ናቸው?
4. እመቤታችንን ስለምን እንወዳታለን?
5. ማርያምን ማን ብለን እንጠራታለን?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ስለ እመቤታችን ማርያም መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ምልጃ

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- የቅዱሳንን አማላጅነት ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**፡- “የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋች፡፡” ያዕ. ፭÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባባት**፡- ፪ነገ. ፲፫÷፳፣ ዮሐ. ፪÷፩-፲፣ ራዕይ ፭÷፰፤ ፰÷፫-፬፤ ፲፬÷፲፫

## መግቢያ

- ➔ መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ➔ ልጆች ቅዱሳን ማለት ምን ማለት ነው?
- ➔ ቅዱሳን እነማን ናቸው?
- ➔ ምልጃ ምንድን ነው?
- ➔ አንድ ሰው በቅዱሳን ምልጃ ለመጠቀም ምን ማሟላት አለበት?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱሳን የእግዚአብሔር ወዳጆች ናቸው፡፡ መከራ እንዳይነካቸው ይጠብቃቸዋል፤ ዘወትር ጆሮው ወደ ጩኸታቸው ነው፡፡ መዝ ፴፮÷፴፮-፵፤ ፴፫÷፲፭-፳፪፡፡ **ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ሰዎች ያማልዳሉ**፡፡ መልአኩ ስለ እስራኤል መማር እግዚአብሔርን ለምኖአል፡፡ ዘካ. ፩÷፲፪፡፡ **ሙሴ ስለ እስራኤላውያን ለምኖአል**፡፡ **ሙሴ** ባይኖር ኖሮ ያጠፉቸው እንደነበር እግዚአብሔር ተናግሯል፡ መዝ. ፻፭÷፳፫፡፡ **ማማለድ ማለት ማስታረቅ ስለሌሎች መለመን** ማለት ነው፡፡ የሚማለደው እግዚአብሔር ነው፡ የሚያማልዱት እግዚአብሔር የመረጣቸው ቅዱሳን ናቸው፡፡ የሚማለድላቸው በእምነት የደከሙት ናቸው፡፡

ልጆች ቅዱሳን ካረፉ በኋላ በዚህ ዓለም የሠሩት በጎ ሥራቸው ስለሚከተላቸው በዐፀደ ነፍስም ያማልዳሉ፡፡ ራዕ ፲፬÷፲፫፡፡ **ኤልሳዕ ከረፈ በኂላ ዐፅሙ ሙት አስነሥቷል**፡፡ ፪ነገ. ፲፫÷፳፡፡ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት በሞት አይቋረጥም፡፡ ቃል ኪዳናቸው ለዘላለም ነው፡፡ በሰማይ ያለው የቅዱሳን ጉባኤና በዓለም ያለው የአማኞች ጉባኤ በመንፈስ ይገናኛሉ፡፡ ቅዱሳን በእምነት የደከሙትን ኃይል በሚያደርግ ጸሎታቸው ያግዙአቸዋል፡፡

አንድ ሰው በቅዱሳን አማላጅነት ለመጠቀም በእግዚአብሔርና በሥራው፣ በወልድ በሥጋ ተገልጦ ዓለምን በማዳኑ ማመን አለበት፡፡ ንስሐ ለመግባትና በቅዱሳን ጸሎት ለመታገዝ ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡

www.zeorthodox.org

የማስታረቅን ቃል በቅዱሳን ላይ ያስቀመጠ በሞቱ የታረቀን አምላካችን ነው፡፡ ስለዚህ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለው ይለምኑናል፡፡ የአማላጅነት አገልግሎት ዓላማው ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ምልጃ ማለት የቅዱሳን የማስታረቅ አገልግሎት ማለት ነው፡፡ ቅዱሳን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቃሉ፡፡ አንድ ሰው በቅዱሳን አማላጅነት ለመጠቀም በእግዚአብሔርና በሥራው ማመን፤ ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡ የቅዱሳን ጸሎት በሥራዋ ኃይልን ታደርጋለች፤ በእምነት የደከሙትን ትደግፋለች፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ማማለድ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ተማላጁ ማን ነው?
3. የማስታረቅ ቃልን በቅዱሳን ላይ ያስቀመጠው ማን ነው?
4. ቅዱሳን በዐፀደ ነፍስ የሚያማልዱት እንዴት ነው?
5. ከሞተ በኋላ በዐፅሙ ሙት ያስነሣው ማን ነበር?

## ተግባር

- መምህሩ  በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ልጆች በቃል እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡
- ስለ ጓደኞቻቸው እንዲጸልዩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ምስጋና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ ማመስገን እንዲለምዱ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት እናቅርብለት" ዕብ. ፲፫÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ተሰ. ፭÷፲፯፣ መዝ. ፲፪÷፯ እና ሉቃ. ፲፯÷፲፩-፲፱

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልሰላቸው፡፡
- ልጆች ሰዎች ለሚያደርጉላችሁ በጎ ነገር "አመሰግናለሁ" ብላችሁ ታውቃላችሁ?
- እግዚአብሔር በሞገስና በጥበብ እያሳደጋችሁ ስለሆነ ታመሰግኑታላችሁ?
- ለምንድን ነው የምናመሰግነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ከዕለታት በአንድ ቀን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላና በሰማርያ መካከል አለፈ፡፡ ወደ መንደርም ሲገባ ዐሥር ለምፃሞችን አገኘ፡፡ እነርሱም እየጮሁ "ኢየሱስ ሆይ አቤቱ ማረን" አሉ፡፡ ጌታም አይቶ "ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ" አላቸው፡፡ ሁሉም ተፈወሱ፡፡ ከዐሥሩ አንዱ እንደተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፤ በኢየሱስ እግር ሥር በግንባሩ ወደቀ አመሰገነውም፤ እርሱም ሳምራዊ ነበረ፡፡ ኢየሱስም "ዐሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም" አለ፡፡ እርሱንም "እምነትህ አድኖሃል፤ በሰላም ሂድ" ብሎ አሰናበተው፡፡

ልጆች ወደ መድኃኔዓለም ደጅ መጥተው የተፈወሱ፣ በረከትንና ድኅነትን የተቀበሉ፣ ከችግራቸው የተላቀቁና መፍትሔ ያገኙ ብዙዎች ነበሩ፡፡ ለምስጋና የተመለሱ ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ ውለታውን የረሱ፣ ማዳኑን የዘነጉና ቀን ያወጣላቸውን አምላክ ቸል ያሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ላደረገልን መልካም ነገር ሁሉ ማመስገን አለብን፤ እንደ ሳምራዊው ለምስጋና ወደ አዳነን አምላካችን መመለስ አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች ሰዎች መልካም ሲያደርጉላችሁ "አመሰግናለሁ" ማለት ተገቢ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሰላም ጠብቆ ስለሚያኖረን፣ ቤተሰብ ስለሰጠንና ስለሚራራልን ልናመሰግነው ይገባል፡፡ ዘወትር የከንፈራችንን /አንደበታችን/ ፍሬ የምስጋናንም መሥዋዕት ልናቀርብለት ይገባል፡፡ ምስጋና ትልቁ መሥዋዕት ነው፡፡ የሚያመሰግን አንደበት ሊኖረን ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች ሁልጊዜ በነገር ሁሉ የሚወደንን አባት እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል፡፡ ሰው የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለማመስገንና መንግሥቱን ለመውረስ ነው፡፡ የምናመሰግነው የተፈጠርንበትን ዓላማ ለመተግበር ነው፡፡

## ጥያቄዎች

1. የከንፈር/አንደበት/ ፍሬ ምንድን ነው?
2. በማመስገናችን ምን እናተርፋለን?
3. ከዐሥሩ ከተፈወሱት መካከል ለምስጋና የተመለሰው ለምፃም ምን ነበረ?
4. ሰዎች መልካም ነገር ሲያደርጉልን ምን ማለት አለብን?
5. የተፈጠርንበት ዓላማ ለምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የምስጋና መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርግ፡፡
- በምስጋና ሕይወት የሚታወቁ አባቶችን ለአብነት ይጥቀስላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አብርሃምና ሣራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች ወደ አባታቸው ወደ አብርሃም ወደ ወለደቻቸው ወደ ሣራ እንዲመለከቱ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእምነታቸው ምሰሉአቸው" ዕብ. ፲፫÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኢሳ. ፶፩÷፪ እና ዕብ. ፲፩÷፰-፳

## መግቢያ

- መምህሩ የባለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ስለ አብርሃምና ስለ ሣራ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
- የአብርሃምና የሣራ ወራሽ ልጅ ማን ነበር?
- አብርሃምና ሣራ በስንት ዓመታቸው ወለዱ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ባለትዳሮች ነበሩ፡፡ አብርሃም በእግዚአብሔር ሲጠራ ሚስቱን ሣራን ይዞ ወጣ፡፡ ወደ ምድረ ርስት ባደረገው ጉዞ አልተለየችውም፡፡ አብርሃምና ሣራ የሚዋደዱና የሚከባበሩ ጥንዶች ነበሩ፡፡ አብርሃም ሣራን ያከብራትና ያዳምጣት ነበር፡፡ ሣራም አብርሃምን "ጌታ" ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት፡፡ ፩ጴጥ.፫÷፮፡፡ **አብርሃምና ሣራ የእግዚአብሔርን ጥሪ አክብረው ሲወጡ በመንገዳቸው ያጋጠሟቸውን** ፈተናዎች በጋራ አሸንፈዋል፡፡ ዘፍ. ፲፪÷፲-፳፡፡

አብርሃምና ሣራ ልጅ አልነበራቸውም፡፡ ነገር ግን ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደሆነ በማመን ጸኑ፡፡ እግዚአብሔርም ቤታቸውን ጎበኘ የሳራ ማኅፀን በወንድ ልጅ ተከፈተ፡፡ የልጃቸውንም ስም ይስሐቅ ብለው ጠሩት፡፡ ለልጃቸው እኩል እንክብካቤ አድርገዋል፡፡ ዘፍ. ፳፩÷፩-፰፡፡

www.zeorthodox.org

ሣራ በአንድ መቶ ሃያ ሰባት ዓመቷ ዓረፈች፡፡ አብርሃም አዘነ፡፡ የሚስቱን አስከሬን በኤፍሮን እርሻ ቀበረ፡፡ ዘፍ. ፳፫÷፩-፳፡፡ አብርሃም ሽመገለ ኬጡራ የተባለች ሚስት አገባ ስድስት ልጆችን ወለደ፡፡ ዘፍ. ፳፭÷፫-፯፡፡ **አብርሃም በአንድ መቶ ሰባ አምስት ዓመቱ ዐረፈ፡፡ አብርሃም በእምነት አባታችን** ነው፤ ሣራም በእምነት እናታችን ናት፡፡ አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔርን በመፍራት፣ ጥሪውን በማክበር፣ ጸንቶ በመጠበቅና ሕጉን በማክበር የእምነት አርአያዎቻችን ናቸው፡፡

አብርሃምና ሣራ እንግዶችን ሳይሰለቹ በመቀበል፣ ስለመጪው ትውልድ ተስፋ በማሰብና በመልካም ቤተሰባዊ ሥርዓት የሕይወት መምህራን ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

አብርሃምና ሣራ በእምነት የምንመስላቸው የእግዚአብሔር ወዳጆች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር የመሰከረላቸው የእምነት ሰዎች ነበሩ፡፡ ስለዚህ የኑሯቸውን ፍሬ አይተናልና በእምነታቸው ልንመስላቸው ይገባል፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. አብርሃምና ሣራ እንዴት ይጠራሩ ነበር?
2. የአብርሃምና የሣራ ትልቁ ፈተና ምንድን ነበር?
3. ከአብርሃምና ከሣራ ሕይወት ምን እንማራለን?
4. የሣራ የመጀመሪያ ስም ማን ነበር?

## ተግባር

- መምህሩ ስለ አብርሃምና ሣራ ልጆች የሚያስታውሱትን እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃልኪዳን አደረገ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ከምርጦቹ ጋር ለዘላለም ቃልኪዳን እንዳደረገ፤ ቃልኪዳናቸውንም የሚጠብቅ አምላክ እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ” መዝ. ፹፰÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፲፪÷፩-፱፣ ዘፍ. ፲፭÷፬-፲፭ እና ዘፍ. ፲፯÷፩-፳፩

## መግቢያ

- *መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡*
- *ልጆች ቃል ኪዳን ምንድን ነው?*
- *እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ያደረገው ለምንድን ነው?*
- *እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ምን ዓይነት ቃልኪዳን አደረገ?*

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም ለእስራኤል ሕዝብ አባቶች የመጀመሪያው ይሆን ዘንድ ከትውልድ አገሩ ከከለዳውያን ዑር እንዲወጣ እግዚአብሔር ጠራው፡፡ አብርሃም ከአባቱ ከታራና ከአጎቱ ልጅ ከሎጥ ጋር ሆኖ ከዑር ተነሥቶ ወደ ካራን ሄደ፡፡ ከካራን ወጥቶ ወደ ከነዓን ምድር ሲገባ ያችን ምድር ለዘሩ እንደሚሰጥ በግልጽ ተናገረው፡፡ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃልኪዳን አድርጓል፡፡

***የመጀመሪያው ቃል ኪዳን፡-*** “ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ፡፡ የሚባርኩህን እባርካለሁ የሚረግሙህ ሁሉ ይረገማሉ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፡፡” የሚል ሲሆን የሚፈጸምለት ጥሪውን አክብሮ ወዳሳየው ምድር ከወጣ ነው፡፡ ቃልኪዳኑ የበረከት ቃል ኪዳን ይባላል፡፡

***ሁለተኛው ቃል ኪዳን፡-*** “ወራሽ ልጅ እሰጥሃለሁ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ” የሚል ሲሆን የተስፋ ቃል ኪዳን ነው፡፡

www.zoorthodox.org

***ሦስተኛው ቃል ኪዳን፡-*** “ዘርህን በባርነት በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እፈርዳለሁ፤ ከዚያም በብዙ ከብት ይወጣሉ፡፡” የሚል ሲሆን የጥበቃ ቃል ኪዳን ነው፡፡

***አራተኛው ቃል ኪዳን፡-*** “ኪዳኔን በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ፡፡ ለብዙ አሕዛብ አባት ትሆናለህ፡፡ ነገሥታት ከአንተ ይወጣሉ፡፡ ቃል ኪዳኔን ከዘርህ ጋር በትውልዳቸውም ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፡፡” የሚል ሲሆን የቃል ኪዳኑን ዘላለማዊነትና

ለዘሩ ተሻጋሪነት ያመለክታል፡፡

ልጆች ኪዳነ አብርሃም በአብርሃምና በዘሩ በትውልዶች መካከል ለዘላለም የቆመ መሐላ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ቃል ኪዳን አይፈርስም፤ የዘመን ብዛት አያስረጀውም፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር ለዘላለም የሚኖር ቃል ኪዳን አድርጓል፡፡ ለአብርሃምና ለዘሩ የሙብዛት፣ የበረከት፣ የጥበቃና የተስፋ ቃልኪዳን ሰጥቷል፡፡ የቃል ኪዳኑም የሚታይ ምልክት ግዝረት ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አይረክስም፤ አያረጅም፤ አይፈርስም፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የምን ቃል ኪዳን አደረገ?
2. የአብርሃም የመጀመሪያ ስም ማን ነበር?
3. በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል ለተደረገው ቃል ኪዳን የሚታይ ምልክት ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ከጓደኞቻቸው ጋር ላላቸው መንፈሳዊ ቃል ኪዳን ዋጋ እንዲሰጡና በቃላቸው እንዲታመኑ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አብርሃም ተራበ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የሕይወትን ፈረቃ እንዲረዱ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን?" መጽሐፈ ኢዮብ ፯÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፲፪÷፲-፳ እና መዝ. ፻፴፬÷፲፫-፳፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ርቦአችሁ ያውቃል?
- እንጀራን ጠግበው ስለማያድሩ ድሆችስ አስባችሁ ታውቃላችሁ?
- አብርሃም እንዴት ተራበ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም የእግዚአብሔርን ጥሪ አክብሮ እግዚአብሔር ወዳሳየው ምድር ወደ ተስፋይቱ ሃገር ጉዞ ጀመረ፡፡ በመንገዱም ለሚመራው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ፡፡ በምድርም ሁሉ ራብ ስለሆነ አብርሃም ተራበ፡፡ እንጀራ ፍለጋ ወደ ግብጽ ተጓዘ፡፡

ልጆች እግዚአብሔር ወዳየልን የሕይወት ከፍታ፤ ወዳሰበልንም የበረከት ምድር ለመድረስ በሕይወት ፈረቃ እናልፋለን፡፡ ሕይወት ፈረቃ አላት፡፡ ሐዘንና ደስታ፣ ሞትና ሕይወት፣ ከፍታና ዝቅታ፣ ክብርና ውርደት፣ ማግኘትና ማጣት በሕይወት ገጽታ ይፈራረቃሉ፡፡ መጥገብ እንዳለ መራብም አለ፤ ማግኘት እንዳለ ማጣትም አለ፡፡ ሰው የሕይወትን ፈረቃ በማወቅ ችግሩን አቻችሎ ሩጫውን መቀጠል አለበት፡፡

አብርሃም ወደ ግብጽ ሲሄድ እንዳይገድሉት ፈራ፤ ስለ ስጋቱም ሳራን "ወንድሜ ነው በይ" አላት፡፡ እርሱዋም እንዳላት አደረገች፡፡ ፈርዖንም ሣራን ሚስቱ ሊያደርጋት ባሰበ ጊዜ እግዚአብሔር በሕልም አስደነገጠው፡፡ ሣራም ወደ አብርሃም ተመለሰች፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች ችግሮችን ላለመጋፈጥ የምንወስዳቸው እርምጃዎች፤ የምናደርገው ሽሽት፤ የምንከተላቸው መንገዶች የከፋ መከራ እንዳያመጡ መጠንቀቅ አለብን፡፡ ከእባብ ጉድጓድ ሸሽተን ወደ ዘንዶ ጉድጓድ መግባት የለብንም፡፡

## ማጠቃለያ

አብርሃም ተራበ፡፡ እንጀራ ፍለጋም ወደ ግብጽ ወረደ፡፡ የሁሉም ዓይን ተስፋ የሚያደርገው አምላክ እግዚአብሔር ምግቡን አዘጋጀለት፤ መንገዱን አቀናለት፡፡

## ጥያቄዎች

1. አብርሃም ሲራብ ወዴት ሄደ?
2. ረኃብ ምንድን ነው?
3. የሕይወት ፈረቃን እንዴት ተረዳችሁት?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች እንጀራን ጠግበው ለማያድሩ ድሆች እንጀራ እንዲቆርሱ ቸርነትም እንዲያደርጉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# አብርሃም ስጌራሩ ንጉሥ ጸሎት አደረገ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ኃይልን እንደምታደርግ ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አብርሃም ጸለየ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ሚስቱንም ባሪያዎቹንም ፈወሳቸው፡፡" ዘፍ. ፳÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳÷፩-፲፰ እና ያዕ. ፭÷፲፮

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይል ፈውስን እንደምታመጣ ታውቃላችሁ?
- ልጆች ስለ ሌሎች ጸልያችሁ ታውቃላችሁ?
- አብርሃም ማን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም በጌራራ በእንግድነት ተቀመጠ፡፡ ሚስቱን ሣራን "እኅቴ ናት" አለ፡፡ የጌራራው ንጉሥ አቤሜሌክም መልእክተኞች ላከና ሣራን ወሰዳት፡፡ እግዚአብሔርም ሌሊት በሕልም ወደ አቤሜሌክ መጣ፡፡ "የወሰድካት ሴት ባለ ባል ናትና ብትነካት ትሞታህ" አለው፡፡ አቤሜሌክም "እኅቴ ናት ያለኝ እርሱ አይደለምን?" አለ፡፡ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን "ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ አውቃለሁ እኔም በፊቴ ኃጢአት እንዳትሠራ ከለከልሁህ፡፡ አሁንም የሰውየውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል፡፡ ትድናለህም፡፡ ባትመልሳት ግን አንተና የአንተ የሆነው ሁሉ ትሞታላችሁ" አለው፡፡

አቤሜሌክ ሣራን ለአብርሃም መለሰለት፡፡ አብርሃምን ወቀሰው፡፡ ለአብርሃም መኖሪያ ሰጠው፡፡ ሣራን "ጽድቅሽ ለሰዎች ሁሉ ተገልጧል" በማለት አመሰገናት፡፡ በዚህ ሰዓት አብርሃም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን ሚስቱንና ባሪያዎቹን ፈወሳቸው፡፡ እነርሱም ወለዱ፡፡

www.zoorthodox.org

ልጆች የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ኃይል ታደርጋች፡፡ በአብርሃም ጸሎት ምክንያት እግዚአብሔር የፈውስ እጁን ዘረጋ፡፡ በቅዱሳኑ ላይ በዐመጽና በድፍረት የሚነሡትን እግዚአብሔር ይቀጣል፤ የእነርሱ የሆነውን የሚነካውንም ያስታውሳል፡፡ ልጆች እግዚአብሔር ያከበራቸውን ማክበር ይጠበቅብናል፡፡ የጌራራው ንጉሥ አብርሃምን ሲያከብር እግዚአብሔር በፈውስ አሠራር ሥርዓቱ ጎበኘው፡፡ ቤቱንም ባረከለት፡፡

## ማጠቃለያ

አብርሃም ጸለየ እግዚአብሔርም ሰማው፡፡ የጌራራውን ንጉሥ ከነቤተሰቡ ፈወሳቸው፡፡ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ኃይልን ታደርጋለችና፡፡

## ጥያቄዎች

1. አብርሃም ለማን ጸለየ?
2. እግዚአብሔር አቤሜሌክን በሕልም ምን አለው?
3. አቤሜሌክ ሣራን ባይመልስ ኖሮ ምን ይሆን ነበር?
4. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች የጸሎት ሕይወትን በተግባር እንዲለማመዱ ያድርግ፡፡
- በጸሎታቸው ኃይል ተአምራት ስላደረጉ ሌሎች ቅዱስን ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አጋርና እስማኤል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር እስራኤል ያልተገነዘባትን ባሪያ መንገዷን እንዳቀናላትና ልጇን ሕዝብ እንዳደረገላት ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የባሪያይቱን ልጅ ሕዝብ አደርገዋለሁ ዘርህ ነውና" ዘፍ. ፳፩÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፲፮÷፩-፲፮፤፳፩÷፩-፳፩ እና ገላ. ፬÷፳፩-፴፩

## መግቢያ

- መምህሩ የባለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ባሪያ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?
- ባሪያ ማለት ምን ማለት ነው?
- ስለ አጋርና ስለ እስማኤል የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አጋር የሣራ ገረድ፤ የአብርሃም ቤት ሠራተኛ ነበረች፡፡ ሣራ ለአብርሃም ልጅ እንድትወልድለት ሚስት ትሆነው ዘንድ አጋርን ሰጠችው፡፡ አብርሃምም የሣራን ቃል ሰምቶ ወደ ግብጻዊት ባሪያዋ ገባ፡፡ አጋርም ፀነሰች፡፡ እንደፀነሰች ባወቀች ጊዜ እመቤቷን ሣራን አቃለለች፡፡ ሣራም አጋርን በቤቷ አስጨነቀቻት፡፡ አጋር የስቃይ በትር ሲበዛባት ከሷ ፊት ኮበለለች፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ በውኃ ምንጭ አጠገብ በበረሐ ተገለጠላትና "የሣራ አገልጋይ አጋር ሆይ ከወዴት መጣሽ? ወዴትስ ትሄጃለሽ?" አላት፡፡ አጋርም "እኔ ከእመቤቴ ከሦራ የኮበለልሁ ነኝ" አለችው፡፡ ሦራ የሣራ የመጀመሪያ ስም ነው፡፡" መልአኩም "ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ ከመብዛቱም የተነሣ አይቆጠርም፤ ወደ እመቤትሽ ተመለሽ ከእጅዋም በታች ሆነሽ ተገዥ" አላት፡፡ አጋርም በበረሐ መልአኩን ልኮ ያጽናናትን አምላክ አመሰገነች፡፡ መልአኩ "እነሆ ፀንሰሻል ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ስሙንም እስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ፡፡" አላት፡፡ እስማኤል ማለት የሁሉም እጅ ደግሞ በእርሱ ላይ ይሆናል እርሱም በወንድሞቹ ሁሉ ፊት ይኖራል" በማለት የሚወለደው ልጇ ምን እንደሚሆን ነገራት፡፡ እርሷም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም ኤልሮኢ ብላ ጠራች፤ የሚያየኝን አየሁት ማለት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

አጋር ወደ እመቤትዋ ወደ ሣራ ተመለሰች ታዘዘችላትም፡፡ አጋር ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም በመልአክ እንደተነገራት እስማኤል አለችው፡፡ በዚህ ጊዜ አብርሃም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰው ነበር፡፡ ሣራ ይስሐቅን በወለደች ጊዜ አብርሃምን "ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አባር፤ ከልጂ ከይስሐቅ ጋር አይወርስምና" አለችው፡፡ አብርሃም ተቸገረ፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም መፍትሔ ሰጠው፡፡ "ስለ ብላቴናህና ስለ ባሪያህ አትዘን የሣራን ቃል ስማ በይስሐቅ ዘር ይጠራልና፡፡ የባሪያይቱን ልጅ ደግሞ ሕዝብ አደርገዋለሁ ዘርህ ነውና" አለው፡፡ አብርሃምም እግዚአብሔር እንዳለው አደረገ፡፡ እግዚአብሔር የባሪያይቱን ልጅ ሕዝብ ያደረገ

አምላክ ነው፡፡ አጋር በቤርሳቤህ ምድረ በዳ ተቀመጠች፡፡ አብርሃም በአቁማዳ የሰጣት ውኃ አለቀ፡፡ ብላቴናውን ከቁጥቋጦ በታች ጣለችው "ብላቴናዬ ሲሞት አልየው" ብላ ሄደች፡፡ ጮሃ አለቀሰች የልቅስዋ ድምፅ ወደ አምላክ ጆሮ ደረሰ፡፡ እግዚአብሔር መልአኩን ድጋሚ ላከላት፡፡ እግዚአብሔር የድሃዋን ጩኸት የሰማ መንገዷንም ያቀናላት አምላክ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን ጠርቶ "አጋር ሆይ አትፍሪ እግዚአብሔር የብላቴናውን ድምፅ ባለበት ስፍራ ሰምቷልና ተነሺ ልጅሽን አንሺ አሳድጊው ትልቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ" አላት፡፡ እግዚአብሔር ዓይኗን ከፈተላት የውኃ ጉድጓድም አየች በአቁማዳው ሞላች ልጇንም አጠጣች፡፡ ልጇ እስማኤል አደገ በምድረ በዳም ተቀመጠ እናቱ አጋርም ከግብጻውያን ጋር አጋባችው፡፡ ነገር ግን ከይስሐቅ ጋር አልወረሰም፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ኮብላዮቹን ከሞት መንገድ የመለሰ፤ የድሆችን ጩኸት ሰምቶ በምድረ በዳ የመገበ፤ የባሪያይቱን ልጅ ሕዝብ ያደረገ ታላቅ አምላክ ነው፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. እስማኤል ማለት ምን ማለት ነው?
2. አጋር ማን ናት?
3. ኤልሮኢ ማለት ምን ማለት ነው?
4. አብርሃም ስለ እስማኤልና እናቱ ሲጨነቅ እግዚአብሔር ምን አለው?
5. የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን ምን ብሎ አጽናናት?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል ከታሪኩ የተማሩትን ቁምነገር እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ይስሐቅ ተወለደ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ስለ ተስፋ ቃሉ የታመነ ስለመሆኑ ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደሆነ ስለቆጠረች ሣራ ዕድሜዋ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፅነስ ኃይልን በእምነት አገኘች" ዕብ. ፲፩÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፩÷፩-፯ እና ዕብ. ፲፩÷፲፩-፲፪

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ይስሐቅ እንዴት እንደተወለደ ታውቃላችሁ?
- ይስሐቅ ማለት ምን ማለት ነው?
- ይስሐቅ እንዴት ወራሽ ሆነ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃምና ሣራ ለረጅም ዓመታት ልጅ አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም "ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ" ብሎ ተስፋ ሰጠው፡፡ ኤልኤዜር እንዳይወርሰው የተጨነቀው አብርሃም ልቡ ዐረፈ፡፡ ሣራ ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደሆነ አመነች፡፡

ልጆች አብርሃም እግዚአብሔርን በድንኳኑ እንዳስተናገደ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር በፊቱ ሞገስ ያገኘውን እንግዳ ተቀባዩ የአብርሃምን ቤት ባረከ "ሣራ ቀጣይ ዓመት ትወልዳለች" አለ፡፡ ሣራ በልቧ ሳቀች፡፡ እግዚአብሔር ግን "በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" በሚለው ቃል ቡራኬውን አተመ፡፡ ሣራም ለአብርሃም ተስፋ የሰጠው ለእርሷም ምሥራችን የተናገረው እግዚአብሔር የታመነ እንደሆነ ስለቆጠረች ዕድሜዋ እንኳ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፅነስ ኃይልን በእምነት አገኘች፡፡

www.zoorthodox.org

እግዚአብሔር እንደተናገረው ሣራን አሰበ፤ እንደተናረውም ለሣራ አደረገላት፡፡ ሣራ ፀነሰች፡፡ እግዚአብሔር በቀጠሮው በቤቷ ተገኝቶ በተናገረው ወራት ፍጻሜ ለአብርሃም በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ወለደችለት፡፡ አብርሃምም በዘመኑ መጨረሻ ያገኘውን ልጁን ይስሐቅ ብሎ ጠራው፡፡ እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስድስተኛው ቀን አስገርዞ የቃል ኪዳን ማኅተም አተመበት፡፡ የዚያን ጊዜ የአንድ መቶ ዓመት ሰው ነበረ፡፡

ሣራም "እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎልኛል ይህንንም የሚሰማ ሁሉ በእኔ ምክንያት ይስቃል" አለች፡፡ ይስሐቅም የተስፋው ዘር

መጠሪያ፤ ወራሽ ልጅ ሆነ፡፡

## ማጠቃለያ

አብርሃምና ሣራ ልጅ አልነበራቸውም፡፡ እግዚአብሔር በእርጅና ወራት ልጅ እንደሚሰጣቸው ተስፋ ሰጠ፡፡ ሣራም ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደሆነ ስላመነች ይስሐቅን ዕድሜዋ ካለፈ በኋላ ወለደችው፡፡

## *ጥያቄዎች*

1. ይስሐቅ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ይስሐቅ ሲወለድ አብርሃም ስንት ዓመቱ ነበር?
3. እግዚአብሔር ለአብርሃም ምን አለው?
4. ሣራ በወለደች ጊዜ ምን አለች?

## ተግባር

- *መምህሩ ልጆች በጋራ በቃል የሚጠናውን ጥቅስ እንዲናገሩ ያድርግ፡፡*

www.zeorthodox.org

# አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕትነት አቀረበ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለእግዚአብሔር ፍጹም መታዘዝን ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አንድ ልጁን በእምነት አቀረበ እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻለው አስቧልና" ዕብ. ፲፩÷፲፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፪÷፱-፲፱ እና ዕብ. ፲፩÷፲፯-፲፱

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች እንደ ይስሐቅ ለወላጆቻችሁ ትታዘዛላችሁ?
- ይስሐቅ ማነው?
- መሥዋዕት ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጎ ወዴት እንደሚሄድ እንኳ ሳያውቅ ከቤተሰቦቹ ተለይቶ ሀገሩን ትቶ የወጣ አባት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ጊዜ ተነጋግሯል፡፡ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶለታል፡፡ ለረጅም ዓመታት የነበረውን የልጅ ናፍቆት አሟልቶለታል፡፡ ይስሐቅ የዘሩ መጠሪያና ወራሽ ልጅ ሆኖአል፡፡

እግዚአብሔር አብርሃም ሊፈትነው ፈለገ፡፡ "የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ሠዋልኝ" አለው፡፡ አብርሃም ሌላ ልጅ እንደሌለው እያወቀ፤ ወራሽ፣ የተስፋው ዘር መጠሪያና የሚጠረው አንድ ልጁን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ወሰነ፡፡ ልጁንና እንጨት በአህያ ጭኖ ወደ ሞሪያ ተራራ ገሠገሠ፡፡ ይስሐቅን ምንም ቢወደው ከሰጪው ከእግዚአብሔር እንደማይበልጥ በሥራ ለማሳየት ወደ ተራራው ሄደ፡፡

www.zeorthodox.org

በመንገድም ሲጓዙ ይስሐቅ "አባቴ አብርሃም የመሥዋዕቱ በግ ወዴት አለ?" ሲል ጠየቀው፡፡ አብርሃም "እግዚአብሔር ያዘጋጅልናል" አለው፡፡ ወደ ሞሪያ ተራራ በደረሱ ጊዜ "ልጄ ሆይ አምላኬ መሥዋዕት አድርጌ እንዳቀርብና ጠይቆኝ ወደዚህ አመጣሁህ" አለው፡፡ ይስሐቅም "አባቴ ሆይ ከእግዚአብሔር ጋር ከምትጣላ እኔን ሠዋ ነገር ግን ኅልማሳነቴ አይሎ እንዳልጎዳህ እጄንና እግሬን እሰር፤ ፊቴንም አይተህ ራርተህ እንዳትተወኝ በደንደሴ ደፍተህ ሠዋኝ" አለው፡፡

አብርሃም በልጁ ፍጹም ታዛዥነት ተደነቀ፤ እርሱም እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያነሣው እንደሚችል አምኖ እጁንና

እግሩን አሥሮ በመሠዊያው ላይ አጋደመው፡፡ ያርደውም ዘንድ ቢላዋ አነሣ፡፡

የእግዚአብሔር ድምፅ ከሰማይ መጣ "አብርሃም አብርሃም" አለው፡፡ አብርሃም "እነሆኝ" አለ፡፡ የእግዚአብሔርም ድምፅ "በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እኔን የምትፈራ እንደሆንክ አውቄአለሁ፡፡" አለው፡፡

አብርሃም ወደ ምሥራቅ ዘወር ሲል አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፡፡ በይስሐቅም ፈንታ ሠዋው፡፡

## ማጠቃለያ

አብርሃም በአንድ ልጁ ጨክኖ ለእግዚአብሔር መታመኑን በሥራ አሳየ፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ በይስሐቅ ሞትክ የሚሠዋ በግ አዘጋጀ፡፡ እግዚአብሔር ያዘጋጃል ብሎ ያመነው አብርሃምም የእምነቱን ፍሬ በሥራ አየ፡፡ ይስሐቅ የሰው ልጅ፤ አብርሃም የእግዚአብሔር አብ፤ ሞሪያ የቀራንዮ፤ በጉ የኢየሱስ ክርስቶስ፤ ዕፀ ሳቤቅ የድንግል ማርያም ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ይስሐቅ በዕፀ ሳቤቅ ታስሮ በተገኘው በግ ከሞት እንደዳነ፤ አዳምና ልጆቹ ከድንግል ማርያም በተወለደውና እግዚአብሔር አብ የዓለም መድኃኒት እንዲሆን በላከው በእግዚአብሔር በግ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ድነናል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ይስሐቅ ሊሠዋ የነበረበት ተራራ ማን ነው?
2. ይስሐቅ እንዴት ከሞት ዳነ?
3. በዱር ውስጥ የተገኘው በግ የማን ምሳሌ ነው?
4. አብርሃም የማን ምሳሌ ነበር?
5. ይስሐቅን ከሞት ለማዳን እግዚአብሔር ምን አደረገ?
6. ኢየሱስ ለምን በበግ ተመሰለ?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል ታሪኩን በአጭሩ እንዲተርኩ ያድርግ፡፡
- የመታዘዝ ጥቅም ምንድን ነው? በማለት ያወያያቸው፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ ቢጋራ ያስብላቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በሐረግ የታሰረው በግ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በሐዲስ ኪዳን ለተገለጠው አማናዊ አካል በብሉይ ኪዳን አንፀባራቂ ጥላ እንደነበረው እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" ዮሐ. ፩÷፳፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፪÷፩-፲፯፣ ኢሳ. ፶፫÷፯ እና ራዕ. ፫÷፮-፲፩

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች ሞሪያ ተራራ ላይ የተከናወነውን ቃል ኪዳን ታስታውሳላችሁ?
- ይስሐቅ ከሞት እንዴት ዳነ?
- በሐረግ የታሰረው በግ በማን ይመሰላል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም ለእግዚአብሔር ታዞ ሞሪያ ተራራ ላይ ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ሊያቀርብ በመሠውያው ባጋደመው ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ሌላ መሥዋዕት እንዳለ አመለከተው፡፡ አብርሃም በዱር ውስጥ በዕፀ ሳቤቅ (በሐረግ) የታሰረ በግ አገኘ፡፡ በይስሐቅም ምትክ አድርጎ ሠዋው፡፡ ይህ ታሪክ በሐዲስ ኪዳን ለተገለጠው የእግዚአብሔር በግ አንፀባራቂ ጥላ ነው፡፡

ልጆች በሐረግ የታሰረው በዱር ውስጥ የተገኘው በግ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ንጉሥ ዳዊት "እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥ አገኘነው" በማለት እንደተናገረው፤ ለክብሩ ካልቆሙ ሰዎች መካከል ለክብሩ ለይቶ በንጽሕና ካሰጌጣት ድንግል የተገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ዱር የተባለው ምንድን ነው?

www.zeorthodox.org

ልጆች በደጅ ተወልዶ ወደ ዘላለም ቤቱ ያስገባን ጌታ ኢየሱስ በበግ ይመሰላል፡፡ ዮሐንስ መጥምቅ ክርስቶስን ሲያየው "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" በማለት ለዓለም አስተዋውቆታል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ "ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም" በማለት በዝምታ ያስተማረ የዋህ በግ እንደሆን መስክሮአል፡፡ ዮሐንስ አፈወርቅ "በቁጣ ቢሰቡት በፍቅር ተከተላቸው" እያለ እንደበግ የዋህ እንደነበረ ተናግሮአል፡፡ በራእየ ዮሐንስ በጉ ኢየሱስ አምልኮና ውዳሴ ሲቀበል ቅዱሳን የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ሲቀኙለት እንደታረደ በግ ሆኖ ቆሞ እናየዋለን፡፡ በመጀመሪያ ምጽአቱ እንደበግ በየዋህነት ምስኪን ሆኖ የመጣው ጌታ በዳግም ምጽአቱ መንጋው እንደተነካበት አንበሳ በኃይል ይመጣል፡፡ በእርግጥ እርሱ

ማኅተሙን የፈታ መጽሐፉን የዘረጋ የይሁዳ አንበሳ ነው፡፡ ራእ. ፭÷፭፡፡

ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት ያስወገደ የእግዚአብሔር በግ ነው፡፡ በቀራኒዮ መሥዋዕት ሆኖ በቤዛነቱ እንደተቤዠን ያሳያል፡፡ በብሉይ ኪዳን ብዙ በጎች ለዓለም አልበቁም ነበር፤ አንድያ ልጁ ግን ለዓለም ሁሉ የሚበቃ በግ ነው፡፡ የሰው በግ ኃጢአትን አላነጻም ነበር፤ የእግዚአብሔር በግ ግን ኃጢአትን በደሙ አነጻ፡፡ በግ የዋህ ነው፤ ኢየሱስም በልቡ የዋህ በኑሮው ትሑት ነው፡፡ በግ ታጋሽ ነው ኢየሱስም ታጋሽ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ይስሐቅ በሐረግ ተይዞ የተገኘው በግ ምትክ ሆኖለት ከሞት እንደዳነ ሁሉ፤ እኛም ሐረገ ወይን ከተባለችው ከድንግል ማርያም የተገኘው የእግዚአብሔር በግ ምትክ (ቤዛ) ሆኖን ሞታችንን ሞቶልን፤ ቁስላችን ቆስሎልን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረናል፡፡

## ጥያቄዎች

1. ሐረገ ወይን ማን ናት?
2. ስለ በጉ ኢሳይያስ ምን አለ?
3. በጉ በራእየ ዮሐንስ እንዴት ተገለጠ?
4. ኢየሱስ በግ መባሉ ለምንድን ነው?
5. ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ እንዴት ይገለጣል?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በቃል የሚጠናውን ጥቅስ እንዲያስታውሱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የያዕቆብ ሕልም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ለሚሰደዱት የመንገድ ተስፋና የኑሮ አለኝታ እንደሆነ ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በምትሄድበት መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ" ዘፍ. ፳፰÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፰÷፲-፳፪ እና ዮሐ. ፩÷፶፩

## መግቢያ

- *መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡*
- *ልጆች ያዕቆብ ለምን ተሰደደ?*
- *ሕልም አይታችሁ ታውቃላችሁ? ምን አያችሁ?*
- *የራእይና የሕልም ልዩነት ምንድን ነው?*

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

*ያዕቆብ ከአባቱ የወንድሙን በረከት ወሰደ፡፡ ዔሳው በወንድሙ አታላይነት ተከፍቶ ያዕቆብን አሳደደው፡፡ ያዕቆብም ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ሄደ፡፡ ወደ ሎዛ ደረሰ፡፡ ፀሐይ ወደ ማደሪያዋ ተመልሳ ነበርና በዚያ አደረ፡፡ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፡፡ ሕልምም አለመ፡፡ እነሆ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር፡፡ እነሆም እግዚአብሔር በላዩ ቆሞበት ነበር፡፡ ያዕቆብን እግዚአብሔር ተናገረው "የአባትህ የአብርሃም የይስሐቅ አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ የተኛህበትን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ፡፡ ዘርህ እንደ አሸዋ ይሆናል፡፡ በምትሄድበትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሀለሁ ወደዚህችም ምድር እመልስሃለሁ፡፡ የነገርኩህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህም፡፡" አለው፡፡ ያዕቆብም በደስታ ብዛት ከእንቅልፉ ነቃ፡፡ "በእውነት እግዚአብሔር በዚህ አለ፡፡ ይህ ስፍራ የሰማይ ደጅ ነው፡፡" አለ፡፡ ማለዳም ተነሥቶ ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ሃውልት አድርጎ አቆመው፤ በላዩም ዘይት አፈሰሰበት፡፡ የስፍራውንም ስም ቤቴል ብሎ ጠራ፤ ትርጓሜው የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው፡፡*

www.zeorthodox.org

*ያዕቆብ "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን በምሄድበትም መንገድ ቢጠብቀኝ የምለብሰውን ልብሴን ቢሰጠኝ ወደ አባቴ ቤት በጤና ብመለስ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፡፡ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጣለሁ" ብሎ ተሳለ፡፡*

*ልጆች ያዕቆብ ያየው መሰላል የእመቤታችን የማርያም ምሳሌ እንደሆነ ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ተናግሯል፡፡ ቅዱስ*

ኤፍሬምም በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ መስክሮአል፡፡ ያዕቆብ ዘሥሩግ ደግሞ በሥጋ የተገለጠው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በማለት “ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ” የሚለውን የክርስቶስን ትምህርት በማስረጃነት ያቀርባል፡፡ ዮሐ. ፩÷፶፪፡፡ **የሁሉም ሊቃውንት ትምህርት በምስጢር ይገናዘባል፡፡**

## ማጠቃለያ

ያዕቆብ በስደት ሳለ በሎዛ ሲያድር ሕልም አየ፡፡ እግዚአብሔርም በመንገዱ ሁሉ ሊጠብቀው ቃል ገባለት፡፡ የሁለት ክፍል ሠራዊት አድርጎ መለሰው፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በሕልም በራእይና በተፈጥሮ ይገለጥ ነበር፡፡

## ጥያቄዎች

1. ያዕቀብ ያደረባት ስፍራ ማን ናት?
2. ቤቴል ማለት ምን ማለት ነው?
3. ያዕቆብ በሕልሙ ምን አየ?
4. እግዚአብሔር ለያዕቆብ በሕልሙ ምን ነገረው?
5. ያዕቆብ ሲነቃ ምን አደረገ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡
- ሕልም በመንፈሳዊ ሕይወት በሚል ርእስ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# በትምህርት ውጤታማ መሆን

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ልጆች በሥጋዊ ትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፦** "ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ትበልጣለች፤ የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም" ምሳ. ፰÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፦** ፩ነገ. ፫÷፱-፲፪ እና ቆላ. ፬÷፲፬

## መግቢያ

- *መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡*
- *ልጆች በሥጋዊ ትምህርታችሁ ስኬታማ ናችሁ?*
- *የጥናት መርሐ ግብር አላችሁ?*
- *በቀን ስንት ሰዓት ታጠናላችሁ?*
- *ተምራችሁ ወደፊት ምን መሆን ትፈልጋላችሁ?*

## የሳምንቱ ትምህርት፦

ልጆች ትምህርት ዓለምንና በዓለም ውስጥ ያለውን ለማወቅ፣ የአኗኗርና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት፣ ራስንና ሌሎችን ለመጥቀም ያገለግላል፡፡ የትምህርት ዓላማው ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ ትምህርት የበለጠ ለመሥራት፣ ነገሮችን በማስተዋል ለማድረግና ዓለምን የሚያስጌጥ አሻራ ለማተም ይረዳል፡፡ ትምህርት የጥበብ ደጆችን የምናንኳኳበት እጅና ወደ ዐዋቂዎች መንደር የምንገባበት መንገድ ነው፡፡

ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ትበልጣለች፡፡ ጥበብን የሚተካከል የከበረ ነገር የለም፡፡ ጥበብ የሰውን የኑሮ ዘዴዎችን ትጠቁማለች፡፡ ጥበብ በትምህርት ታድጋለች፡፡ የጥበብ መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ምሳ. ፩÷፯፡፡

www.zeorthodox.org

በመንፈሳዊው ዓለም ሰገነት ላይ የምናውቃቸው ጠቢባን ሰዎች በሥጋዊ ዕውቀትም ስኬታማ የነበሩ ናቸው፡፡ ቅዱስ ሉቃስ በሕክምና ሙያ የሚታወቅ ሐኪም (ባለመድኃኒት) ነበር፡፡ ቆላ. ፬÷፲፬፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የግሪክን ፍልስፍና ጠንቅቆ ያውቅ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በዘመኑ ሁሉ እውቀትን ያበዛ ጥበብን ይጨምር ነበር፡፡ ልጆች በሥጋዊ ትምህርታችን ውጤታማ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ስኬታማ መሆን ይጠበቅብናል፡፡ በሥጋዊ ትምህርታችን ስኬታማ በመሆን የዓለምን የምርምር ጉዞ እግዚአብሔርን ወደማወቅ እንዲመጣ ማድረግ አለብን፡፡ እግዚአብሔር የለሽ ሥርዓትን በሚያራምዱት ላይ ተፅዕኖ ልንፈጥርና በሥጋዊው ዓለም ላይ የመንፈስ ሥርዓትን ልናሰፍን ይገባል፡፡ የጥበብ ምንጭ እግዚአብሔር ነው፡፡ ሰሎሞን የጥበብን ባለቤት

እግዚአብሔርን ጥበብ ለመነው እግዚአብሔርም በልግስና ሰጠው፡፡ አሁንም ጥበብ የጎደለው እግዚአብሔርን ቢለምን ይደረግለታል፡፡ ያዕ. ፩÷፭፡፡

***ልጆች በትምህርት ስኬታማ ለመሆን፡-***

- በክፍል ውስጥ መምህሩ ሲያስተምር ከልብ ማዳመጥ
- የዕለቱን ትምህርት ፍሬ ሐሳቦች በማስታወሻ መጻፍ
- በመርሐ ግብር የተመሠረተ ጥናት ማድረግ
- ፈተና ከመድረሱ በፊት መዘጋጀት
- ፈተናን በጥንቃቄ መሥራት
- ተጨማሪ (አጋዥ) መጻሕፍትን ማንበብ
- ያልገባንን እንዲብራራልን መጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡

## ማጠቃለያ

በሥጋዊ ትምህርት ስኬታማ መሆን ትልቅ ማዕረግ ያስገኛል፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ከስንፍና መለየት አለብን፡፡ ስለዚህ ልጆች በመርሐ ግብር እያጠናን ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቅብናል፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. ሐኪም (ባለመድኃኒት) የነበረ ወንጌላዊ ማን ነው?
2. ጥበብን ከእግዚአብሔር የለመነው ማን ነው?
3. የጥበብ መጀመሪያ ምንድን ነው?
4. በትምህርት ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ አለብን?
5. የግሪክን ፍልስፍና በመማር ተጽዕኖ የፈጠረ አባት ማን ነው?

## ተግባር

www.zeorthodox.org

✂ መምህሩ ለልጆች የጥናት መርሐ ግብር እንዲያወጡ ያድርግና ያርምላቸው፡፡

# የአገልግሎት ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች እግዚአብሔርን በሚችሉት ሁሉ በማገልገል በድጽቅ ሥርዓት እንዲያድጉ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር* የተሰጠ ይሆናል" ፩ሳሙ. ፩፥፳፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ጢሞ. ፬፥፩-፰ እና ሮሜ. ፲፪፥፯-፰

## መግቢያ

- መምህሩ ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- አገልግሎት ምንድን ነው?
- እስከ መቼ እናገለግላለን?
- የአገልግሎት ጥቅም ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የአገልግሎት ሕይወት እግዚአብሔርን አክብረን የምንባረክበት ሕይወት ነው፡፡ አገልግሎት የሰማያውያን መላእክት የማይቋረጥ ሥራ፤ የምድራውያን አማኞች የየዕለት የበረከት መንገድ ነው፡፡ አገልግሎት የተጠራንበት ዓላማ ነው፡፡ **፩ጴጥ.** ፪፥፱፡፡ አገልግሎት በጎነቱን ለዓለም የመናገር ማዳኑን የማወጅና የምሥራቹን ድምፅ የመናገር ሓላፊነት ነው፡፡

የአገልግሎት ሕይወት በጊዜ የሚገደብ አይደለም፡፡ በዕድሜ፤ በቦታና በሁኔታ አይወሰንም፡፡ ሳሙኤል ዘመኑን ሙሉ እንዲያገለግል ለእግዚአብሔር ተሰጠ፤ እርሱም ዕድሜውን ሁሉ የእግዚአብሔርን ሐሳብ አገለገለ፡፡ አገልግሎት እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ የምንወጣው አደራ የዘላለም ሕይወትን የሚያወርስ የጽድቅ ሥርዓት ነው፡፡

www.zoorthodox.org

ልጆች የአገልግሎት ዓላማ እኛን ከዓለም ርኩሰትና ከሰይጣን ወጥመድ ከዘላለምም ቅጣት ማዳን ነው፡፡ ልጆች ሰውነታችንን ከዓለም እድፈት ጠብቀን ለመኖር በእግዚአብሔር ቤት በአገልግሎት ሕይወት ማደግ አለብን፡፡ በመዘመር፣ በመስበክ፣ በመማር፣ በመቀደስ፣ በማስቀደስ፣ በመታዘዝና በሌሎችም የጸጋ ስጦታዎች ማገልገል እንችላለን፡፡ ሰጭው መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን የጸጋ ስጦታዎቹ ግን ብዙዎች ናቸውና እንደሰጠን ጸጋ ዘመናችንን ሙሉ ማገልገል አለብን፡፡

ልጆች እግዚአብሔርን በማገልገል በጽድቅ ሥርዓት ማደግ ብዙ ጥቅም አለው፡፡ እንደ ሳሙኤል በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት በሞገስና በጸጋ ያሳድጋል፡፡ የምናገለግለው አምላክ ከክፉ ጠብቆ፣ ከመልካሙ አጥግቦ፣ ከጸጋው አብዝቶ፣ በምሕረቱ ሸፍኖ

ያኖረናል፡፡ በምድርም በሰማይም የአገልግሎት ሕይወት በረከትን ያስገኛል፡፡ የአገልግሎት ሕይወት ግቡ የዘላለም ሕይወትን ጽድቁንና መንግሥቱን መውረስ ስሙንም መቀደስ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የአገልግሎት ሕይወት እግዚአብሔርን በማክበር የምንባረክበት፣ ሰዎችን በማገልገል የኅሊና ዕረፍት የምናገኝበት ሕይወት ነው፡፡ ዝቅ ብለን እናገልግል እግዚአብሔር ከፍ አድርጎ ያኖረናል፤ እንደ ሳሙኤል ዕድሜአችንን ሁሉ እግዚአብሔርን እናገልግለው፡፡

## ጥያቄዎች

1. የአገልግሎት ሕይወት ምንድን ነው?
2. ዕድሜውን ሙሉ እግዚአብሔርን ያገለገለ ማን ነው?
3. በማገልገላችን ምን እናገኛለን?
4. የአገልግሎት ዓላማና ግብ ምንድን ነው?

## ተግባር

- መምህሩ ዝቅ ብለው አገልግለው ከፍ ብለው ስለኖሩ አባቶች ይንገሯቸው፡፡
- ልጆች ወላጆቻቸውን በመታዘዝና ቤተክርስቲያንን በሚችሉት ሁሉ በማገልገል እንዲለማመዱ ያድርግ፡፡
- በቃል የሚጠናውን ጥቅስ እንዲያስታውሱ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች በትክክለኛው የበረከት መንገድ እንዲባረኩ /በረከትን እንዲቀበሉ/ መምከር፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ልጄ ሆይ መርገምህ በእኔ ላይ ይሁን" ዘፍ. ፳፯÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፯÷፩-፴፯ እና ዕብ. ፲፪÷፲፮-፲፯

## መግቢያ

- መምህሩ የባለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በረከት እንዴት ይገኛል?
- ይስሐቅ ማን ነው?
- ያዕቆብ ለምን ማጭበርበር ፈለገ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ይስሐቅ በሸመገለ ጊዜ ልጁን ዔሳውን ጠርቶ "እኔ አረጀሁ የምሞትበትን ቀን አላውቅም የጣፈጠ ምግብ አምጣልኝና ልመርቅህ" አለው፡፡ ዔሳውም ለአባቱ የጣፈጠ ምግብ አምጥቶ ሊባረክ ወደ ምድረ በዳ ለአደን ሄደ፡፡

ርብቃ የሆነውን ባወቀች ጊዜ የጣፈጠ ምግብ አዘጋጅታ ያዕቆብን "ግባና ተባረክ" አለችው፡፡ ያዕቆብ "ወንድሜ ኤሳው ፀጉራም ነው እኔ ደግሞ ለስላሳ ነኝና አባቴ ቢዳስሰኝ ያውቀኛል ስለዚህ በረከቱ በእርግማን ይቀየራል" ብሎ እምቢ አላት፡፡ ርብቃ "ልጄ ሆይ መርገምህ በእኔ ላይ ይሁን ቃሌን ስማኝ ሂደህ ተባረክ" አለችው፡፡ ያዕቆብ ምግቡን ይዞ ወደ አባቱ ቀረበ፡፡ ይስሐቅም "እንዴት ፈጥነህ መጣህ?" አለው፡፡ ያዕቆብ "እግዚአብሔር ወደ እኔ ስላቀረበው ነው" አለ፡፡ ይስሐቅ ና ልዳስህ ብሎ ዳሰሰው፡፡ "ድምፅህ የያዕቆብ ፀጉርህ የዔሳው ይመስላል" አለው፡፡ "በእርግጥ አንተ ዔሳው ነህ" አለ፡፡ ያዕቆብም "አዎ ነኝ" አለ፡፡ ማዕዱን አቀረበለት፡፡ ይስሐቅ የጣፈጠውን በላ፡፡ ልጁን "ሳመኝ" አለው፡፡ ያዕቆብም አባቱን ሳመው፡፡ ይስሐቅም አፉን ከፍቶ ልጁን መመረቅ ጀመረ፡፡ "እግዚአብሔር ከሰማይ ጠል ከምድር ስብ የእህልንም ብዛት ይስጥህ፤ አሕዛብ ይገዙልህ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን" ብሎ መረቀው፡፡ ያዕቆብ በተውሶ ሙያ በወንድሙ ስም ተባረከ፡፡ ይስሐቅ ያዕቆብን ባርኮ በፈጸመ ጊዜ ኤሳው መጣ፡፡ "አባቴ ነፍስህም ትባርከኝ ዘንድ ተነሥ ብላ" አለው፡፡ ይስሐቅም "አንተ ሳትመጣ ከሁሉ በላሁ ባረከሁትም እርሱም የተባረከ ሆኖ ይኖራል፡፡" አለው፡፡ ዔሳው አዘነ፡፡ መራራ ጩኸትም ጮኸ፡፡ "አባቴ ሆይ እኔንም ደግሞ ባርከኝ" አለው፡፡ ይስሐቅ "ወንድምህ በረከትህን ወሰደብህ" አለው፡፡ ዔሳው ያዕቆብን ለማሳደድ ተነሣ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ልጆች ያዕቆብ የራሱ ባልሆነ ማንነት በረከትን ወሰደ፡፡ እግዚአብሔር የልቡን የበረከት ናፍቆት ስላየ ወዶታል፡፡ በረከትን ከልባችን እንፈልገው፡፡ በራሳችን ማንነት ቀርበን እንባረክ፡፡

## ጥያቄዎች

1. ያዕቆብ እንዴት ተባረከ?
2. ርብቃ ልጇን ያዕቆብን ምን አለችው?
3. ይስሐቅ ዔሳውን ምን አለው?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች ከታሪኩ ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ያዕቆብ ስለመባረክ ታገለ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የበረከትን መንገድ ለልጆች ማሳወቅ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ካልባረከኝ አልለቅህም" ዘፍ. ፴፪፥፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፴፪፥፴፪-፴፪ እና ዕብ. ፲፪፥፲፮-፲፯፤ ፯፥፲፩-፲፱

## መግቢያ

- መምህሩ የባለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች በያዕቆብና በዔሳው መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ታስታውሳላችሁ?
- በረከት ምንድን ነው?
- የሚባርከው ማን ነው?
- በረከት እንዴት ይገኛል?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ያዕቆብ ዘመኑን ሙሉ በረከትን ፍለጋ ከሰዎች ጋር ታገለ፡፡ ነገር ግን እውነተኛውን በረከት ማግኘት አልቻለም፡፡ ስለዚህ የበረከት ጥሙ አልቆረጠለትም፡፡ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ በመወለድ የብኩርናን በረከት ተሻማ ግን አላገኘውም፡፡ ባደገ ጊዜ ወንድሙ ተርቦ እንጀራ ሲፈልግ በምስር ወጥ ብኩርናውን ገዛ፡፡ አባቱ ዔሳውን ሊባርክ እንዳሰበ እናቱ ስትነግረው የጣፈጠ ምግብ ለአባቱ አቅርቦ ዔሳው ነኝ ብሎ የዔሳውን ምርቃት ወሰደ፡፡ በዚህም ምክንያት ከወንድሙ ጋር ተጣልቶ ተሰደደ፡፡

እግዚአብሔር ለያዕቆብ ሞገስ ሆነው፡፡ በጎነትን አደረገለት፡፡ በመንገዱ ሁሉ ጠበቀው፡፡ ኑሮውን አቃናለት፡፡ ያዕቆብም "ወደ ተወለድህበት ምድር ተመለስ በጎነትን አደርግልሃለሁ ያልከኝ እግዚአብሔር ሆይ ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትህና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ ስንኳ የማይገባኝ ነኝ፡፡ በትሬን ብቻ ይዤ ይህን ዮርዳኖስን ተሻግሬ ነበርና አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ" በማለት እግዚአብሔርን አመሰገነው፡፡ ወደ ዔሳው እጅ መንሻ በባሪያዎቹ ላከ፡፡ ሚስቶቹንና ልጆቹን እንስሳቱንም የያቦቅን ወንዝ አሻገረ፡፡ ለብቻውም አደረ፡፡

www.zeorthodox.org

የያዕቆብን የበረከት ናፍቆት የተመለከተ እግዚአብሔር አብሮት አደረ፡፡ ያዕቆብ የአምላኩን እግር ያዘ፡፡ ሊነጋ ሲል "ሊነጋ አቅላልቶአልና ልቀቀኝ" አለው፡፡ ያዕቆብ ግን "ካልባረከኝ አልለቅህም" እያለ ለመባረክ ታገለው፡፡ እግዚአብሔርም "ስምህ ማን ነው?" አለው "ያዕቆብ" አለው፡፡ እግዚአብሔር "ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና" አለው፡፡ ያዕቆብ በመባረኩና ስሙ በመለወጡ ደስ አለው፡፡ የባረከውንም አምላክ ወደደ፡፡

የቦታውንም ስም “ጵኒኤል” ብሎ ጠራው፡፡ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ ሰውነቴም ድና ቀረች ማለት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ያዕቆብ ዘመኑን ሙሉ የመባረክ ናፍቆት ነበረው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ፡፡ እግዚአብሔርም ባረከው፡፡ ያዕቆብ በሰው ማንነት ሊባረክ መቅረቡ ልክ አልነበረም፤ በራሳችን ማንነት ልንቀርብና በረከት ልንቀበል ይገባናል፡፡

## ጥያቄዎች

1. ያዕቆብ የተባረከበት ሥፍራ የት ነው?
2. ጵኒኤል ማለት ምን ማለት ነው?
3. እስራኤል ማለት ምን ማለት ነው?
4. የያዕቆብ ስም ለምን ተለወጠ?
5. በእግዚአብሔር እንዴት እንባረካለን?

## ተግባር

- መምህሩ ከልጆች መካከል ታሪኩን እንዲከልሱና ከታሪኩ የተማሩትን ቁም ነገር እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ይስሐቅ ርብቃን አገባ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ልጆች የእግዚአብሔርን ስጦታ በደስታ እንዲቀበሉ ማድረግ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ይስሐቅ ስለሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ" ዘፍ. ፳፭÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፳፬÷፷፯፤ ፳፭÷፳፩-፳፯

## መግቢያ

- መምህሩ የባለፈውን ሳምንት ትምህርት ይከልስላቸው፡፡
- ልጆች የይስሐቅ ሚስት እንዴት እንደተገኘች ታስታውሳላችሁ?
- ጋብቻ ምንድን ነው?
- ይስሐቅ የእነማን አባት ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ከወገኖቹ መካከል ሚስት እንዲያጭለት አገልጋዩን ኢያውብርን ላከ፡፡ ኢያውብርም ርብቃን ለይስሐቅ ሚስት ትሆነው ዘንድ አመጣለት፡፡ ይስሐቅም የባቱኤልን ልጅ ርብቃን ተቀብሎ ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት፡፡ ሚስትም ሆነችው፡፡ ይስሐቅ ከእናቱ ሞት ተጽናና፤ ርብቃንም ወደዳት፡፡ ርብቃና ይስሐቅ እግዚአብሔርን በመፍራትና ጋብቻቸውን በማክበር መኖር ጀመሩ፡፡ ይስሐቅ ስለ ሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ መካን ነበረችና፡፡ እግዚአብሔር ሰማው ርብቃ መንታ ልጆች ፀነሰች፡፡ ልጆቿም በሆድዋ ውስጥ ይገፋፉ ነበር፡፡ ርብቃ "እንዲህ ከሆነ ለእኔ ምኔ ነው?" አለች፡፡ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየች፡፡ እግዚአብሔርም "ሁለት ወገኖች በማኅፀንሽ ናቸው፡፡ ሁለቱም ሕዝብ ከሆድሽ ይከፈላሉ፡፡ ሕዝብም ከሕዝብ ይበረታል፡፡ ታላቁም ለታናሽ ይገዛል" አላት፡፡ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ፡፡ ወለደችም፡፡ ቀድሞ የተወለደው ቀይ ነበር፤ ሁለንተናውም ፀጉር ለብሶ ነበር፡፡ ስሙም ዔሳው ተባለ፡፡ ቀጥሎም የተወለደው የወንድሙን ተረከዝ ይዞ ወጣ፤ ስሙም ያዕቆብ ተብሎ ተጠራ፡፡

www.zeorthodox.org

ይስሐቅና ርብቃ ሁለቱንም ልጆቻቸውን አሳደጉ፤ ይስሐቅ ዔሳውን ርብቃ ደግሞ ያዕቆብን ይወዱ ነበር፡፡ ዔሳው በአደን ሥራ ቤተሰቡን ሲያግዝ ያዕቆብ በቤት ሥራዎች እናቱን ይረዳት ነበር፡፡ ይስሐቅና ርብቃ በመልካም ሽምግልና ዐረፉ፡፡

## ማጠቃለያ

ልጆች ጋብቻ እግዚአብሔር የመሠረተው ቅዱስ ሥርዓት ነው፡፡ ስለዚህ ይስሐቅና ርብቃ በዚህ ሥርዓት ከበሩ፡፡ ልጆችን ወለዱ፤ በዘመናቸው እግዚአብሔርን አምልከው በመልካም ሽምግልና ዐረፉ፡፡

## ጥያቄዎች

1. ይስሐቅ እና ርብቃ እነማንን ወለዱ?
2. ተረከዝን ይዞ የተወለደው ማን ነው?
3. ማን ለማን ይገዛል?
4. ይስሐቅ ስለ ሚስቱ ለምን ጸለየ?

## ተግባር

- መምህሩ ልጆች በቃል የሚጠናውን ጥቅስ በጋራ እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡
- ከታሪኩ ምን እንደተገነዘቡ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ጎሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም


www.zeorthodox.org

- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት። 2000 ዓ.ም። የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም። አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )። 2000። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። 1996 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)። 1996 ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)። 19 ዓ.ም። የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው። አዲስ አበባ።
- ዳንኤል ተሾመ። 19 ዓ.ም። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች። አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)። አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ።


www.zeorthodox.org

- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ:: አዲስ አበባ::
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር ):: 2001:: የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ:: አዲስ አበባ::
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን):: 2001ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት:: አዲስ አበባ:: ባናዊ ማተሚያ::
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን):: ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር):: 1997 ዓ.ም:: የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን):: 1998ዓ.ም:: የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች:: አዲስ አበባ:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::
- .........:: አዋልድ መጻሕፍት:: ሐመረ ተዋሕዶ::


www.zeorthodox.org


- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology፡ Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;
- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.

- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሸኮርመምና ማሸኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡


www.zeorthodox.org